# የሰሜን አፍሪን አብዮት እና ኢትዮጵያ?

ኃይለመስቀል በሸዋምየለ

እ.ኤ.አ በታህሳስ 17/2011ዓ.ም ሳይዲ ቦአዚድ በምትባል የገጠር ከተማ ውስጥ ከኮሌጅ ቢ
መረቅም ስራ አጥ እንዲሆን የተገደደው መሀመድ ቡአዚዝ ራሱን እና ድሃ ቤተሰቡን ለመ
ርዳት ችግር በአቆረፈዳት ከተማ እየዞረ ለምግብ የሚሆኑ የአትክልት ፍራፍሬዎችን መሸ
ጥ ጀመረ፡፡ በዚህም ቢያንስ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ገቢ ማግኘት አስችሎታል ይህም ቢሆን
ግን የፕ/ት ቤን አሊ አምባገነናዊ አገዛዝ አፋኝ እጆች የ26 ዓመቱን ስራ-አጥ ሰው አላሰራ
አሉት፡፡ ንብረቱም በከተማይቱ ፖሊሶች ተወረሰበት፡፡ ይሄንን ኢ-ፍትሃዊነት መታገስ ያ
ቃተው ቡአዚዝ በፅንፈኛ ሙስሊሞች እንኳን የተነወረውን ራስን የማቃጠል ድርጊት ፈፀ
መ፡፡ በልጃቸው ራስን የማቃጠል የእምቢባይነት አካሄድ የተነቃቁት የገጠሪቱ ከተማ ነዋ
ሪዎች ፕ/ት ቤን አሊን ፍትህ እንዲሰጧቸው ጠየቁ፡፡ይህንን ጥያቄያቸውን ይዘው ወደ አ
ደባባይ የወጡት የሳይዲ ቦአዚድ ነዋሪዎች የተሰጣቸው ምላሽ ግን  እስር እና አፈና ነበር፡
፡ በዚህ ዓይነት ትንቅንቅ የተጀመረው የመንግስት እና የነዋሪዎቹ ግጭት ወደ ሌሎችም የ
ቱኒዚያ ከተሞች ተዛምቶ ለሁለት አስርት ዓመታት መላ ቱንዚያን በጡንቻ የመሩት ቤን
አሊን እና የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ሲዘውሩ የከረሙትን ባለቤታቸውን ከስልጣን አባረረ፡፡ የነ
ዚህ የቱኒዚያውያንን የእምቢ ባይነት ንቅናቄ ተዛማጅ ተፅዕኖ /Domino effect/ ወደ ሌ
ሎችም የሰሜን አፍሪካ  ሀገራትም ደርሶ በየሀገራቱ ያሉትን አምባገነን ስርዓቶች መነቅነቅ
ያዘ፡፡ ከግብፅ እስከ ሊቢያ፤ ከሶሪያ እስከ ጆርዳን ብሎም ከኡጋንዳ እስከ ጅቡቲ የአብዮቱ
ወላፈን መፋጀቱን አልተወም፡፡ ይሄ የአረቡ አለም መነቃቃት (The Arab awakening)
እየተባለ ሲጠራ የሰነበተው የቡአዚዝ አብዮት ታህሪር አደባባይ ሲደርስ ፕ/ት ሙባረክ
..የፌስ ቡክ ትውልድ.. ሲሉ ያላገጡበት ትውልድ በ15 ቀናት ውስጥ ጠንካራው ፈርኦናዊ
ው መንበራቸው ፈነቀላቸው፡፡ የታህሪር አደባባይ የነፃነት ሰልፈኞች ለአምባገነን አገዛዝ
እምቢ የማለታቸውን ሁነት ከቡአዚዝ ሲቀበሉ፤ መፍትሄ አድርገው የወሰዱት ራሳቸው
ላይ ክብሪት መለኮስ አልነበረም፡፡ በታህሪር አደባባይ ሲዘዋወር ለነበረው የዋሽንግተን ፖ
ስት ጋዜጠኛ የ50 ዓመቱ ካህሊፍ የተናገረው ግብፃውያንን በአግባቡ ይገልፃል፤
..እኛ ከቱኒዚያውያን ምን እንደተማርን ታውቃለህ?.. ይላል አዛውንቱ መሀንዲስ “Down
with mubarake” እያሉ ወደሚጮኹት ወጣቶች እየተመለከተ ..ራስህን አታቃጥል፤ ማ
ቃጠል ያለብህ በውስጥህ ያለውን ፍርሃት ነው የሚለውን ትምህርት ነው፡፡..

Hurriya! Hurriyya!

በየሀገራቱ ያሉትን የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች ቁጥር በየጊዜው የሚያወጣው Internet
world stats እንደሚለው በቱኒዝያ 3.6 ሚሊዮን የሚሆኑ ተጠቃሚዎች አሉ፡፡ ተጠቃ
ሚዎቹ ከአጠቃላይ የህዝቡ ቁጥር አንድ ሶስተኛ መሆናቸው ሀገሪቱን ከአፍሪካ ኢንተር
ኔት ተጠቃሚ ሀገራት ቀዳሚ ያደርጋታል፡፡ ቱኒዚያውያንም ይሄንን የኢንተርኔት ተጠቃ
ሚነታቸውን በመጠቀም ላለፉት በርካታ ዓመታት በሀገራቸው ውስጥ የተከሰቱትን ሙስ
ናን፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን፣ ስራ አጥነትን እና የአገዛዙን አፈና ለዓለም ለመንገር ሲደ
ክሙ ሰንብተዋል፡፡ ከቀደመው ዓመት ጀምሮ ቅጥ ማጣት የጀመረውን የስራ አጥነት ጉዳ
ይ ዋነኛ መሰባሰቢያ አጀንዳቸው አደረጉት፡፡ በዛው ዓመተ ምህረት የአፍሪካ ሀገራትን የ
ነፍስ ወከፍ ገቢ የሚያወጡት ምዕራባውያን ተቋማት የሀገሪቱን ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገ
ቢ 9..500 ዶላር ቢያደርሱትም 700..000 (16ኀ) የሚሆኑት ቱኒዚያውያን ግን ስራ አጥነ
ት አላመለጠም፡፡ በየዓመቱ ከሚመረቁት ወጣቶች ውስጥ ደግሞ 30ኀ የሚሆኑት ስራ-አ
ልባነት ዕጣ ፈንታቸው እንዲሆን ተገደዋል፡፡ በዚህ አይነት የኢኮኖሚ ዝቅጠት የከረመች
ው ቱኒዚያ ከቦአዚዝ ዓመፅ በኋላ ወጣቶቹ ማህበራዊ ድረ-ገፆችን በመጠቀም የስራ አጥነ
ትን ችግር ዋነኛ ማስተባበሪ ጉዳያቸው በማድረግ በተለያዩ ከተሞች ባሉ አደባባዮቻቸው
“Hurriyya (ነፃነት-ነፃነት..ን እያሉ ዘመሩ፡፡ ንቅናቄያቸውም የሰራተኛውን መደብ እና የ
ህግ ባለሞያዎችን በማካተቱ የተሻለ ብርታት አገኘ፡፡ እነዚህ ሰልፈኞች  ላይ መንግስት የ
ወሰደውን የአ ፈና እርምጃ በመቃወም የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች በተለይም የሀገሪቱ
መካከለኛው መደብ ወደ ንቅናቄው መካተቱ ነገሩን ለፕ/ት ቤን አሊ አስቸጋሪ አደረገባቸ
ው፡፡ ሁኔታውን የበለጠ ከባድ ያደረገው የንቅናቄው ኢ-ተገማችነት እና በየከተሞቹ የተካ
ሄዱት የተሰበጣጠሩ ሰልፎች ናቸው፡፡ እኒህ ድንገተኛ እና የተሰበጣጠሩ ሰልፎች ለቱኒዚ
ያውያን ሁለት ጥቅሞችን ሰጥተዋቸዋል፡፡ የመጀመሪያው ምንም እንኳን በቀጥታ የተሳተ
ፉት ሰዎች ቁጥር ትንሽ ቢሆንም (በተለይም በአመፁ የመጨረሻ ቀናት ወደ 100..000 ዝ
ቅ ቢልም) የንቅናቄው ድንገተኛነት የዓመፁን ጉልበት አጠንክሮታል፡፡ በአብዮቱ ተንታኞ
ች እንደሁለተኛነት ጠቀሜታ የሚጠቀሰው በስርዓቱ በኩል የንቅናቄው ሰልፎች መቼ እ
ና የት እንደሚደረጉ መገመት ባለመቻ ሉ ስርዓቱ ሰልፎቹን ለማፈን እንዲቸገር መሆኑ ነ
ው፡፡ ቱኒዚያውያን በእዚህ መልክ መበርታታቸውን የተገነዘቡት ፕ/ት ቤን አሊ የዜጎቻቸ
ውን ጥያቄ ያለዝባል ብለው ያሰቧቸውን የተለያዩ እርምጃዎች ለመውሰድ ሞክረዋል፡፡ የ
መንግስታቸውን ካቢኔ አባላት መገወዝ፣ ወደ 300..000 የሚጠጉ የስራ እድሎችን ለማቅ
ረብ ቃል መግባት አልፎም የአብዮተኞቹ ዋነኛ ጥያቄ ነው ብለው የገመቱት በነፃ ሀሳብን
የመግለፅ መብትን እንደሚሰጡ መግለፅ ዋነኞቹ ናቸው፡፡ እነዚህን የፖለቲካ እና የኢኮኖ
ሚ ማሻሻዮች እንደ ዋና መፍትሄ አድርገው መውሰድ የተቸገሩት የቡአዚድ ሰዎች ቤን አ
ሊ ራሳቸው ከስልጣን እንዲወርዱ ጠየቁ፡፡ ፕ/ቱም ይህን ጥያቄ መታገስ አይች ሉምና ..የ
አብዮቱ ጠባቂ.. ተብለው ለሚወደሱት ለጦር ኃይሉ አዛዥ ጄነራል ራቺድ አማር አብዮቱ
ን በጠመንጃ እንዲደፈጥጡ ቢያዟቸውም ሰውየው ለርሳቸው ትእዛዝ ባለመገዛታቸው ከ
ስልጣናቸው ተነሱ፡፡ አዲሱ ተሿሚም በእምቢ ባይነታቸው ቀጠሉ፡፡ ከነዚህ ሁለት የጦ
ር ሀይል ሹሞች በተጨማሪም ሌሎች የስርዓቱ ሚኒስትሮችም ለአብዮተኞቹ ማድላታቸ
ው የስርዓቱን መጨረሻ አቀረበው፡፡ 11ኛው ሰአት እንደአለፈ የተረዱት  ፕ/ት ቤን አሊም
ከሀገሪቱ ግምጃ ቤት ወርቅ የዘረፉትን ባለቤታቸውን ይዘው ወደ ሳዑዲ አረቢያ ኮበለሉ፡፡

ፍካሬ አብዮት ወግብፅ

በቀደመው ዓመት አምባገነኖቹን የአረቡን እና የሰሜን አፍሪካ ሀገራትን እስካጠለቀለቀው
የአረቡ መነቃቃት ድረስ የአብዮትን ምንነት በተመለከተ ገዢ ብያኔ ሆኖ የቆየው የማርክ
ስሲቶቹ ትርጓሜ ነበር፡፡ በዚህ ግራ ዘመም አስተምህሮት መሰረት አንድን ህዝባዊ ንቅናቄ
አብዮት ሊያስብለው የሚችለው የነበረውን ስርዓት የቆመባቸውን የቅቡልነት ምሰሶዎች
በሌላ እጅግ ተፃራሪ ከሆነ የርዕዮተ ዓለም መሰረት ላይ ከሚነሳ አዲስ ፖለቲካዊ እና ማ
ህበራዊ መዋቅር መተከል ሲችል ብቻ ነው የሚለው ትንታኔ ነው፡፡ በዚህ ዕይታ መሰረት
የቤን አሊም ሆነ የሙባረክ መውደቅ የአብዮት ጅማሮ እንጂ አብዮታዊ ክስተት አይደለ
ም፡፡ ለዚህም ይመስላል ይሄን የሰሜን አ ፍሪካ ህዝቦች የነፃነት እንቅስቃሴ አብዮት ከማ
ለት ይልቅ የአረቡ ዓለም መነቃቃት በሚል ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች ሊጠሩት የመረጡ
ት፡፡ ከዚህ ዓይነቱ የየሀገራቱ ዓመፅ በኋላ ግን ይሄ የአብዮት አስተምህሮት ገዢ አመለካ
ከት እየለዘበ እንደሆነ እና እኒህን ከአምባገነን ነፃ መውጣትን ዋነኛ ጥያቄያቸው ያደረጉት
ን ክስተቶች የሚያቅፍ አዲስ የአብዮት ብያኔ መምጣትን ግድ እንደሚል የተለያዩ የማህበ
ረሰብ ሳይንስ ምሁራን መሞገት ጀምረዋል፡፡ ይሄ ከቱኒዚያ እስከ ግብፅ አልፎም እስከ ሱ
ዳን የቀጠለው የሰላማዊ አመፅ ጥያቄ ውስጥ ማስገባት የጀመረው ከላይ የጠቀስነውን የአ
ብዮት ትርጓሜ ብቻ ሳይሆን በብዙ ምዕራባውያን የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን እና መንግ
ስታት ሲጠነጠን የቆየውን ..የአረቡ ዓለምም ሆነ የአፍሪካ ሀገራት ለብቸኛ ጉልበታም መ
ሪ (Strong man) እና አምባገነናዊ ስርዓት እንጂ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት የተመቸ የማ
ህበረ-ባህላዊ አወቃቀር የላቸውም.. የሚለውን የባህል ወሳኝነት አስተምህሮት (cultural
determinism Scholl of  thought) ነው፡፡ አብዮቱ በናጣቸው ሀገራት ያሉት ዜጎች በ
ነፃ የመሰብሰብንና የማሰብን እንዲሁም ከነርሱ ቁጥጥር ውጪ  ያለ አምባገነናዊ ስርዓት
ን ለመሸከም ፍቃደኛ ያለመሆናቸው ሁነት አስተምህሮቱን ስነ-አመክንዮያዊ ኪሳራ እን
ዲገጥመው ግድ ብሏል፡፡
የግብፅን አብዮት በተመለከተ በልዩ እትሙ ዝርዝር ዘገባ ያቀረበው Time መጽሔት፤
ፕ/ት ሙባረክ ፖለቲካዊ ማሻሻያዎችን እንዲያደርጉ በተጠየቁ ቁጥር መልሳቸው ምን እን
ደሆነ ሲነገረን እንዲህ ይላል ..በባለፈው ዓመት የታህሳስ ወር መጨረሻ ግድም ፕ/ት ኦባ
ማ ወደ ግብፅ የላኳቸው ልዩ ዲፕሎማት ፍራንክ ዋይዝነር ከፕ/ት ሙባረክ ጋር ስለመካ
ከለኛው ምስራቅ ጉዳዮች ከተወያዩ በኋላ ሙባረክን ስለምን ቀስ በቀስ የፖለቲካ ማሻሻያ
ዎችን እንደማያደርጉ ይጠይቋቸዋል፡፡ ፕሬዘዳንቱም እንዲህ ሲሉ መለሱ “If I do what
you want, the Islamic fundamentalists will seize power.” ፕ/ት ሙባረክ ከዚህ
ቀደም ምንም ዓይነት የፖለቲካ ተሳትፎ ኖሯቸው የማያውቀው የግብፅ ወጣቶች በታህ
ሪር አደባባይ ሰውዬው ከስልጣን እንዲወርዱ እየጠየቁ እንኳን ሳለ የወጣቶቹን ጥያቄ በ
ሙስሊም ወንድማማቾች ድርጅት ላይ ማሳበባቸውን ጀምረው ነበር፡፡.. እርሳቸውም ሌ
ሎቹ የአፍሪካ አምባገነን መሪዎች እንደሚያደርጉት የተለያዩ የፖለቲካ ጥያቄዎችን ስርዓ
ቱ በፅንፈኝነት እና በሽብርተኝነት ወደፈረጇቸው የፖለቲካ ስብስቦች ለማዞር ሞክረዋል፡
፡ የሙባረክን መልስ በይሁንታ ማለፍ ምዕራባውያኑ እንደግዴታ የሚወስዱት በሀገሪቱ
የዴሞክራሲ ስርዓት እንዲገነባ ከመፈለግ ይልቅ የግብፅን አንፃራዊ መንግስታዊ መረጋጋ
ት ቀዳሚ ምርጫቸው በመሆኑ እንደሆነ ሲነገር ሰንብቷል፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ካይ
ሮ በሰላማዊ አመፀኞች እየተናጠች ባለችበት ሰዓት እንኳ የውጪ  ጉዳይ ሚኒስትሯ ሂላ
ሪ ክሊንተን የተናገሩት ነው፡፡ ሴትዮይቱ በጥር ወር አ ጋማሽ የመንግስታቸውን አቋም ሲ
ገልፁ ..በእኛ ግምገማ ግብፅ የተረጋጋች ሀገር ነች ፡፡ ስለዚህም ፕ/ት ሙባረክ ይሄን መን
ግስታዊ መረጋጋት ሳይዘነጉ ለተቃዋሚዎቻቸው ጥያቄዎች አጥጋቢ ምላሽ መስጠት ይኖ
ርባቸዋል.. ነበር ያሉት፡፡
ይሄን መሰል አስተያየት ከምዕራባውያኑ መሪዎች ብቻም ሳይሆን ከአፍሪካ ተንታኝ ልሂ
ቃኖቻቸውም በተደጋጋሚ ይሰማ ነበር፡፡ በነሱ ምልከታ ግብፅ እጅግ ጠንካራ መንግስታ
ዊ አወቃቀር እና ቢሮክራሲ ስላላት ማህበረሰቡ አገዛዙን ከመጠየቅ ይጠነቀቃል፡፡ ከዓለ
ም ሀገራት ውስጥ በወታደሮች ቁጥር 10ኛ ደረጃ ላይ ያለችው ግብፅ ባለፈው ዓመት ከተ
ካሄዱት የመሳሪያ ሽያጮች ውስጥ ሀገሪቱ 13 ሚሊዮን ዶላር ለመሳሪያ ግዢ በማውጣት
በአራተኝነት ደረጃ ላይ ነበረች፡፡ በዚህ መልክ ይገለጽ የነበረው የግብፅ ፖሊሲያዊ መን
ግስት (Police state) ባለፈው ዓመት አጋማሽ ላይ የተጋፈጠውን ሰላማዊ ዐመፅ ስናይ የ
ግብፅ ማህበረሰብ ሲባል እንደከረመው (እንደሌሎቹ የአፍሪካ ሀገራት ሁሉ) ለአገዛዝ ተ
ገዢ (doclie) የሆነ አለመሆኑን ነው፡፡ ..ሐሐኑ GPS ፕሮግራም አዘጋጅ ፈሪድ ዘካሪያ እ
ንደሚለው ይሄ ማህበረሰብ የተለያዩ የፖለቲካ ፍላጎቶችን እና ርዕዮተ-ዓለሞችን ታግሶ አ
ልፏል፡፡ ከማርክሲዝም እስከ ፅንፈኛ የእስልምና ንቅናቄ፤ ከአረባዊ ብሔርተኝነት እስከ
ኒዩ-ሊበራል የፖለቲካ ምልከታዎች በግብፅ አደባባይ ላይ ተፈራርቀዋል፡፡ ይሄም ቢሆን
ግን እ.ኤ.አ ከ1950ዎቹ ጀምሮ የግብፅ ፈርኦኖች የሲቪል ማህበረሰቡን እንቅስቃሴ ከማ

ገድ ጀምሮ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ማስወገድ፣ ነፃ ጋዜጦችን መዝጋት፣ ተቀናቃኝ ፖለቲከ
ኞችን ማሰር አልፎም ከስርዓቱ ጋር ያልተስማሙትን አሰላሳዮች ወደ ዘብጥያ ማውረድ
ጀመሩ፡፡ ላለፉት 30 ዓመታት በግብፅ ውስጥ የሚታተሙት መጽሐፍት ቁጥርም ማሽቆ
ልቆል ጀመረ፡፡ ፕ/ት ሙባረክም በፅንፈኛ ሙስሊም ልሂቃን ሰበብ የተቃውሞውን መድ
ረክ ጭር አደረጉት፡፡
እንደ ፕ/ት ሙባረክ እና ወዳጆቻቸው እምነት ስርዓቱን የሚያቆየው የፖለቲካ መብቶች
መከበር ሳይሆን የኢኮኖሚ እድገቱ ነበር፡፡ ለዚህም እ.ኤ.አ ከ1990ዎቹ ጀምሮ ከህ.. እና የ
ዓለም ባንክ ብድር ለማግኘት ሲሉ በ..ሶሻሊስት መሰል የኢኮኖሚ አወቃቀርነት.. ሲተች የ
ነበረውን የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከያዘው ማነቆ ቀስ በቀስ ለማላቀቅ ሞክረዋል፡፡ በአውሮፓዊ
ተኮር ባህል ባደገው ልጃቸው ገማል እየተመሩ የታክስ እና የታሪፍ ማስተካከያ ለማድረግ
ሞክረዋል፡፡ የተለያዩ ተቋማት እንደሚሉትም እ.ኤ.አ ከ2006 እስከ 2008ዓ.ም የሀገሪቱ
ኢኮኖሚ በ7ኀ አድጓል፡፡ ይሄን ያህል የኢኮኖሚ እድገት ቢመዘገብም ቅሉ በአገሪቱ ውስ
ጥ ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ስርዓት ባለመኖሩ የተነሳ በማህበረሰቡ ውስጥ እጅግ ዝንፈታዊ የገ
ቢ ክፍፍል እንዲኖር ግድ ብሏል፡፡ ግና በሞስኮው ፍራንዝ የወታደር አካዳሚ ማርክሲስ
ታዊ ስልጠናቸውን የወሰዱት ሙባረክ የዘነጉት አንድ ነገር የአሜሪካንን የዴሞክራሲ ዘይ
ቤ ተቺ የነበረውን የአሌክስ ዲ ቶኬቪሊን ..ለአምባገነን አገዛዞች እጅግ አደገኛው ሙከራ
ስርዓቱ ራሱን ለማሻሻል መሞከር ሲጀምር ነው፡፡.. ማለቱን ነበር፡፡ በዚህ አይነት ግራ-ቀኝ
ሙከራዎች እየተመራ ለሶስት አስርት ዓመታት ግብፃውያንን ሲጨቁን የከረመው ፈርኦና
ዊው ስርዓት ለመውደቁ ዋነኛ ምክንያቶች ተብለው የሚጠቀሱት የስራ ዓጥነት ቁጥር መ
ብዛት እና የምግብ ዋጋ ውድነትን ተከትሎ እያደገ የሄደው የዋጋ ንረት ናቸው፡፡ እነዚህን የ
ኢኮኖሚ ጥያቄዎች ወደ ታህሪር አደባባይ ይዘው የወጡት ከሀገሪቱ ህዝብ 1/3ኛ የሚሆኑ
ት ከ30 ዓመት በታች የሆኑት ወጣቶች ናቸው፡፡ ወደ ስልጣን ከመጡ ጀምሮ የተለያዩ ብ
ሔራዊ ምርጫዎች እንዲደረጉ ቢፈቅዱም፤ የምርጫ ስርዓቱን ወደ ..የምርጫ አምባገነነት
ስርዓት.. (electoral authoritarianism) የቀየሩት ፕ/ት ሙባረክ "The praxis of the
Egyptian Revolution" በሚለው ፅሁፋቸው ሞና ኢል ጎህብሻይ ..በምርጫ የመቀየራቸ
ውን እድል ዝግ እንደሆነ ያደረጉት ፕ/ት ሙባረክ ግብፃውያን በተራቸው በሰላማዊ አመ
ፅ እንዲያወርዷቸው ተገደዋል፡፡.. ያሉት የታህሪርን አደባባይ ትርክት በሚገባ ይገልፃል፡፡

## ኢትዮጵያውያን ያምፃሉ?

የሰሜን አፍሪካን የነፃነት ጉዞ የታዘቡ ኢትዮጵያውያን የፖለቲካ ልሂቃን፣ ተንታኞች እና
ለዘብተኛ ምሁራን ለዚህ ጥያቄ የሚሰጡት መልስ እጅግ የተለያየ ነው፡፡ የኢትዮጵያው
ን ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ሁነታዎች የአምባገነን ስርዓቶቻቸውን ከገረሰ
ሱት የዓረቡ ሀገራት ጋር ያላቸውን ተመሳስሎ ያጠኑት የነገረ-ሀብት አጥኚው ዶ/ር አክሎ
ግ ቢራራ "Ethiopia fascination with the Arab spring" በሚለው ባለሁለት ክፍል
ጽህፋቸው ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ከመጣ ከ1983ዓ.ም ጀምሮ 40 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰ
ዎች መወለዳቸው እና በ20 ዓመታት ውስጥ ኢህአዴግ የገነባው የኢኮኖሚ ስርዓት ፍላ
ጎቶቻቸውን የሚያስተናግድ ያለመሆኑ እና በሀገሪቱ ውስጥ ያለው የስራ አጥ ቁጥር ከጠ
ቅላላ ህዝቡ ከ60-70 % መድረሱ፤ አልፎም አሁን አሁን የበለጠ ከተሜ እና ምዕራብ ተ
ኮር የሆነው ይሄ የማህበረሰብ ክፍል መብዛቱ እንደ ግብፅ አቻዎቹ ሁሉ ወደ አደባባይ የ
ሚወጣበት ጊዜ ሩቅ ላይሆን ይችላል ሲሉ ተንታኔቸውን ያቀርባሉ፡፡ እርሳቸው በዚህ የ
ሀገሪቱ ተመሳስሎ ላይ ቆመው ቢከራከሩም፤ በሰሜን አፍሪካ በተካሄደው ሰላማዊ ዓመፅ
ዋነኛ ጠቀሜታ የነበረውን የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች የበዛ ቁጥር ጉዳይ ከሀገሪቱ ህዝብ
1ኀ ከሚሆነው የኢትዮጵያውያን የኢንተርኔት ተጠቃሚ ጋር ሲወዳደር የጎረቤት ሀገራትን
መሰል ማህበራዊ ድረ ገፅ ለንቅናቄው የመጠቀም ጥልቀት ባለመኖሩ ኢትዮጵያውያን ሰላ
ማዊ አብዮት ሊያነሱ አይችሉም የሚሉ ተንታኞችም አሉ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የፃፈው ጃ
ዋር መሀመድ "Ethiopia: Nonviolent straggle: Ethiopian exceptionalism?" በሚ
ለው መጣጥፉ ኢንተርነት ከመፈጠሩ በፊት የተካሄዱትን የህንድ፣ የቺሊ፣ የደቡብ አፍሪ
ካ እና የፊሊፒንስን አብዮት በመጥቀስ የኢንተርኔት ተጠቃሚነት በሀገሪቱ ዝቅ ያለቢሆን
ም ሰላማዊ ዓመፅ ለመከወን ግን ብዙም አስቸጋሪ እንዳልሆነ ይከራከራል፡፡ እንደ እርሱ
ክርክር በኢትዮጵያ ውስጥ የኢንተርኔት ተጠቃሚው በዋናነት የተማሪው እና የወጣት ም
ሁራኑ የማህበረሰብ ክፍል ከመሆኑ በተጨማሪ የአቶ መለስ ስርዓት የፕ/ት ሙባረክን ተ
ሞክሮ በመውሰድ የኢንተርኔት እና የስልክ ግንኙነቶችን ለማቋረጥ ከሞከረ ስርዓቱ የራሱ
ን የፖሊስ፣ የስለላ እና የፓርቲ ግንኙነት አደጋ ውስጥ የሚከትበት እድል መኖሩን ግምት
ውስጥ ማስገባት አለብን በሚል ነው፡፡ የሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ ወደ ግብፅ መሰል ሰላማዊ
ዓመፅ ሊያመራ መቻሉን የሚቀበሉ ነገር ግን እንዲህ አይነት ሰላማዊ አብዮት ለሀገሪቷ አ
ያስፈልጋትም ከሚሉ ፀሐፍት መሀከል አቶ ያሬድ አይቼህ ቀዳሚ ናቸው፡፡ናማሻስ case
Against Jasmine Revolution Ethiopia" በሚለው ፅሁፋቸው የ1966ቱን አብዮት አ
ስታውሰው እንደሚሉት ..አብዮት በባህሪው የማይገመት እና ፈጣን ክስተት ነው፡፡ በዚህ
ባህሪው የተነሳ አሁን በኢትዮጵያ ሊከሰት ቢችል ሀገሪቷን የሚጎዳ ክስተት ሊፈጠር ይች
ላል፡፡.. ሲሉ፤ ሆኖም ግን ሀገሪቱን ከዚህ ውጥንቅጥ ለማዳን የተሻለው መፍትሄ በገዢው
እና በተቀናቃኝ ልሂቃን መሀከል ሊኖር የሚገባው የመቻቻል ፖለቲካ እንደሆነ ፅፈዋል፡፡
ከነዚህ ክርክሮች ሳይርቅ እየቀረበ ያለው ሌላኛው ሙግት በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ ውስጥ
ከላይ የጠቀስነውን ዓይነት ሰላማዊ ዓመፅ ለማስነሳት ..የጎደሉ ነገሮች አሉ.. የሚለው የክ
ርክር ጫፍ ነው፡፡ፕ/ር መሳይ ከበደ "Are Ethiopians Angry enough to Revolt?" ብ
ለው በሰየሙት ስራቸው የሰሜን አፍሪካ ህዝቦችን ወደ አደባባይ ያስወጣቸው የአምባገነ
ናዊ አገዛዙ አፈና ብቻ ሳይሆን ከጭቆናው መከፋት የተነሳ የተፈጠረውን የህዝቦቹን የቁ
ጣ ደረጃ ወደ ዓመፅ ካልቀየሩት በቀር ሌላ ምንም ምርጫ ከማጣታቸው የተነሳ እንደሆነ
ፅፈዋል፡፡ እንደ ፍልስፍና መምህሩ ክርክር ኢትዮጵያውያን እንደ ሰላማዊ አብዮተኞች አ
ቻዎቻቸው ወደ አደባባይ የሚያስወጣ የቁጣና የንዴት ደረጃ ላይ ባለመድረሳቸው አብዮ
ት ለማንሳት ጥቂት ጊዜ ይፈልጋሉ የሚል ነው፡፡ ከፕ/ሩ ጋር የተቀራረበ ሀሳብ ያላቸው ደ
ግሞ የቀድሞው በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር የነበሩት ዴቪድ ሺን ናቸው፡፡ የኢትዮ
ጵያ መንግስት በሚቆጣጠራቸው የተለያዩ ሚዲያዎች በኩል ስለሰሜን አፍሪካው አብዮ
ት እጅግ የተመጠነ ዘገባ እያቀረቡ ነው ሲሉ የሚከሱት ፕ/ር ሺን ..የሀገሪቱ የሀገሪቱ ዜጎ
ች በስራ አጥነት እና በከፍተኛ የዋጋ ንረት ቢሰቃዩም ወደ ጎዳና ለመውጣት ግን አሁን ካ
ለው የከፋ የኑሮ መወደድን ግድ እንደሚል.. "Revolutionary winds from North to
south of the sahara" በሚለው ስራቸው ተሟግተዋል፡፡
በሀገር ውስጥም በውጭም ያሉ የሀገሪቷ የፖለቲካ ተዛቢዎች ስለሰላማዊ አመፅ ጉዳይ በ
ዚህ መንገድ እየተከራከሩም ቢሆን የገዢው ፓርቲ ሰዎች ስለሁኔታው እየሰጡ ያሉት አስ
ተያየት ጉዳዩን የበለጠ ግልፅ ያደርጋል፡፡ ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የአረቡ ዓለም መነቃ
ቃት ወደ ጎረቤት ግብፅ በደረሰበት ወቅት ለሀገር ውስጥ ጋዜጠኞች በሰጡት ቃለ-መጠይ
ቅ ..አንዳንድ ስደተኛ ፖለቲከኞች በሀገር ውስጥ ዓመፅ ለማስነሳት ፍላጎት እንዳላቸው እ
ናውቃለን፡፡ ቢሆንም ግን የሰሜን አፍሪካው ዓይነት አብዮት በሀገሪቱ ሊካሄድ የሚችልበ
ት ነባራዊ ሁኔታ ካለመኖሩ በተጨማሪ ህዝቡ የአምስት አመት ኮንትራት ስለሰጠን አመፅ
ይነሳል በሚል እንቅልፍ አጥተን አናድርም፡፡.. ማለታቸው ይታወሳል፡፡ እርሳቸው እንዲ
ህ ቢሉም ይሄን በተናገሩበት ሳምንት የወጣው የእንግሊዙ ዘጋርዲያን ጋዜጣ በበኩሉ በ
ባለፈው ግንቦት ወር ..በቃ.. በሚል መፈክር አሰባሰቢነት ስር ዓመፅ ይነሳል ከሚል ..ስጋ
ት.. የተነሳ አቶ መለስ ከስርዓቱ የስለላ ተቋም ተወካዮች ጋር እጅግ ተደጋጋሚ ስብሰባ ያደ
ርጉ እንደነበር አስነብቧል፡፡ አቶ መለስ ከላይ ከጠቀስነው አስተያየታቸው ውጪ ሰላማዊ
ው አብዮት በሀገሪቱ እንደማይነሳ ማስተማመኛ እንደሰጣቸው የሚታመነው በተለያዩ የ
ፖለቲካ ተንታኞች የሚጠቀሰው ከ2002ቱ ምርጫ በኋላ እራሳቸው በይፋ የተናገሩለት የ
አውራ ፓርቲነት ጉዳይ ነው፡፡ ፓርቲያቸው 99.6ኀ የምርጫ ድምፅ ከማግኘቱ በመነሳት
ራሱን ወደ አውራ ፓርቲነት (Dominant party) መቀየሩ ምንም ነውር እንዳልሆነ የስዊ
ድንን እና የጃፓንን ተሞክሮ በመጥቀስ የምርጫውን ውጤት በመንተራስ የተቃውሞ ድ
ምፅ ለማሰማት የሞከሩትን የፖለቲካ ተንታኞች ሞግተዋል፡፡ ኢህአዴግ በ99.6ኀ ምርጫ
ውን ማሸነፉንም ሆነ 5 ሚሊዮን አባላት እንዳሉት ማመኑ ከሰላማዊ አብዮት ሊያድነው
እንደማይችል ከሚሞግቱት ተንታኞች አንደኛው ጃዋር መሀመድ፤ የቱኒዚያው ቤን አ
ሊ በባለፈው ዓመት ብሔራዊ ምርጫ በ89ኀ ማሸነፋቸውን እና የፕ/ት ቤን አሊን ፎቶ የ
ያዙ ቲሸርቶችን ይለብሱ የነበሩትን ሁለት ሚሊዮን የቤን አሊ ፓርቲ አባላትን የሚጠቅሰ
ው ጃዋር ..የቱኒዚያ ተሞክሮ የአውራ ፓርቲነትን አደጋ በበቂ ያሳያል.. ሲል "Tunisia Vs
Ethiopia could the Northern wave reach East?" በሚለው ፅሁፍ ተከራክሯል፡፡
በኢትዮጵያ ሰላማዊ አብዮት ይነሳል አይነሳም የሚለው ክርክር እንዳለ ሆኖ በሀገር ውስ
ጥ ካሉ ፖለቲከኞች መሀከል ለመስከረም 21/2004ዓ.ም በመስቀል አደባባይ ሰላማዊ ሰል
ፍ እንደሚጠሩ የተናገሩት የመኢዴፓ ሊቀመንበር እና የሀገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ ከሰሜን
አፍሪካው አብዮት አንፃር በመተንተን ጥብቀት ያላቸውን ፅሁፎች ሲፅፍ የነበረው ጋዜጠ
ኛ እስክንድር ነጋ በ..ሽብርተኝነት.. ክስ ወደ እስር ቤት መግባታቸው ጉዳዩ ላይ መከራከ
ርን የሚመች እንዳላደረገው አንዳንድ ተንታኞች ይናገራሉ፡፡
የሀገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታ በዚህ መሰል ሁነት ውስጥ እያለፈም ቢሆን የ1966ቱን አብዮት
ጨምሮ በተለያዩ የሀገራችን የፖለቲካ ክስተቶች ላይ የበዙ ስራዎችን ያቀረቡት ፈረንሳዊ
ው ጋዜጠኛ ሬኒ ሌፎርት "Will Ethiopia next?" በሚለው ፅሁፋቸው ስለሰላማዊው አ
መፅ ጉዳይ እንዲህ ሲሉ ደምድመዋል፡፡ "No one had predicted either the erup-
tion or the course of the Arab spring. Ethiopia may still surprise."

# የአስተሳሰብን ህግ ካልጠበቅን ለመግባባት ያቅተናል

ፐ/ር መስፍን ወልደ ማርያም

ለብዙ ዓመታት የማውቀው ወዳጄ ገብሩ ታረቀኝ በፍትህ ጋዜጣ ላይ፣ የማላውቀው አቶ ዓሥራት በአድማስ ጋዜጣ ላይ በትግሬነታቸው ተቆርቁረውና እኔን ባዕድ አድርገው የጻፉትን አንብቤ ሁላችንንም የሚያውቁ ሌሎች ሰዎች አስተያየት እንዲሰጡበት በማለት መልስ ከመስጠት ተቆጥቤ ቆየሁ፤ ሆኖም እስካሁን ከአንድ ሰው በቀር የደረሰልኝ የለም፤ ስለዚህ እኔው ልጋፈጠው፡፡

ገብሩ ወዳጄ ነው የምለው ሰው ስለሆነ የጋለ ስሜቱን ይዞ አደባባይ ከመውጣቱ በፊት ከእኔ ጋር ጉዳዩን አንስቶ አለመወያየቱ ከሚችለው በላይ የሆነ ግፊት ቢያጋጥመው መስሎ ታየኝ፤ እንዲያውም ሌላ ሰው እሱ ያለውን ሲናገር ቢሰማ ለእኔ ቆሞ ይከራከራል ብዬ የምገምተው ሰው ነበር፤ አንድ ሳይካያትሪስት (የአእምሮ ሐኪም) ሲናገር እንደሰማሁት የጎሳ አስተሳሰብ የጎሳን ድንበር ጥሶ ወዳጅነት የሚባል ነገር አያውቅም ያለውን አስታወሰኝ፤ ይህ እንደማይሆን ተስፋ አለኝ፡፡

በምን ላይ እንደጻፍሁት ሳልናገር ለሁለቱም የትግራይ ተቆርቋሪዎች የሚከተሉትን አጫጭር ነጥቦች ላመልክታቸው፡-

1. ወያኔ "ከሚኒልክ በፊት ኢትዮጵያ አገር አልነበረችም ሲል የአፄ ዮሐንስንና የራስ አሉላን ትግሬነትና ኢትዮጵያዊነት በመካድ.. ጀመረ፤

2... የጎንደርን በሬ፣ የጎጃምን በሬ፣ የሸዋንም በሬ፣

   ባንድ አርጎ ጠመደው የትግሬው ገበሬ..

(የትግራይን የኢትዮጵያዊነት መሰረት ለማስረዳት የጠቀስሁት)

3. ..የትግሬ ዘር (ኤርትራውያንን ጨምሮ) የኢትዮጵያ መሰረት ነው፤ የትግሬ ዘር የኢትዮጵያን ታሪክ ተሸካሚ ነው፤ እንኳን በኢትዮጵያዊነታቸው ያሉትን ትግሬዎች የተገነጠሉትንም ለማጥፋት ማሰብ በምድርም በሰማይም ይቅርታ የማያስገኝ ወንጀል ነው፡፡ ከኤርትራውያን ጋር የተደረገውንም የወንድማማቾች ጦርነት አጥብቄ የተቃወምሁት በዚህ ምክንያት ነበር፤ በሰሜን ያሉትን ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን ከመቅጽበት ወደባዕድነት ለውጠን አሁን ደግሞ የተረፍነውን አጥፊና ጠፊ አድርጎ መፈረጁ ለማንም የሚበጅ አይሆንም፡፡..

ብዙ ሌሎችንም መጥቀስ እችላለሁ፤ ልብ ላለው ይበቃል፡፡

በደርግ ዘመን በዩኒቨርስቲ ውስጥ ስናወራ ስለ የአእምሮ ወዝ-አደር ስናገር አንዱ ካድሬ የአእምሮ ወዘ-አደር የሚባል ነገር የለም ብሎ ተቆጣ፤ አብረውን የነበሩት ሁሉ በስምንት ተኩል እኔ ቢሮ እንዲመጡ ጋበዝሁና መጽሐፉን ይዤ መጣሁና ለካድሬው አሳየሁት፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሌኒን ተናዶ በደርዘን የሚቆጠሩ ካድሬዎችን በአንድ ትጉህና ታታሪ ባለሙያ የሚለውጠኝ ባገኘሁ ብሏል ስል ያው የማይማር ካድሬ ተቆጣና ..አይወጣውም.... አለ፤ መቶ ብር ከኪሴ አወጣሁና አንድ ጊዜ በነፃ አስተምሬሃለሁ፤ አሁን ግን መክፈል አለብህ፤ የሌኒንን ጽሑፍ ካላመጣሁልህ መቶ ብር ታገኛለህ፤ ካመጣሁ ግን መቶ ብር ትከፍላለህ ብለው አሻፈረኝ ብሎ በስህተቱ ጸና፤ አቶ ዓሥራት ብዙውን ጽሑፎቾን አንብቤአለሁ ሲል እውነት እንዳልሆነ ስለማውቅ ውርርድ ላቀርብለት ፈልጌ ነበር፤ ስለአማራ የተናገረው እኔ የጻፍሁትን እንዳላነበበ ጥሩ ማስረጃ ነው፤ ሳያውቁ በእርግጠኛነት አዋቂ መስለው ለሚቀርቡ ቀላሉ መንገድ በአደባባይ ውርርድ ነው፤ ገብሩ ታረቀ እንኳን በአሜሪካ የፈረንጅ ልጆች ሲያስተምር ስለኖረ በአገር ውስጥ የተጻፈውን ሁሉ ማንበቡ አጠራጣሪ ነው፡፡

ለነገብሩና ለነዓሥራት ትልቁ ፍሬ ነገርና ቁም-ነገር ትግሬነታቸውን ለብቻቸው የያዙት መስሎአቸው ነው፤ በትግሬነታቸው ውስጥ አነሱንና እኔን የሚያያይዙ ብዙ ከባድ ሰንሰለቶች መኖራቸውን አያውቁም፤ ለነሱ ትግሬ ከትግሬነት ሌላ ፋይዳ ወይም ትርጉም የለውም፤ እንደዚህ ያለ ክርክር መነሳቱ ኢትዮጵያዊነት ምን ያህል እንደላላ የሚያመለክት ነው፡፡

..ማወቅ ወደ እርግጠኛነት የሚያመራው በመጠራጠርና በመጠየቅ ነው፤ አለማወቅ ግን ምንጊዜም ወደጠን ካራ የጨለማ እርግጠኛነት የሚመራ ነው፤ አለማወቅ ከኃይል ጋር ሲጋባ የአምላክን ቦታ ይይዝና እስመ አልቦ ዘይሰአኖ ይሆናል፡፡..

ሁለቱም ሰዎች፣ ፕሮፌሰር ገብሩም አቶ ዓሥራትም ባሳዩዋቸው ሁለት የእውቀት ጉድለቶች ልጀምር፤ ይህንን ማድረጉ አያስደስተኝም፤ ነገር ግን አለማወቅን ወደ እውቀት እየለወጡ ሰዎችን ማሳሳቱ፣ ከዚያም አልፎ በትግራይ ማህበረሰብ ላይ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ የጥላቻ መርዝን ለመንዛት የሚደረገውን ሙከራ አገርን የሚጎዳ ነውና ሊታለፍ አይገባም፤ ፐ/ር ገብሩም አቶ ዓሥራትም በሂሳብ ትምህርታቸው ስለ Set theory ትንሽ ቢያውቁ ..የኤርትራና የትግራይ ዜጎች..ያልሁት ደማቸውን አያፈላውም ነበር.. ትግራይ በኢትዮጵያ ውስጥ፣ ኢትዮጵያ በትግራይ ውስጥ ይገኛሉ፤ የኔ ስህተት የአንባቢዎችን ደረጃ ከፍ አድርጌ መመደቤ ነው፡፡

ሌላው የእውቀት ልዩነት ሰው የመሆን ግንዛቤያችን ነው፤ ለእኔ ሰው በቁና የሚሰፈር፣ ወይም በከረጢት የሚታሰር አይደለም፤ እያንዳንዱ ሰው በነጠላ ለራሱ ስራ ኃላፊነቱን ይወስዳል፤ እንኳን በ2004ዓ.ም ጥንትም ቢሆን ጽድቅም ሆነ ኩነኔ የግል ነው፤ በጎሳ ወይም በጅምላ አይመጣም፤ የሰው ልጅ እንደ አይጥና እንደድመት አይደለም፤ እንኳን አብሮ የኖረና የተዛመደ፣ አንዱ ለሌላው የመጨረሻ መስዋዕትነት የከፈለ ቀርቶ እንግዳም ቢሆን አንዱ ለሌላው መሰረታዊ ጠላትነት የለውም፤ ፐ/ር ገብሩና አቶ ዓሥራት እንጀራቸውን ለማብሰል ለትግሬዎች ዘብ የቆሙ መስለው ባልገባቸው ነገር ሁሉ ደማቸውን ያገነፈሉት እኔን ባዕድ በማድረግ ለመጠቀም ነው፤ ለእነሱ አዝናለሁ፤ የትግራይ ህዝብ እኔን በነሱ ዓይን እንደማያየኝ አምናለሁ፡፡

ፐ/ር ገብሩ ..እኔም እንደአስገዶም ገ/ስላሴ የወዲያ ማዶ ልጅ ነኝ.. ይላል፤ ወዲያ ማዶ ስል ትግራይ ማለቴን ማን ነገረው? ስብሐት ነጋን ወዲህ ማዶ ሳደርገው በገብሩ ግንዛቤ ትግሬ አይደለም ማለቴ ነው መሰለኝ.. ገብሩን ወዴት ከፍ ከፍ እለዋለሁ.. ገብሩ የወዲያም የወዲህም ልጅ አይደለም፤ የባህር ማዶ ልጅ ነው..

ሁለተኛ ስለኤርትራውያን የተናገረው መልካም ስሜቱን ከመግለጽ በቀር መጽሐፉን ቢያነብበው ኤርትራውያን በስሜት ሳይሆን በተግባር እሱ ..እስረኞች.. ያላቸው ሰዎች የገለጹትን እውነት ያስተባብለዋል፤ በተጨማሪም ለታሪክ ባለሙያው መንገር ካልሆነብኝ የሠርጸ ድንግልን ዜና መዋዕል ቢያነበው ከወራሪ መከላከል እንደሚችሉ ሊገነዘብ ይችላል፡፡

ሶስተኛ፣ ..የሞራል ሉዓላዊነት.. በአማርኛም ሆነ በእንግሊዝኛ አልገባኝም፤ አላግባብ ተሰካክቶ የተደነቀረ ነገር ነው፡፡

አራተኛ፣ ለኢጣልያ ገብረው የጠላት ወታደር በመሆን ወገናቸውን የወጉት ኤርትራውያን እጅና እግር መቆረጡ በአሁኑ ጊዜ ላለነው የሚዘገንን ነው፤ ነገር ግን ፐ/ር ገብሩ በዓድዋ ጦርነት በምኒሊክ አገዛዝ የተደረገውን ሲናገር በቅርቡ በማይጨው የደጃዝማች ኃ/ስላሴ ጉግሳን ሆነ በሌላ የተፈፀመን ቅጣት አለማንሳቱ፤ በአገራችንም ቢሆን የአፄ ቴዎድሮስን አልሰማም ይሆን? የአጼ ዮሐንስንስ አልሰማም ይሆን? ወይስ እኔ እንዳነሳለት ፈልጎ ይሆን? አንዳንድ ነገሮችን እየነቀሱ በማውጣት ታሪክ እንደማይጻፍ ለፐ/ር ገብሩ መንገር አያስፈልግም፤ የምኒልክን ሀጢአት ለማበራከት ከሆነ ከሸዋ ሳይወጣ በጧፍ ያነደዱትን ሊጨምርበት ይችላል፡፡

አሁን ከባድ ወደሚመስሉኝ ነጥቦች ልምጣ፤ ለእኔ እንደሚገባኝ ታሪክ ሁነትን በመግለጽ ይጀምራል፤ በትክክል ለተመዘገበው ሁነት ፍቺ መስጠት፣ ወይም ጥሩና መጥፎነቱን በመግለጽ ፍርድ መስጠት በኋላ የሚመጣ ነው፤ በሌላ አነጋገር ፍርድ ሁነትን ተከትሎ ይመጣል እንጂ የሁነቱ ፍቺ ወይም በሁነቱ ላይ የሚሰጠው ፍርድ አይቀድምም፤ ይህ ከሆነ ፈረንጆች እንደሚሉት ፈረሱን በጋሪው ለመጎተት እንደመሞከር ይሆናል፤ አጉል ድካም ነው፤ አንድ ጊዜ ብቻ አይደለም፤ ለሁለት ጊዜ ገብሩ ለማድረግ የሚፈልገው ይህንን ነው፤ ምን እንደተናገርሁ ለአንባቢው ሳይነግር፣ በራሱ ግምት የተናገርሁ ለመሰለው ነገር ፍቺና ፍርዱን መስጠት ይጀምራል፤ ይህ የእውቀትና የእውነት ፈላጊ ምሁር የአጻጻፍ ስርዓት አይደለም፤ በዚህ ጉዳይ አቶ ዓሥራት እኔ ያልሁትን በትክክል ጠቅሶ ወደራሱ አስተያየት ይሻገራል፤ ይህ ተገቢ ነው፡፡

ገብሩ ግን ..ኢትዮጵያዊ ዜግነትን በትግራይ ዜግነት መተካትዎ ምን ቢያስቡ ነው?.. ይለኛል፤ መጀመሪያ በዚህ ጉዳይ ላይ እኔ ምን እንደተናገርሁ አይገልጽም፤ የተገነጠለውን ኤርትራን ይገድፍና ዘልሎ ትግራይን ለማስገንጠል የፈለግሁ ለማስመሰል ..ምን ቢያስቡ ነው?.. ይለኛል.. ኤርትራን የጨመረ እንደሆነ ተንኮሉ ይበላሻል.. ለኢትዮጵያውያን ነግሮ ሊያስወነጅለኝ ፈልጎ ነው? ወይስ ለአስገንጣዮቹ ነግሮ ሊያስሸልመኝ.. ለተገንጣዮቹና ለአስገንጣዮቹ በስሜት ማንኛችን እንቀርባለን?

ከላይ እንደጠቀስሁት በሂሳብ ወይም በፍልስፍና ንባብ ቢደገፍ እዚህ ስህተት ላይ አይወድቅም ነበር፤ ..ምን አስበህ ነው?.. የሚለው ለመወንጀልና ለማስወንጀል የተቃጣ ለማንም ግልጽ የሆነ ንጹህ ተንኮል ነው፤ ከኢትዮጵያ ዜግነት የተለየ የትግራይ ዜግነት መኖሩን ሊነግረኝ ያሰበ ይመስላል፤ እንዲህ ያለ መያዣና መጨበጫ የሌለው ነገር እኔ አልተናገርሁም፤ በ1998 ጓደኞቼና እኔ ከተከሰስንበት አንዱ የትግሬን ዘር ለማጥፋት መሞከር የሚል ለጆሮም የሚቀፍ ነገር ነበር፤ በ1998 ፍርድ ቤት በቀረብንበት ጊዜ የዛሬው የገብሩ ጽሑፍ ቢገኝ ትልቅ ማስረጃ ሆኖ ይቀርብ ነበር፤ እግዚአብሔር ሲያወጣን ገብሩ በዚያን ጊዜ ከእኛ ጣጣ ተከልሎ በአሜሪካው ነበር፤ ዛሬም 1998 እየሸተተ ነውና ገብሩ ስራ አያጣም፡፡

አንድ የታሪክ ባለሙያ ፐ/ር ትናንት በጋዜጣ የተጻፈውን በትክክል መድገም ሲሳነው ከአስር፣ ከሃምሳ፣ ከመቶ ወይም ከዚያ በላይ የቆዩ ጉዳዮችን እንዴት አስታውሶ እውነቱን ሊናገር ነው? እኔ የጻፍሁትን እሱ በመሰለው ተርጉሞ ከአገርና ከዘመድ ጋር የሚያጣላ ከባድ ነገር ሲለጥፍብኝ በጣም ያሳዝናል፤ መቼም ኢትዮጵያ ሆነና ነው እንጂ በሌላ አገር ቢሆን የጋዜጣው አዘጋጅ ያልተባለ ነገር ተቀብሎ አያሳትመውም ነበር፤ ከዚያም በላይ ገብሩና እኔ ስለምንተዋወቅ እሱ የጻፈውን ሌላ ሰው ቢጽፈው ገብ

ሩ ይቃወማል ብዬ ሙሉ እምነት ነበረኝ፤ እንዲህ ዓይነት ጭራሽ ትርጉም የሌለው ነ
ገር እኔ አልወጣኝም፤ ከኢትዮጵያ የተለየ የትግራይ ዜግነት የሚባል ነገር መኖሩንም
አላውቅም፤ ዜግነት ምን እንደሆነና ከጎሳዊነት የተለየ መሆኑን አውቃለሁ፤ ዜግነትን
በጎሰኛነት የሚተኩት እነማን እንደሆኑ ገብሩ አላወቀም ማለት ነው፤ ወይም አምስት
መቶ ዶላር ኪራይ የሚከፈልበት ጊዜያዊ ዜግነት ከሌለው በቀር ወደ ቀበሌ መታወቂ
ያ ለማውጣት ሲሄድ ያስረዱታል፤ እኔ ግን ዜግነትንና ጎሰኛነትን አላነካካቸውም፤ ዜ
ግነቴንም እንዲያው በዋዛ አላየውም፡፡
* ..የኤርትራና የትግራይ ዜጎች.. ያልኋቸው ኢትዮጵያውያን ካልሆኑና የዜግነት ግዴ
ታ ከሌለባቸው ኃላፊነቱን ከየት አምጥቼ ጫንሁባቸው?
* ገብሩስ የኢትዮጵያ ዜግነታቸውን ተገፈፉ ብሎ ወደቁጣና ወደመከፋት ያመራው
ዜግነታቸውን ከዜግነታቸው ግዴታ እንዴት ለይቶ ነው?
የዜግነት መብትና ግዴታ በእያንዳንዱ ግለሰብ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ነው፤ ዘርን ወ
ይም ጎሳን ከዜግነት ጋር ማገናኘት ግልጽ ስህተት ነው፤ በ1969 ሶማሊያ ኢትዮጵያን
በወረረበት ጊዜ አንድ የትግራይ ዜጋ በራሱ ፈቃድና ወጪ  አዲስ አበባ መጥቶ ለመ
ዝመት መወሰኑን በቴሌቪዥን አይተናል፤ የኢትዮጵያ ዜጋ ስላላልሁት በተግባር የገለ
ጠውን የዜግነት ግዴታ ይፍቀዋል የሚል የጎሳ ህመም የያዘው ብቻ ነው፡፡
እጅግ የሚያስደንቀውና ከገብሩ በጭራሽ የማልጠብቀው የቼኮዝላቫኪያውን ጸሐፊ
የሀበሻ ጀብዱ የሚለውን መጽሐፍ ገና ሳያነብበው መጥላቱ ነው፤ እኔ ሰውዬውን ጎበ
ዝ በማለቴም የተበሳጨ ይመስላል፡፡
..የትግሬ ሽፍቶች.. በሚለውም ጥቅስ ተበሳጭቷል፤ የእሱ መበሳጨት አንሶ ሌሎችን
ለመቆስቆስ ..በዚህ አባባልዎ ብዙዎች ዜጎችን ሳያስከፉ እንዳልቀሩ ሳልጠቅስ ለማለፍ
አልፈልግም.. ይላል፤ ብዙ ሰዎችን የሚያስከፋው አባባሌ ምን እንደሆነ የታሪክ ፕ/ሩ
አልተናገረም፤ የእኔን ጽሑፍ ያላነበበ ሰው አንድ መጥፎ ነገር የተናገርሁ ይመስለዋል፤
እኔ ያልሁት ስላልተጠቀሰ አንባቢው የራሱን ፍርድ ለመስጠት እንዳይችልና የገብሩን
ፍርድ ብቻ ተቀብሎ መስመር እንዲይዝ ይጋብዘዋል፤ ከገብሩ እኔ የምጠብቀው አን
ደኛ ምንም ያህል ቢያስከፋ እውነትን ለመቀበል ዝግጁ መሆንን ነበር፤ ሁለተኛ ፀሐ
ፊው የጠቀሳቸውን የትግሬ ሽፍቶች ለትግራይ ህዝብ በሙሉ ማልበስ አጉል ጎሰኛ አ
ስተሳሰብ ነው፤ ትዕግስትና ፍላጐት አድሮበት መጽሐፉን ቢያነብበው የራስ ስዩምም
ጦር ከራስ ካሣ ጦር ጋር ተሰልፎ ሲዋጋ እንደነበረ መረዳት ይችል ነበር፤ በህገ ኀልዮ
ት (ሎጂክ) ለጥቂቶች የተነገረውን ለጠቅላላው ማልበስ ልዩ ስም ያለው የአስተሳሰብ
ጉድለት ነው፤ ነገር ግን ፕ/ር ገብሩ በዚህ በህገ ኀልዮት ስህተቱ እኔን ለማቄል ..በሽፍ
ቶች አሳበው መላውን ትግሬ ለመፈረጅ ነው የሚል እሳቤ የለኝም ይላል፤.. እንኳን ይ
ቺንና የዝንብ ጠንጋራ እናውቃለን ሲባል አልሰማም መሰለኝ..
በፍትህ ጋዜጣ ከአቶ ስብሓት ነጋ ጋር የተጀመረው ክርክር በአንድ ጉዳይ ላይ ነበር፤
ከዚያ ክርክሩ እየወረደ የጎሳ ሽታ ይዞ መጣ፤ የኔ የመጨረሻ ጥረት ይህንን የጎሳ ሽታ ለ
ማስወጣት ነበር፤ ሐጎስ እርገጤ ሌባ ነው ሲል በላቸው የሚናደድ ከሆነ፣ እርገጤ ሐ
ጎስ ሌባ ነው ሲል ጥዑም የሚናደድ ከሆነ እንደሰዎች ለመነጋገር የምንችልበት ጊዜ አ
ልደረሰም ማለት ነው፤ በግላችንም ሆነ በህዝብነታችን የሚያዳክመን አጉል መሸፋፈ
ንና ድብብቆሽ ነው፤ እውነቱን ለማወቅና እውነቱን ለመናገር ድፍረቱን ከአገኘን ሳን
ጎዳዳ እንደልብ ለመነጋገር እንችላለን፤ ለጋዜጦቹም ሆነ ለአንባቢዎች አንድ ለመግባ
ቢያ የሚረዳን ሀሳብ ላቅርብ፤  INTERNET ውስጥ ገብተን LOGICAL FALLACY
ብለን ብንጠይቀው በምንነጋገርበትም ጊዜ ሆነ በምንጽፍበት ጊዜ ሊረዳን የሚችል
ትምህርት የምናገኝ ይመስለኛል፤ በገለባ እየለወጥን የምናውቀውንም የማናውቀው
ንም እያደባለቅን ብንነታረክ ዋጋ የለውም፤ ከዚያም በላይ እያንዳንዳችን ተምረናል፤
አውቀናል፤ ብለን በውስጣችን ያለውን መርዝ ከምንነዛው በውስጣችን ይዘነው እኛ
ኑ እንዳደረገ ያድርገን፡፡

# ህወሓት ኢህአዴግ የብዙሃን ፓርቲችን በኢትዮጵያ መኖር እያጨለመው ይገኛል

ከአቶ አስገደ ገብረስላሴ
(የህወሓት መስራች የነበሩ ከመቀሌ)

ህወሓት ኢህአዴግ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ በአስተሳሰብ የተለየው (የሚበልጠው
ፓርቲ ቡድን ፣ግለሰብ) በጠላትነት ፈርጆ የማጥቃት ሴራ አሁን የጀመረው ሳይሆን የ
ቆየ በሽታው ነው፡፡

ለዚሁ ማረጋገጫ በ17 አመቱ የትግል ጊዜ በወቅቱ ከነበሩ ፖለቲካ ድርጅቶች ይነሱ
የነበሩ ዴሞክራሲያዊ ጥያቄዎችን በሰላማዊ እና በዴሞክራሲያዊ ውይይት እንደመፍ
ታት ፈንታ መጥፎ ስም መለጠፍን እንደመልካም ልምድ ይዞት የመጣና ለኢትዮጵያ
ህዝብ እንደ ገፀ-በረከት ያቀረበው ነገር ነው፡፡

በትጥቅ ትግል ጊዜ ከፖለቲካ ፓርቲና ከደጋፊዎቻቸው ጋር የነበረው የግጭት አፈታ
ት በቅንነት ነገሮችን በዴሞክራሲ አግባብ በውይይት እንደመፍታት ለጊዜው ለማጥቃ
ት እስኪዘጋጅ ትእግስተኛና ሰላም ፈላጊ መስሎ እንዲታይ እና በህዝብ በታጋዮች መሀ
ከል ለጊዜው የፖለቲካ ቅስቀሳ ያደርጋል፡፡ የነበሩትን ፓርቲዎቹም ለዝግጅት ጊዜ ሽመ
ታ እንወያይና ልዩነታችንን እናጥብብና አብረን እንታገል ይል ነበር፡፡ እንዲህ እያለ ቆ
ይቶ አስፈላጊ ዝግጅት ካደረገ በኋላ ነፍጥን በመምዘዝ እርምጃ ይወስድባቸው ነበር፡፡
በዚህም ህይወት ያልፋል ፣ ንብረት ይወድማል ብዙ አካል ይጎድላል፡፡

የነዚህ ድርጅቶች ሲቪል ደጋፊዎች/ደጋፊ ያልሆኑ ግን ደግሞ በቅንነት ጥያቄ ያነሱ ም
ሁራኖች፣ ገበሬዎች ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ስም በመለጠፍ እንዲታሰሩ ከህብ
ረተሰብ እንዲገለሉ የተለያዩ ቅጣት የሚጣልባቸው ብዙ ነበሩ፡፡

በህወሓት ኢህአዴግ አባል ድርጅትም ከ1968ዓ.ም ጀምረው እስከ አሁን ጥያቄ ያነሱ
ታጋዮች የተለያዩ ስም በመለጠፍ ለሚያነሱት ጥያቄ የወላዋይ ሃይሎች የአነግ፣ የኢህአ
ፓ፣ የቅንጅት፣ የአንጃ፣ የኪራይ ሰብሳቢ፣ የነፍጠኛ፣ የጎዳና ነውጠኞች አስተሳሰብ ነ
ው እየተባለ ብዙ ጀግና ታጋዮች ተንገላቱ ተሰቃዩ፤ በየሄዱበት ተበታተኑ አንድ አንድ
ጊዜ በብዙ ሺዎች የሚታሰርበት፣ ከድርጅቱ የሚባረርበት ሁኔታዎች ነበሩ፡፡

ህወሓት ኢህአዴግ ከተለያዩ ድርጅቶችና ከግዙፉ የደርግ ሰራዊት ጋርም ተዋግቶ አሸ
ንፎ ወደዚህ እንደፈለጉ ወደ የሚያደርጉበት የሞቀ ወንበር ያወጣቸውና ያላዩትንም ሀ
ብት እንዲያካብቱ ሆኗል፡፡ ወንበሩን በውድድር ሊነጥቁት ለመጡ ተቃዋሚዎች እን
ዴት ብሎ ስልጣን ያስረክባል፡፡ አዲስ ባህሪስ እንዴት ያመጣል፡፡

የኋላ ጉዞው እንደጠቀስኩት ሆኖ ደርግ ከተወገደ በኋላስ? ደርግ ከተወገደ በኋላ ኢህ
አዴግ በበላይነት በሚመራው የሽግግር መንግስት ወቅት ብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተ
ፈለፈሉ፡፡ ከተፈለፈሉ ፓርቲዎች አብዛኞቹ በኢህአዴግ መልካም ፍቃደኝነት መሪዎ
ቻቸው እየተመለመሉና እየታሰሩ ተመረቱ፡፡ ጥቂት የማይባሉም ከኢህአደግ የተለየ አ
ስተሳሰብ ያላቸው ተመሰረቱ፡፡ በሌላ በኩል በህወሓት ኢህአዴግ ታጋዮች ብዙ ዴሞ
ክራሲያዊ ጥያቄዎች ተነሱ፡፡

ህወሓት ኢህአዴግ ራሱ ጠፍጥፎ ከሰራቸው አባል አጋር ድርጅቶች ከሚላቸው ፓር
ቲዎች ውጭ ለሆኑት ተቃዋሚዎች ለይስሙላ እንዲደራጁ ህገ-መንግስት ተረቀቀ፡፡
ኢህአዴግ ከፓርቲዎች ጋር በመቻቻል በህገ-መንግስቱ መሰረት በውይይትና በመግባ
ባት አብሮ እየሰራ እንደሆነና የብዙሃን ፓርቲ ተሳትፎ ባለበት ሀገር የሚመራ ዴሞክራ
ሲያዊ መንግስት ተብሎ በአለም ደረጃ በተለያዩ ብዙሃን መገናኛ ይናገር ነበር፡፡ ከ80
በላይ የግል ፕሬሶች ተፈቅዶላቸው የሠሩ ነበሩ፡፡ ኢህአዴግ ግን ባህሪው ስለማይፈቅ
ድለት ለፓርቲዎችም ለፕሬሶችም ምርጥ ምርጥ ስም በመለጠፍና ስጋት በመፍጠር በ
ጥቃቅን ክስ ምክንያት ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ፕሬሶችም እየከሰሙ ሄዱ፡፡

ኢህአዴግ ህዝብንና አለምን ለማደናገር ሃቀኛ ተወዳዳሪ ፖለቲካ ድርጅቶች ካሉ (የ
እድል ሆኖ የሉም እንጂ) ሩቅ ተጉዘን ልንቀበላቸው እንችላለን ብሎን ነበር፡፡ ይህ ግ
ን ሳይሆን ቀረ፡፡

በህወሓት ኢህአዴግ ታጋዮችና ህዝቡ የሚነሱ ፖለቲካዊ ጥያቄዎች በጅምላ መታሰር
ና ከስራ መባረር ያስከትሉ ነበር፡፡ እንደተለመደው የወላዋይ ኃይሎች የትምክህትና ጠ
ባብነት፣ የኢሰፓና የመሳፍንቶች አስተሳሰብ ጥገኞች እየተባሉ ይናናቃሉ፡፡

በወቅቱ ለነበሩ ተቃዋሚ ኃይሎችም ከጥርጣሬ ነፃ ሆነው ፍላጎታቸውን በውይይት
እንዲፈቱ እንደማድረግ ወደ ጦርነት በሚያመራ መልኩ መቅረቡ ሁኔታውን እያባባ
ሰው ሄደ፡፡

ተቃዋሚዎችም ሰከን ብለው እንደማየት ፈንታ በሚፈጠሩ ችግሮች ተገፋፍተው ወዳ
ልሆነ አቅጣጫ ይሄዱ ነበር፡፡ ለዚህ ሁሉ ግን ዴሞክራሲያዊ ነኝ የሚለው የኢህአዴ
ግ መንግስት ሀላፊነት ባለው ሁኔታዎች በትዕግስትና በመቻቻል መፍታት ነበረበት፡፡
ግን ደግሞ ታሪካዊ አመጣጡና ባህሪው አልፈቀደለትም፡፡ ኢህአዴግ አንድ ብሎ ስል
ጣን ከያዘበት ቀን ጀምሮ እስከ አሁን አገሪቱ በከተማም በገጠርም በተለያየ መልኩ እ
የታወከች ትገኛለች፡፡

የነዚህ ከስቶች ዋና ምክንያት በአገራችን መልካም አስተዳደር፣ ፍትህ፣ የህግ የበላይነት
ና ልማት አለመረጋገጥ፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አለመኖር ናቸው፡፡ ህወሓ
ት ኢህአዴግ የተጠቀሱትን ችግሮች አስወግዶ አገራችን እና ዜጎቿ ተስማምተው ብሎ
ም ተቻችለው የሃሳብ ልዩነታቸው በህዝብ ዳኝነት እንዲዳኙ ከማድረግ ይልቅ ይህ
ች አገር ከኔ አስተሳሰብ ውጭ ማንም ሊመራት አይችልም በሚል አፍኖ በመያዙ እነሆ
አገራችን ለ20 አመታት በህወሓት ኢህአዴግ ፈላጭ ቆራጭነት እየተመራች ትገኛለች፡፡

## ህወሓት ኢህአዴግ ካለፉት ስርዓቶች በምን ይለያል?

የአፄው ስርዓት የኢትዮጵያን ህዝብ ለጃንሆይንና ንጉሳዊ ቤተሰቦችን እንዲያመልክ፣ ታ
ማኝ ሆኖ እንዲገለግል፣የሃይማኖት መሪዎችም ለስብከት እንደመሳሪያነት በመጠቀም
በየክፍለ ሀገሩ ጋብቻ በመስፋፋት መዋቅራቸውን በመዘርጋርት፣ ራሳቸው ጃንሆይም
ለኢትዮጵያና ህዝቦቿ ከአንገታቸው በታች ቀዝቃዛ ውሃ በተሞላ በርሜል ተነክረው ፀ
ሎት እያደረጉ ስለህዝብ እየተሰቃዩ እንደሚኖሩ ይሰብኩ ነበር፤ ህዝቡም ካለማወቅ ሃ
ቅ መስሎት ያዝንላቸውና ከእግዚአብሔር በላይ ያመልካቸው ነበር፡፡

ውሸት ቀስበቀስ ይጋለጣል እንደሚባለው የጃንሆይ ስርዓት ጨቋኝና የተጨማለቀ መ
ሆኑ ተጋልጦ ወደቀ፡፡

የአፄው ስርዓት ባለስልጣናት ግን ድሃው ህዝብን እየበዘበዙ ልጆቻቸውንና ዘራቸው
ን ያስተምራሉ፤ ገንዘብ እየዛቁ በውጭ ባንኮችም ያስቀምጡ ነበር፡፡ በወቅቱ የህዝብ ሰ
ብል በተባይ ሲበላና በድርቅ ሲጠቃ ምንም የሚሰማቸው አልነበረም፡፡ በአገራችን መ
ልካም አስተዳደርና ፍትህ፣ ነፃነት፣ የህግ የበላይነት አልነበረም፡፡ የሰብዓዊና ዴሞክራ
ሲያዊ መብቶች ከቶም ለሽታም አልነበረም፡፡ የህዝብ ብሶት ከገነፈለ አይመለስምና በ
ህዝብ ትግል ተፈነገሉ፡፡

የደርግ ስርዓት የህዝብን ትግል በመጠቀም ወንበሩን ልቅመሰው በማለት የህዝብን ዴ
ሞክራሲያዊ መፈክሮች በመታጠቅ ..ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም.. በሚል መፈ
ክር ጆሮቻችን አደነቆረን፡፡ ቆየት ብሎ ወታደሩ 60ዎቹ ሚኒስትሮችና መኳንንቶችን በ
መረሸን በደም ጎርፍ ታጠበ፤ ሁሉንም ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ዘጋው፡፡ ቤቶችና ንብረቶ
ች ወረሰ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ በደርግ ጥርስ ውስጥ ገባ፡፡

በወቅቱ ወደፊት የመነጠቁ ምሁራኖች ደርግን ታግሎ ለመጣል ተደራጁና ወደ ትጥቅ
ዘመቱ፤ ህዝቡን በየአለበት በማንቃትና፣ አደራጅቶ በማስታጠቅ ከደርግ ጋር መፋለም
ጀመሩ፡፡ በዛን ጊዜ የነበሩ ፖለቲካ ፓርቲዎች ልዩነታቸውን በማቻቻል አንደነት ፈጥረ
ው ለደርግ ሞት እንደመቀላጠፍ ፈንታ፤ እርስ በእርሳቸው እየተጣረሱ ብዙዎች ፓር
ቲዎች ከሰሙ፡፡ ሆኖም ግን ያን የሚገፋ የማይመስል የደርግ ሃይል በህዝብ አቅም ተደ
ምስሶ ድምጥማጡን ጠፋ፡፡

የደርግ መውደቂያው ምክንያትም እንደ ጌቶቹ ጃንሆይ ሁሉንም ዓይነት ዴሞክራሲያ
ዊ ሰብዓዊ መብቶች ባለማስጠበቅ፣ መልካም አስተዳደርና፣ ፍትህ፣ ነፃነት፣ የህግ የበላ
ይነት፣ ልማት ባለመረጋገጡ ተፍረክርኮ ወደቀ፡፡ አወዳደቁ ግን ዝም ብሎ አይደለም፡
፡ እጅግ ብዙ ምሁራን ወጣቶች፣ ተማሪዎች፣ ገበሬዎች፣ ነጋዴዎች ረሽኗል፣ አስሯል፣
ገርፏል፣ አሰቃይቷል ብዙ ወጣት በማስገደድ ወደ ጦርነት ማግዷል የአገራችንን ሀብ
ት አውድሟል፡፡

ደርግ ስልጣን እንደያዘ የነበሩትን የህዝብ ጥያቄዎች መልስ ቢሰጥ ኖሮ፤ በህዝብ መፈ
ክሮችና አላማዎች አምኖ ቢጓዝ ኖሮ ያ ሁሉ ህይወት፣ ንብረትና ሀብት አይጠፋም ነበ
ር፡፡ በደርግና በተጋጣሚዎቹ ድርጅቶች መካከል የጠፋው ህይወት አይጠፋም ነበር፡
፡ ደርግ ብዙ ጦር፣ ፖሊስ፣ ደህንነት ፣ዘመናዊ መሳሪያና የውጭ የጦር አማካሪዎች ይ
ዞ ተንኮታኮተ፡፡ ህዝባዊ ሃይል ከተነሳ የሚያግተው ሃይል የለምና፡፡ ይህን ህወሓት ኢ
ህአዴግም ያውቃል፡፡

## ህወሓት ኢህአዴግስ

ህወሓት ኢህአዴግ በ11 ታጋዮች 5 ኋላቀር ነፍጠና አንድ ሽጉጥ ይዞ ትግል ጀምሮ 1ኛ፣
2ኛ፣ 3ኛ፣ 4ኛ የደፈጣ ውግያ ደረጃዎችን በመጠቀም ደርግን አሸንፌ ዴሞክራሲያዊ
ስርዓት እመሰርታለሁ ብሎ ወደ ትጥቅ ትግል ሲዘምት አሁን ወደ ኋላ ተመልሰን ስናየ
ው የሚቻል አይመስልም፡፡ ግን ደግሞ ተችሏል፡፡

ህወሓት 11 ደፈጣ ተዋጊ 5 ነፍጥ ይዞ ትግል ሲጀምር ደርግ 60000 በአሜሪካ፣ በእስራ
ኤል፣ በጀርመኖች የሰለጠነ ጦር ሰራዊት እና ፖሊስ ሃይል ነበረው፡፡ ኋላ ህወሓት በአ
ስር ሺዎች ሲደርስ ደርግ ሁሉም ታጣቂዎች ተደምሮ በሚልዮን የሚቆጠር ሰራዊት ነበ
ረው፡፡ እንደ አሁኑ የኢህአዴግ ደህንነት ብዛት ባይኖረውም በኬጂቢ ስለላ የሰለጠነ እ
ጅግ ብዙ ደህንነቶች ነበሩት፡፡ ህወሓት ኢህአዴግ ግን ለትግራይ ህዝብ ከ12 አመት በላ
ይ ኋላም ሰሜን ጎንደር፣ ሰሜን ወሎ፣ በከፊል ሰሜን ሸዋ በማንቃት በማደራጀት በማስ
ታጠቅ በመቶ ሺ የሚቆጠር ተዋጊ ሰራዊት በመፍጠር መልካም አስተዳደር ፍትህ፣ ነፃ
ነት፣ የህግ የበላይነትን እናረጋግጣለን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እናስጠብቃለ
ን ወዘተ... በማለት ከህዝብ ጋር በመተባበር ደርግን አሽቀንጥሮ ጣለው፡፡ ህወሓት ኢህ

አዴግ ደርግን አስወግዶ ስልጣን ከያዘ በኋላ ልክ ደርግ አዲስ መፈክር ይዞ ወደ መድረክ ብቅ እንዳለ ሁሉ  አንድ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ሊሰራቸው የሚችለውን ሁሉ እሰራለሁ አለ፡፡ የተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ያቀፈ የሽግግር መንግስትም አቋቋመ፡፡ ቆየት ብሎ የአገራችን ህገ-መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን አቋቁሞ ረቂቁ ህዝብ እንዲወያይበትም ቀርቦ ነበር፡፡ ይህ ተግባር ከዛ በፊት ያልነበረ ስለሆነ መልካም ነው ሊባል ይችላል፡፡

የህወሓት ሴራ በሽግግር ወቅት

1. በሽግግሩ የነበሩ ፓርቲዎች በተለያየ መንገድ ከሽግግሩ መንግስት እንዲወጡ ማድረግ በመጨረሻም ወደ ጦርነት እንዲያመሩ ማድረግ

2. በሁሉም ክልሎች ግለሰቦች በመመልመል በህወሓት ኢህአዴግ ሳምባ የሚተነፍሱ አጋር ፓርቲዎች በተለያየ መንገድ እንዲደራጁ ማድረግ፣ ነባር ፓርቲዎች እና ሚዲያን በማፈን ራሱ ለመለመላቸው ወጣት ፓርቲዎች ከፍተኛ የሚዲያ ሽፋን በመስጠት የፀጥታ ድጋፍም ይሰጣቸው ነበር፡፡

ለአዲስ ፓርቲዎች በደቡብ ህዝቦች፣ አሮሞ፣ ጋምቤላ፣ ሀረሪ፣ ሱማሌ፣ አፋር፣ በአማራም በህወሐት ማዕከላዊ ኮማቴ የሚመሩ ካድሬዎችና የደህንነት ሰዎች በመመደብ ድርጅቶቹ የህወሓት አስተሳሰብን እንዲጨብጡ በማድረግ አደረጃጀቱን በማጠናከር ተንቀሳቀሰ፡፡ ይህን የሚያደርገው  ህገ-መንግስት ከማፅደቁ በፊት ነው፡፡ ሁሉም የህወሓት ኢህአዴግ አጋር ድርጅቶች ሲመሰረቱ የገንዘብና የትራንስፖርት  ችግር አልነበራቸውም፡፡

ህገ-መንግስቱ ከፀደቀ በኋላ የተደረገው ምርጫ ትክክለኛ ተቃዋሚዎች ወደ ፓርላማ በብዛት እንዳይገቡ የፓርላማ ምልአተ ጉባኤውን ህወሓት ኢህአዴግ እንዲያዝ ተደርጎ ፓርላማው በርከት ያሉ ተቃዋሚዎች እንኳን ቢኖሩት ምልአተ ጉባኤው የኢህአዴግና አጋር ድርጅቶች ስለሞሉት ሁሉም ውሳኔዎች ህወሓት ኢህአዴግ በሚፈልገው ይፀድቃሉ፡፡ ልጥፍ ያልሆኑ ፓርቲዎች ሀሳብ ቢያቀርቡ እንኳ መድረኩ  የስድብና የአሽሙር ንግግሮች መንሸራሸርያ ይሆን ነበር፤ ሁለተኛውና ሶስተኛው የፓርላማ ጊዜም ያው እንደ አንደኛው ፓርላማ ነበር፡፡

ህወሓት ኢህአዴግ በ97ዓ.ም ተሞክሮ ምርጫ   የ2002 የፓርላማ ውጤት  99.6ኀ እንዲሆን አደረገ፡፡ የክልል ም/ቤቶችም የባሱ ናቸው፡፡ ባለፉት 3 የፓርላማ ጊዜያትና የአሁን የ4ተኛ ፓርላማ ጊዜ ብዙ አዋጆች ታውጀዋል፡፡ እነኚህ አዋጆች ሲታወጁ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ተቃውሞ 1 ድምፅ ተአቅቦ ካልሆነ በስተቀር የህወሓት ኢህአዴግ አባላት  ባለፈው የፓርላማ ጊዜያት አዋጆች ሲፀድቁ ሁሉም አይነት አገሪቱ የምታደርጋቸውን ስምምነትቶች ሲፀድቁ አዎን እንጂ አይሆንም የሚል ድምጽ ከህወሓት ኢህአዴግ መንደር ታይቶም ተሰምቶም አያውቅም፡፡

አዋጆቹ የሚያወጣቸው ድንገትና ሳይታሰብበት ነው ለአብነት ፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ ፀረ-አሸባሪነት፣ የምርጫ ስነ-ምግባር ወዘተ ለኢትዮጵያ ህዝብም ለአለምም አግራሞት የፈጠሩ ናቸው፡፡

ህወሓት ኢህአዴግ የአፄውና የደርግ ስርዓት በምን እንደወደቁ እያወቀ ከነሱ  እንደ መማር እነሱ ሲፈፅሙት የነበሩትን ስህተት እየደገመ ይገኛል፡፡ ለዚሁ ማረጋገጫ ህወሓት ከመጀመርያ ሲነሳ  መነሻው የህዝብ ብሶትን ለመፍታት ነበር፡፡ የወደቁ ገዥዎቻም ብሶት በፈጠረው የህዝብ ማዕበል መሆኑ ይረዳል፡፡ በደረጃም በጠባብነት አስተሳሰብ የአንድ ብሄር ንጉስ መሆን የማያዋጣው መሆኑን አወቀ፡፡ ትግሉ ሃገራዊ ይዘት እንዲኖረው አድርጓል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ህዝብ ብሶት ለመፍታት እታገላለሁ ብሎ የኢትዮጵያን ህዝብ ከጫፍ እስከ ጫፍ አንቀሳቅሶ ድል አግኝቶ ከላይ ለጠቀስኩት ደረጃ ደርሶ ነበር፡፡

በአሁኑ ጊዜ ግን ህወሓት ኢህአዴግ ወደ ወደቁት፣ የሾቁ መንግስታት ወደ ኋላ በመመለስ፤ ያ ሁሉ ህይወት ያለፈበት፣ ደም የፈሰሰበት አላማ እየተረሳ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ብዙሃን ፓርቲዎች ነፃ ሆነው የሚወዳደሩበት፣ ሁሉም አይነት ሰብአዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩባት፣ መልካም አስተዳደር፣ ፍትህ የህግ የበላይነት ነፃነትና ልማት የሚረጋገጥባት ሀገር ፣ ሰዎች ነፃ ሀሳብ የሚገልፁበት፣ ነፃ ብዙሃን መገናኛ ክፍት እንዲሆኑ ግልጽነትና ተጠያቂነት ሙስናና ወገናዊነት እንዲጠፋ የታገለ ፓርቲ ተመልሶ የታገለለትን አላማዎች ወደ ጎን በመተው  የዘመኑ አምባገነን በመሆን ህዝቡን ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዲሄድ እያደረገ ነው፡፡

ሌላ የኢህአዴግ ትልቁ ስህተት ህወሓት በ11 ሰውና 5ኋላ ቀር ነፍጦች ታጥቆ ሃሳቡን ለህዝብ ቢያሰረፅም ይሄ ጀግንነት ብቻ ግን ትርጉም የለውም፡፡ የግብፁ ሆስኒ ሙባረክ፣ የሊቢያው ጋዳፊም በህዝብ ተወዳጆች እንደሆኑ ይመስላቸው ነበር፡፡ ሆስኒ ሙባረክም 5 ጊዜ በህዝብ ተመርጦ ነበር ይባላል፡፡ ህዝብ ስለማያምንበት ግን በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ጦር ሰራዊት ልዩ ኮማንዶዎች ሰላዮች የታጀበው፤ ሁስኒ ሙባረክ በአስር በሚቆጠሩ ቀናት ፈረሰ፡፡ ገዥዎችና አምባገነኖች ተጋለጡ፡፡ ለሌሎች አገርም አስተማሪ ነው፡፡ ለውጊያ ህዝብ በማሰለፍም ሂትለርና ሞሶሎኒም ዝነኞች ነበሩ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ምንም ቂም የሌላቸው ሚስተር ማንዴላ ጥሩ አባት አሉን፤ አፍሪካዊ የፍትህና ነፃነት መልካም አስተዳደርና የህግ የበላይነት የፕሬስ ነፃነት ተምሳሌት፣ ቂም የማይዙ ሰው በላውን አፓርታይድ የታረቁ ናቸው፡፡ ህወሓት ኢህአዴግ ቢማር በትስ?

የአሸባሪዎች፣የደፈጣ ውግያ ፈጣሪዎች
መንግስታት ናቸው

በአንዲት አገር ፍትህ፣ ነፃነት መልካም አስተዳደር፣ የህግ የበላይነት ከሌለ ዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶች ካልተከበሩ ልማት ካልተረጋገጠ፣ ረሃብ፣ ስደት፣ በሽታና እርዛት ካለ ህዝቦች ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ለመቃወም ይሁን ለመደገፍ ካልቻሉ፣ መሪዎቻቸውን ከስልጣን የማውረድና ወደ ስልጣን በምርጫ ማስወጣት መብታቸው ካልተጠበቀላቸው ሰው በመሆናቸው ሊያገኙት የሚገባቸው እንደ መጠለያ (የሚለበስ፣ የሚጠጣ ውሃና ህክምና) የማግኘት መብታቸው ከተነጠቁ፡፡ በአገራቸው ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮች አስተያየት ሊሰጡና ሊሳተፉ ካልቻሉ፤ መሪዎች ለሚፈፅሙት ብልሹ አሰራርና ያለአግባብ ብልጽግናን ሊቆጣጠሩ ካልቻሉ እና ሁሉንም አይነት መብቶቻቸውን ከተከለከሉ በአምባገነኖችና ገዥዎች ማመፃቸው ላይ አይቀርም፡፡

ለዚህም ጥሩ አብነት የህወሓት የትጥቅ ትግል  ነው፡፡ ይህም ታጋዮች በሰኮንዶች  ጊዜ ውስጥ መስዋእት ለመክፈል ፈንጅ በመርገጥ፤ ሞተው ጓዶቻቸው እንዲያልፉ ያደርጉ ነበር፡፡ በረድፍ የተደረደሩ ታንኮችን እና መድፎችን ቦምብ በሻንጣ በመያዝ ገብተው አቃጥለው የሚቃጠሉ ነበሩ ረሃብ፣ ውሃ ጥም ድካም፣ ያለ በቂ ልብስ መኖር ለረጅም አመታት በጨለማ መኖር እና ከቤተሰቦቻቸው ተነጥለው ነው የታገሉት፡፡

ህወሓት ኢህአዴግ የአሸባሪዎችና የደፈጣ ውግያ ምንጭ ገዥዎች መሆናቸውን በሚገባ ተንትኖ ያውቃል፤ ታድያ ሁሉምን ነገር እያወቀ ህብረተሰቡን ወደ ሌሎች አማራጮች እንዲሄዱ ለምን ያደርጋል? መልሱን ለህወሓት/ ኢህአዴግ ትቼአለው፡፡

በየመን፣ በሶርያ፣ በሊብያ እየተካሄደ ያለው የህዝብ አመፅና የሰው ህይወት እልቂት ምን ይሁን ምንም ሽብር ፈጣሪዎቹ  የሃገሮች መሪዎች ናቸው፡፡ ህወሓት ኢህአዴግ ከነዚህ ይማር፡፡

በመጨረሻም ማጠቃለያ የዚህ ፅሁፍ ርእስ የብዙሃን ፓርቲን በኢትዮጵያ መኖር ኢህአዴግ እያጨለመው ነው ያልኩበት ምክንያት፤ በአሁኑ ጊዜ ህወሓት ኢህአዴግ፤ ጠንከረው ይወዳደሩኛል የሚላቸውን እንደ መድረክ የመሳሰሉ ፓርቲዎችን ሽብርተኛ ሚል ሽፋን ማሰር፤ ማንገላታት የስራ እድልና የትምህርት እድል መከልከል ፤ በአገሪቱ የድህነት ሰዎች ክትትልና ጭንቀት መፍጠር፤ እያደርግ ስላለ ይህን ጉዳይ አይቶና አስቦበት ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በዲሞክራሲያዊ መንገድ ማስተናገድ አለበት እነሡ ግን በተቃራኒው ህገ መንግስት አክብረው በሰላማዊ ትግልና የምርጫ ውድድር አምነው ለሚታገሉ ሁኔታዎችን  እንደመመቻቸትና ተቻችሎ እንደመታገል የ99.6ኀ የፓርላማ ወንበር ያለው የህወሓት ኢህአዴግ አፋኝ ህጎች እና አዋጆችን በማፅደቅ አሸባሪዎች እና አገር አሳልፈው የሰጡ ናቸው እያለ ለሰላማዊ ትግል የቆሙ የፓርቲ መሪዎችን ማሰር ማንገላታት ነፃ ሆነው ብቅ ያሉ ጋዜጠኞችን ማሰርና ማዋከቡም ትልቅ ስህተት ነው፡፡ ይህ አሰራር ከቀጠለ ለህወሓት ኢህአዴግ እንዲሁም ለተቃዋሚ ፓርቲዎች፤ ትልቁ ነገር ደሞ ለህዝቡ አይጠቅምም፡፡በአሁኑ ጊዜ ፍትህ፣ ነፃነት፣ ልማት ወዘተ ባለመረጋገጡ አገር አቋርጦ ወደ ስደት የሚሄደው እና በስደት አገር ፍዳውን የሚያይ ወጣት ብዙ ነው፡፡ ስራ አጥነትን ተስፋፍቶ ሰው ፆሙን የሚያድርበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡

ሌላው ቀርቶ የትግራይ፣ የጎንደር ወጣቶች ለ17 ዓመት ወላጆቻቸው የተሰዉ፣ አካላቸው የጎደለ፣ ወንድማቸውን እና እህታቸውን በሻዕብያ ተገሎባቸውም፡ ወደ ሚጠሉት ሻዕብያ  እየተጠጉ ተቃዋሚ ነን እያሉ  አገራቸውን የሚያደሙት ያሉት፤ ስራ አጥ ወጣት ገበሬዎችና ተማሪዎች ፍትህና ነፃነት ልማት ስለሌለ የህግ የበላይነት ስለተጣሰ ነው በሚል ነው፡፡

ኢህአዴግ ሰላማዊ ትግል የሚያካሄዱ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እና  ነፃ ፕሬስን ከመወንጀል ይልቅ ለሁሉም ሃይሎች ሰለማዊ ጥሪ አድርጎ ግልጽና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ቢፈታው ይሻላል፡፡ ምክንያቱም ህወሓት ኢህአዴግ እንኳን በፓርቲ የተደራጁ ቀርቶ  ግለሰብዎችም ቢሆኑ  ጥሩ አላማ ይኖራቸው አይኑራቸው የሚያሰልፉት ሃይል ሊኖር እንደሚችል አንጥሮ ያውቃል፡፡ ህወሓት፣ ኢዲዩ፣ ኢህአፓ፣ ኦነግ፣አኝዋክ፣ ጉምዝ ሌሎችም የሱማልያ ድርጅቶች ያሰለፉት ሃይል ደርግን አዳክሟል፡፡ ግን የተለያዩ አላማና መፈክር ነበራቸው፡፡ ከነዚህ ፓርቲዎች ጋር ደርግ ተፈጥሮው አይፈቅድለትም  እንጂ በሚገባ ቢደራደራቸው ኖሮ ያሁሉ እልቂት ባላጋጠመው ነበር፡፡ ደርግም በስልጣን በኖረ፡፡ ህወሓት ኢህአዴግ በአፋኝ ህጎች ሰዎችን ከሚየስርና ከሚያዋክብ ለሁሉም ነገር ፖለቲካዊ መፍትሄ ቢቸር ለራሱም ለህዝብም መልካም ነው፡፡

ደርግ 150000 በላይ ሰላዮች በሚልዮን የሚቆጠሩ ታጣቂዎች ነበሩት፡፡ የራሽያ፣ ቻይና፣ ሊቢያ፣ ቡልጋሪያ፣ ኩባ፣ ሰሜን ኮርያ የማያቋርጥ የትጥቅ አና ስንቅ ሙያተኞች ድጋፍ ነበረው፡፡ ግን ህወሓት ኢህአዴግ አሸንፎታል ኢህአዴግ ከተማረ ከዚህ ይማር፡፡ የተከበራችሁ አንባብያን እስከ አሁን የገለፅኩት የህወሓት ኢህአዴግ የአመጣጥ ባህሪን ለመውንጀል አይደለም፡፡ እኔ ከመጀመሪያው እስከ 1985ዓ.ም አብሬው ታግያለው፡፡ ህወሓት ኢህአዴግ ኮሚኒስት (ካፒታሊም) የሆነ አይዶሎጂ እምነት ይኑረው ህዝብን አስተባብሮ እንደ አንድ እስትንፋስ አንቀሳቅሶ መርቶ ደርግን በመደምሰሱ ያሳየው ጀግንነት ተወዳዳሪ አልነበረውም፤ በዚህ ጀግናም ነው፡፡

# ርእሰ አንቀጽ

አዎን! ባንዲራችንን እናክብር፣ ባንዲራው የሚወክለውን ሕዝብ ደግሞ የበለጠ እናክብር!

ከአለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ መንግስት ብሔራዊ የባንዲራ ቀን መሰየሙና ማክበር መጀመሩ ይታወሳል፡፡ እጅግ ቢዘገይም እንኳ ለብሔራዊ ባንዲራችን ይሄን መሰል ክብር መስጠቱን ተገቢ ነው እንላለን፤ እርምጃውንም እናከብራለን፡፡

ነገር ግን በእዚህ መልካም መንፈስ ለባንዲራችን መሰረት የሆነው፣ የባንዲራው ማማ የሆነው ምድር ጥቁር አፈር ያፈራቸው ኢትዮጵያዊያን ዜጎቻችን ሰብዓዊ መብታቸውን፣ መሰረታዊ ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን እና ህገ-መንግስቱ የተከበረላቸውን የዜጎች መብቶች ሳይሸራረፍ ማክበር ሲቻል ብቻ የባንዲራ ቀን ውጤታማ ይሆናል ብላ ፍትሕ ታምናለች፡፡

ከ2003ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ በተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ ከሁለት መቶ በላይ ወጣቶች፣ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች፣ የፖለቲካ አባላት ..በአሸባሪነት.. ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ውለው ይገኛሉ፡፡ ሰሞኑን ደግሞ ይሄው ሁኔታ በስፋት ቀጥሎ ጋዜጠኞች ፣ የፖለቲካ ፓርቲ የአመራር አባላት እንዲሁ ..በሽብርተኝነት.. ተጠርጥረዋል ተብሎ ከየቢሮዎቻቸው፣ ከዩኒቨርስቲ ተቋማት እና ከመንገድ ላይ እየተለቀሙ በቁጥጥር ስር እየዋሉ ይገኛሉ፡፡ ሁኔታው በዚሁ የሚያባራም አይመስልም፡፡

በዚህ የተነሳም ላለፉት ሃያ ዓመታት ሲነሳ-ሲወድቅ የከረመው የግሉ ዘርፍ መገናኛ ብዙሃን ላይ የሚሰሩ ጋዜጠኞች ፣ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች የአመራር አባላትና ነፃ አሳቢ ዜጐች በሰሞነኛው የፀረ ሽብር ዘመቻ አፈፃፀም ሂደት ተሸብረዋል፣ ተደናግጠዋል፡፡

የሰዎቹ ክስ (የወንጀል ድርጊት ጥርጣሬ) እውነተኝነት በፍርድ ቤት ገና ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የመንግስት የሕግ አስፈፃሚ ተቋም የሆነው የፌደራል ፖሊስ እና የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በተከታታይ እየሰጡት ያለው ጋዜጣዊ መግለጫ መንፈስ ..ከፈረሱ ጋሪው.. ሆኖ ህብረተሰቡንም በፍርሃት እያሸበሩት በመሆኑ ሊታሰብበት ይገባል ስትል ፍትሕ ትጠይቃለች፡፡

በገዛ መንግስቱ የህግ አፈፃፀም የተሸበረ ህዝብ በአግባቡ ሊሰራ፣ ሊያሰራ፣ ሊማር፣ ሊያስተምር፣ አዳዲስ ነገሮችን ሊፈጥርና ለውጥ ሊያመጣ ስለማይችል መንግስት የሚያከናውናቸው ተግባሮች በትዕግስት፣ በእርጋታ እና በተጨባጭ እውነታ ላይ ተመርኩዞ ማስረጃ ካሰባሰበ በኋላ ብቻ ሕግን ቢያስከብር እርሱም የበለጠ ይከበራል እንላለን፡፡

የፌደራል ፖሊስ የፀረ-ሽብር ግብረ ኃይል ..በሽብር እንቅስቃሴ.. ጠርጥሬያችዋለሁ ያላቸው ዜጐች በቁጥጥር ስር ከአዋላቸው በኋላ በየጊዜው 28 ቀን የጊዜ ቀጠሮ እየጠየቀ ማስረጃና መረጃ በማፈላለግ መሞከሩ መንግስትን ትዝብት ላይ ይጥለዋል፤ ምክንያቱም ከተጨባጭ ውሃ ከሚያነሳ መረጃና ማስረጃ በፊት የመንግስት ፍርድ ቀድሟልና ነው፡፡ ስለዚህ በመጪው መስከረም 15ቀን 2004ዓ.ም የባንዲራን ቀን ስናከብር የሀገሪቱ ዜጐች ለሀገሪቱ ባንዲራ ያላቸው ፍቅር እና ታማኝነት ህገ-መንግስታዊ መብቶቻቸው ሳይሸራረፉ ከመከበራቸው የተነሳ እንደሆነ እንዲታወስ ፍትሕ ትጠይቃለች፡፡

ባንዲራችን ከነልዩነቶቻችን እና ተመሳስሎአችን ጋር ሆነን እንድናከብራት ግድ እንደሚለን ሁሉ በህገ-መንግስቱ የተዘረዘሩት የዜጎች መብቶችም በየትኛውም ወንጀል ተከሰው በእስር ላይ ላሉ ዜጎቻችን እኩል እንዲተገበር ፍትህ ትጠይቃለች፡፡

# እስክንድር ነጋን ሳስበው ሳስበው...

ተመስገን ደሳለኝ

ኢህአዴግ እና መለስ 20 ዓመት ያህል በስልጣን ቆይተዋል፡፡ ይሄ የሆ
ነው ግን እነሱ እንደሚሉት ምርጫ አሸንፈው ሳይሆን ..አሸናፊ.. ስለሆ
ኑ ብቻ ነው፡፡ ለነገሩ እኮ ደርግንም አሸንፈዋል፡፡ እስቲ አስበው.. ደር
ግ ከአየር ኃይል እስከ ባህር ሃይል፤ ከሚሊሻ እስከ ምድር ጦር ጠንካራ
እና ፈጣን ..መች.. ሀይል አሰማርቶ ሲያበቃ፤ እንዲህ ብሎ ፎከረ ..ሰሜ
ኑ የወንበዴዎች መቀበሪያ እንጂ መደበቂያ አይሆንም፡፡.. የሆነው ግን
የተገላቢጦሹ ነው፡፡ ..ወንበዴ.. ለተባሉት ሰሜኑ መቀበሪያ ሳይሆን መ
ደበቂያ፤ ከዛም መንደርደሪያ ሆናቸው፡፡ ቀጥሎም ደርግን መቅበሪያ በ
ማድረጋቸው፤ የተቆጣ እና የተገፋ ህዝብ እንደማይሸነፍ ምስክር ሆኖ
አልፎአል፡፡ ደርግ የደበረውን በሙሉ (በተለይም የትግራይ እና የኤር
ትራ ተወላጆችን) የወንበዴ አባል፣ ደጋፊ... እያለ በመግደሉ፣ በማሰሩ፣
በመግረፉ፣በማሳደዱ... ለ..ወንበዴዎቹ.. የማይነጥፍ የሰው ኃይል ምን
ጭ ሆናቸው፡፡ ሁሉም ሲገፋ፣ ሲገፋ፣ ሲገፋ... ማን ነበረ

..ምንም የማያውቀውን ገራገሩን በሬ፣

ነካክተው ነካክተው አደረጉት አውሬ..

ያለው? ብቻ ማንም ይበለው ዋናው መባሉ ነው፡፡ ይሄ እውነት ነው፡
፡ ምስክሩም ህወሓት እና ሻዕቢያ ናቸው፡፡ ደርጉ የወንበዴ ደጋፊ ከሚ
ላቸው ባሻገር ፀረ አብዮተኛ፣ አናርኪስት፣ ኢምፔሪያሊስት፣ምናምን
ሊስት... እያለ የገፋው ህዝብ በቀጥታ ነፍጥ በማንሳት ከጎናቸው ተሰ
ልፎአል፡፡

ይሄ ሁሉ ሆኖ ኢህአዴግ እና መለስ ስልጣን ከያዙ በኋላ ተቀናቃኞቻ
ቸውን ደርግ ይገፋ በነበረበት መንገድ ላለመግፋት በጣም ይጠነቀቁ ነ
በር፡፡ ስልታቸው ምንድን ነበር? ጠንካራ ተቃዋሚዎችን በተለያየ መን
ገድ ማዳከም፤ ከዛም የደከሙ ፓርቲዎች የሚወዳደሩበትን ምርጫ ደ
ግሞ ማጭበርበር፤ ይሄ እንግዲህ ለ20 አመት የቆየ ፍቱን ዘዴ ነው፡፡

ከ20 አመት በኋላስ? ከ20 አመት በኋላማ ብዙ ነገር ተቀይሮአል፡፡ ለም
ሳሌ አሰላለፉ ..ኢህአዴግ እና መለስ.. የነበረው፤ አሁን ..መለስ እና ኢህ
አዴግ.. ሆኖአል፡፡ መለስ ከፊት፣ ኢህአዴግ ከኋላ፡፡ እኔን ካላመንክ በ
ቀላሉ የህወሓት ፖሊት ቢሮ አባላት እነማን እንደሆኑ እይ፡፡ እዚያ ው
ስጥ ቢያንስ በህወሓት ውስጥ ተሰሚነት የነበራቸው አመራሮች ዛሬ የ
ሉም፡፡ አቶ መለስ ዜናዊ አሉ፡፡ ባለቤታቸው ቀዳማይ እመቤት አዜብ
መስፍንም አሉበት፡፡ በተቀረ ለጥንዶቹ የሚታዘዝ ካልሆነ  በቀር ወደ
ፖሊት ቢሮ ድርሽ እንዲል የተደረገ የለም፡፡ አባይ ፀሐይ፣ ስብሃት ነጋ፣
አርከበ እቁባይ፣ ስዩም መስፍን፣ ብርሃነ ክርስቶስ... ቢያንስ የሉም፡፡ እ
ነዚህ ሰዎች አንገፋ ታጋዮች ከመሆናቸው አኳይ ለቀዳማዊት እመቤት
ሊታዘዙ አይችሉም፡፡በእርግጥ መለስን ስለዚህ ጉዳይ ብትጠይቃቸው
..መተካካቱ የማይዋጥልህ.. ሲሉህ ሊያጣጥሉህ ይችላሉ፡፡ በመሬት ያ
ለው ግን ይሄ ሳይሆን መለስ እና አዜብ ብቻ ናቸው፡፡

የሆነ ሆኖ ከ20 አመት በኋላ መለስ እና አህአዴግ ተቀናቃኞቻቸውን የ
ሚያስወግዱበት አዲስ መላ ፈጥረዋል፡፡ ..አሸባሪ.. የሚል የዳቦ ስም ያ
ለው፡፡ ለምሳሌ ይህንን ፅሁፍ  ፅፌ ሳልጨርስ ..አሸባሪ.. ተብዬ በፌደ
ራል ፖሊስ አባላት ልያዝ የምችልበት እድል ሰፊ ነው፡፡ እስከአሁን ግን
አሳሪዎቹ አልመጡምና መፃፌን ቀጥያለው፡፡ ብእሬን እስኪነጥቁኝ ድረ
ስም ገና እፅፋለሁ፡፡ እውነት ለመናገር ግን ሰሞኑን ከመቼውም ጊዜ በ
ላይ ከፍቶኛል፡፡ ለወትሮ እንኳን ዘመን ሲለወጥ ብዙ ተስፋ ስለማደር
ግ የዚህ አይነት ስሜት አይሰማኝም ነበር፡፡ አሁን ግን በጣም የምቀርባ
ቸው ሰዎች እንደድንገት እነዛ በቴሌቪዥን እንደምናወቃቸው፤ ቦንብ
ለብሰው፣ ቦንብ ጨብጠው እየሩሳሌምን የሚደበላልቁት ወይም አፍጋ
ኒስታን ያለው የአሜሪካ ሰራዊት ላይ የእሳት ዝናብ እንደሚያዘንቡት አ
ይነት ሰዎች ናቸው እየተባሉ እየተያዙ ነው፡፡ በጣም የማከብረው አን
ጋፋው እና ተወዳጁ አርቲስት ደበበ እሸቱ አንዱ ነው፡፡ ሌላኛው እንዳ
ንተ ላሉ በርካታ ወጣቶች አንደሞዴል እየታየ ያለው ወጣቱ ፖለቲከኛ
አንዱአለም አራጌ ነው፡፡ ሌሎች ስም የሌላቸው እልፍ አላፍት ሀገር ወ
ዳዶችም ..አሸባሪ.. እየተባሉ በገፍ እየታፈሱ ነው፡፡

ከወራት በፊት እንደዋዛ የአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ምክትል አዘጋጅ
ውብሸት ታዬ እና ባልደረባዬ የፍትህ ጋዜጣ ትንታግ ፀሐፊ  ርዕዮት አ
ለሙ አሸባሪ ተብለው በቊጥጥር ስር ዋሉ፡፡ ነገሩ በጣም እየመረረ መ
ሄዱን እና የመለስና የኢህአዴግም ለቀጣዮቹ 20 አመታት በስልጣን የ
መቆያ ስልትም እንደተቀየረ በብርቱ ጠረጠርኩ፡፡

አሁን ጥርጣሬ እውን ሆኖአል፡፡ ለምን መሰለህ? በጣም የማከብረው
ጋዜጠኛ እና ተንታኝ እስክንድር ነጋ አሸባሪ ተብሎ በመያዙ ነው፡፡እስ
ክንድር ነጋን መቼም ታውቀዋለህ፡፡ ቢሆንም ግን ስለዚሁ ብርቱ እና
መንፈስ ፅኑ ወዳጄ ትንሽ ላጫውት፡፡

ይህ ..የፕሬስ ጀግና.. የዛሬ 44 አመት ነው በአዲስ አበባ ከተማ የተወለ
ደው፡፡ የመጀመሪያ እና የመለስተኛ ደረጃ ትምህርቱን በእንግሊዝ ስኩ
ል ነው የተማረው፡፡ ከሁለተኛ ደረጃ አስከ ሁለተኛ ዲግሪው ድረስ ደ
ግሞ በአሜሪካን ሀገር ተማረ፡፡ ከለታት አንድ ቀንም አምባገነኑ የወታ
ደራዊ ጁንታ መንግስት ..ትግላችን ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ነው.. የሚ
ል ሰንደቅ ባነገቡ እና ብሶት በወለዳቸው ጎበዞች ተገረሰሰ የሚል ዜና እ
ንደዋዛ በቢቢሲ ሰማ፡፡ ይህንንም ተከትሎ በ1983 ወርሀ ሰኔ በተካሄደ
ው ኮንፈረንስ መዝጊያ ላይ ..የታሰርንበትን እግረ ሙቅ በሀይላችን በጥ
ሰን ዴሞክራሲን ከእውነተኛ ባለቤቷ (ከህዝብ) ጋር አገናኘናት.. ሲሉ የ
ወቅቱ ፕሬዝዳንት መለስ ዜናዊ መናገራቸው በመላው አለም ተሰማ፡፡
ይህ ሰውም ሰውየው የሚናገሩት እውነት መስሎት በአመቱ ወደ አገሩ
ኢትዮጵያ ገባ፡፡ ገብቶም እስፔሻላይዝድ ባደረገው የኢኮኖሚክስ ሙ
ያ ላይ አልተሰማራም፡፡ ይልቁንም ከነብሱ ጋር በተሳሰረው የጋዜጠኝነ
ት ሙያ ተሰማራ እንጂ፡፡

እስክንድር ነጋ ለሀገሪቱ የመጀመሪያ የሆነችውን ነፃ ጋዜጣ ..ኢትዮጲ
ስ..ን መስርቶ የሀገሩን ፕሬስ ለማሳደግ ደፋ ቀና ማለት ጀመረ፡፡ ሆኖም
ትግሉ ካለቀ በኋላ የ..ዳቦ ተቆረሰ፤ ጨዋታ ፈረሰ.. ደራሲዎች እልፍ አ
ላፋት የደሃ ልጆች ያለቁበትን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ጥያቄ ትግል እና
አላማውን፤ እስከ አሁን ማንም ወደ አልደረሰበት ጥልቅ ውስጥ ከቀበ
ሩ በኋላ፤ የህወሓት አመራሮች እና ዘመዶቻቸውን በሚያበለፅግ አዲስ
ድርሰት ተኩት፡፡ ይሄን ጊዜም የእስክንድር አላማ እንቅፋት ገጠመው፡
፡ የኢትዮጲስ ዋና አዘጋጅም ተፈራ አስማረ (ነብሱን ይማረውና) ፀጉሩ
ን ተላጭቶ ከርቸሌ ገባ፡፡ የደርግ የአፈና ስልትም ጥቂት መሻሻሎች እየ
ተደረገባቸው  ተመልሰው መጡ፡፡

እነሆም ኢትዮጲስ ተዘጋ፡፡ እስክንድር ነጋም ..ሀበሻ.. የምትባል የእንግ
ሊዘኛ ጋዜጣ ማዘጋጀት ጀመረ፡፡ ከእለታት በአንዱ ቀንም  የጠዋት ስ
ፖርት (በነገራችን ላይ እስከተያዘበት ጊዜ ድረስ የጠዋት ስፖርት አቋ
ርጦ አያወቅም) በሚሰራበት ጊዜ ከየት መጡ ያልተባሉ ሰዎች፤ ገና ጎ
ህ ሳይቀድ፤ የሰማይ አዋፋት እና ፈጣሪ ብቻ ምስክር በሆነበት በዛ ጭ
ር ባለበት ጠዋት ደብድበው ሲበቃቸው፤ እጁን ሰበሩት፡፡ ለረጅም ጊ
ዜም እጁ  በጀሶ ታስሮ ዳነ፡፡ ይሄም ሆኖ ግን እስክንድር አልተበገረም፡
፡  መንግስትም እሱን መደብደብ አልሰለቸውም፡፡ አሁንም በአንድ ጠ
ዋት በተለመደው ቦታ እና ሰዓት (ስፖርት በሚሰራበት) በታጠቁ ሀይ
ሎች ተከቦ ማዕከላዊ ገባ፡፡ በማዕከላዊ ሁለት ቀን ካደረ በኋላ የደረሰበ
ትን በአንደበቱ  የነገረኝን እንደወረደ ላውርድልህ፡-  ..አንድ ሌሊት ሶ
ስት ሰዎች ለብቻዬ የታሰርኩበትን በር ጓጉንቸር መፈልቀቅ ጀመሩ፡፡ እ

ኔም ነቃ ብዬ የሚሆነውን መጠበቅ ጀመርኩ። ከጥቂት የቁልፍ ካካታ
በኋላ በሩ ወለል ብሎ ተከፈተ። ሶስቱ ሰዎችም ወደ አለሁበት ክፍል
ገቡ። ነገር ግን የሰዎቹ ፊት አይታይም። በፎጣ ተሸፍኖአልና። አንደ
ኛው ታጣቂ ..በዚህ ፎጣ ፊትህ እንዳይታይ አድርገህ ሸፍን.. አለና አን
ድ ፎጣ ወረወረልኝ።አይኔ ማየት እንዳይችል አድርጌ በሰጡኝ ፎጣ እ
የሸፈንኩ፤ በልቤ አይ ሊረሽኑኝ አይደለም የመጡት። ሊረሽኑኝ ቢሆን
መልካቸውን እንዳላየው ፊቴን እይሸፍኑም ነበር እያልኩ ትእዛዛቸውን
ፈፅሜ ጨረስኩ። ከዛ በኋላ ሁለቱ ወደ እኔ መጥተው ክንድ እና ክን
ዴን ይዘው አነሱኝ። በዛ ውድቅትም ከዛች ብቸኛ ክፍል ወጣሁ። ለሶ
ስት ጊዜ ያህል ግቢውን እየደጋገሙ አዙረው ሲያበቁ አንድ ክፍል ወስ
ጥ ይዘውኝ ገቡ። የገባንበት ክፍል ውስጥ ፎጣውን ከፊቴ ላይ አነሱና
ገለበጡኝ (ወዳጄ እስክንድር ገለበጡኝ ሲል ገብቶሃል? ማዕከላዊ ተገለ
በጥክ ማለት ደርግ እስረኛን ይገርፍበት የነበረው ዘዴ እየተተገበረብህ
ነው ማለት ነው። በደንብ ግልፅ እንዲሆንል ከፈለክ ደግሞ መስቀል አ
ዳባባይ ባለው የሰማታት መታሰቢያ ውስጥ አገራረፉ በምስል ተቀምጦ
ልህል) ውስጥ እግሬን እስኪደክማቸው ገርፈው ሲያበቁ በመጣሁበት
ተመሳሳይ መንገድ መራመድ ስላልቻልኩ ተሸክመው መለሱኝ። አሁን
አንድ ነገር ገባኝ፤ ለካ  አይኔን በጨርቅ አስረው ግቢውን ሶስቴ ያዞሩኝ፤
ስለተገረፍኩበት ቦታ መረጃ እንዳይኖረኝ ወይም ከግቢው ውጭ እንደ
ተገረፉኩ እንዳስብ ነው።..

ብታምንም ባታምንም እስክንድር ነጋ እነዚህን ሁሉ ያለፈ የፕሬስ ጀ
ግና ነው። በእርግጥ የወዳጄ ህመማት በዚህ አላበቃም። እንዲሁ ከለ
ታት አንድ ቀንም ማዕከላዊ ተይዞ ገባ። እዛም አንዱ ጠባቂ ጎኑን በወ
ታደር ጫማ እረገጠውና አጥንቱ ተሰብሮ ለአንድ ወር ያህል ለመመገ
ብም ሆነ ወደ መፀዳጃ ቤት ለመሄድ፤ አሊያም ከተኛበት ፍራሽ ለመነ
ሳት ያለጠባቂዎቹ እርዳታ የማይሞከር ሆኖበት በመከራ ማቆ ማቆ ድ
ኖአል።

መቼም እየነገርኩህ ያለሁት በኢህአፓ ጊዜ ስለነበረው አሰቃቂ ድርጊ
ት ነው ብለህ ማሰብህ አይቀርም። ግን አይደለም። እመነኝ.. ይሄ ሁ
ሉ መከራ ዛሬም በስልጣን ላይ ባለው መንግስት፤ ዛሬም በማዕከላዊ እ
ስር ቤት ታስሮ በሚገኘው እስክንድር ነጋ የደረሰ ነው። የእስክንድር
መከራ በዚህ አልቆመም። ሚኒሊክ፣ አስኳል እና ሳተነው የሚባሉ ሶ
ስት ጋዜጦችን (አርብ፣ ማክሰኞ እና እሁድ የሚታተሙ) ከባለቤቱ ጋ
ር ማሳተም ጀመረ።

አንተ.. ..ባል እና ሚስት ከአንድ ባህር ይቀዳሉ.. ያለው ማን ነበር?... የ
ሆነ ሆኖ እስክንድር ነጋ እንዲህ እንደዛሬው ለጋዜጠኞችም ..አሸባሪ.. የ
ሚባል ታፔላ ሳይለጠፍ    ዘጠኝ ጊዜ  ለምን ፃፍክ ተብሎ ታስሮ ተፈ
ቶአል። የመጨረሻው እስሩ ምርጫ 97ን ተከትሎ በተፈጠረው ቀው
ስ እሱ የ..ቅንጅት አባል.. ተብሎ፣ ባለቤቱ ሰርካለም ፋሲል ደግሞ በ
ተጠቀሱት ጋዜጦች አሳታሚነት እና ጋዜጠኛ በመሆኗ ተያይዘው ቃሊ
ቲ ወረዱ። የሚገርመው ነገር እስክንድር ነጋ የቅንጅት አባል አልነበረ
ም። በመጨረሻም ከ20 ወራት እስር በኃላም በጅምላ እንደገቡ በጅም
ላ ወጡ። እስክንድር ግን በይቅርታ ሳይሆን በነፃ ነው የተለቀቀው። ለ
ምን መሰለህ? ሲጀመርም ..ሰውየው.. የታሰረው በብዕሩ ስለነበረ ነው፡
፡ በእርግጥ ..የተከሰስከው በጋዜጠኛነትህ ነው.. አልተባለም። የተባለ
ው ባልዋለበት የቅንጅት አመራር ተብሎ እንጂ። ዛሬም ይኼው ታሪክ
መሰለኝ የተደገመው። መቼም ስለቃሊቲ፣እስክንድር እና ባለቤቱ ካነሳ
ን አይቀር አሳዛኙ ገጠመኛቸውም አብሮ መነሳቱ አይቀርምና፤ እኔም ላ
ንሳልህ። እንዳልኩህ እስክንድር የታሰረው እስከባለቤቱ ነበር። እናም
ከቀናቶቹ በአንዱ በዛው በቃሊቲ ..የሴቶች.. ተብሎ በተከፈለው እስር
ቤት ውስጥ አንዲት እስረኛ ምጥ አጣደፋት። ምንም ሊያደርጉ የማይ
ችሉት አብረዋት የታሰሩ እስረኞችም የሚዙት የሚጨብጡትን አጡ፡
፡ ሴቲቷም ምጡ እየጠነከረ ህመሙም እየበረታባት ሄደ። የማታ ማታ
ም ወደ ፖሊስ ሆስፒታል ተወስዳ ወንድ ልጅ ከነቃጭሉ ተገላገለች ።
ይች እናት እንደሌሎች እናቶች ወጉ አልደረሳትም። አራስ ቤት ተቀም
ጣ ..ማርያም በሽልም ታውጣሽ.. የሚላትም አልነበረም። እንደ እመ
ጫቶችም ገንፎ እያገነፉ፤ አጥሚት እየሰራ የሚያርሳት አልነበረም። በ
ፖሊስ ታጅባ ከወለደችበት ፖሊስ ሆስፒታል ወደ ፌደራል ፖሊስ ማ
ረሚያ ቤት ተመለሰች። ባለቤቷም እሷ ካለቸበት አስር ሜትር ባልበ
ለጠ እርቀት ላይ ይገኛል። ሆኖም ግን እጎኗ ተገኝቶ የጭንቀቷ ተካፋ
ይ የመሆን እድል አልነበረውም። ሌላው ቀርቶ ህፃኑንም አላየው። ይ
ች ሴት የዛ ሰው ባለቤት ነች። የእስክንድር ነጋ፤ጋዜጠኛ ሰርካለም ፋ
ሲል። ሆኖም ይሄ ሁሉ ሲሆን አባትየው የሰላም እንቅልፍ እያንቀላፋ
አልነበረም። ደመ ነፍሱ አንዳች ነገር ነግሮታል። አየ.. ይሄ ሰው ባለቤ
ቱ የፀነሰችበትን ቀን ያውቀዋል። እናም መቼ እንደምትወልድ ያውቀ
ዋል ማለት ነው። በዛ ወቅትም በጥብቅ እንደምትፈልገው ያውቃል።
ነገር ግን የግዙፉ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት አጥር ለያይቷቸዋል። ብቻ ባለ
ቤቱ በሰላም ትገላገል ዘንድ ፈጣሪውን በልቡ እየተማፀነ ነው። የሚወ
ዳት ባለቤቱ ደህንነት አሳስቦታል። ከተፀነሰ ጀምሮ በጉጉት ሲጠብቀ
ው የነበረውን ልጁንም በጣም ናፍቋል። ዳሩ ምንም ሊያደርግላቸው
እንደማይችል ጠንቅቆ ያውቀዋል። ብቻ ይብከነከናል።... አቤት የዚ
ህ ሰው መከራ? መቼ ይሆን የሚያልቀው? ለሀገሩ ያለውስ ፍቅር በም
ን ይለካ ይሆን?

...በመልእክት ቅብብሎሽ ባለቤቱ በሰላም ወንድ ልጅ ተገላግላ፤ የአራ
ስ ቤት ጊዜዋን በእስረኞች ተከባ በእስር እያሳለፈች እንደሆነ ሰምቷል፡
፡ በዚህም ምክንያት  አንድ ሸክም ወርዶለታል። በብርቱ አሳስቦት የነ
በረው የባለቤቱ ደህንነት። አሁን አንድ ነገር ቀረ። የልጅ ናፍቆት። ያ
ውም የመጀመሪያ ልጅ ሲሆን አስበው? እኔ ስጽፈው ብዙም አይሰማኝ
ም። አባት አይደለሁማ። አባትነት ግን ምን አይነት ስሜት ይኖረው ይ
ሆን? መቼም አሳሪዎቹ አባቶች ስለሆኑ ጠንቅቀው ያውቁታል ብዬ አስ
ባለው።...ብቻ ከአድማስ ውጭ ምንም ከማያሳየው አጥር ጀርባ፤ የሚ
ወዳት ባለቤቱ እና ዘጠኝ ወር የናፈቀው ልጁ እንዳሉ ስለሚያውቅ ይ
ብሰለሰላል። መብሰልሰል ብቻ። ይሄ አባት አሳሪዎቹ ራርተው ልጁን
ሊያሳዩት እንደማይችሉ ያውቃል። ሆኖም ጊዜው እስኪያልፍ ናፍቆቱ
ን የሚወጣበት አንድ መላ ዘየደ። ከተወለደ ጀምሮ ያለየውን ልጁን ስ
ም ..ናፍቆት.. በማለት፤ ናፍቆቱን ማስታገስ።

...ዛሬ ናፍቆት አምስት አመት ከግማሽ ላይ ደርሶአል። ሰሞኑን ደግሞ
አባቱ ከትምህርት ቤት ሲያመጣው በታጠቁ ሀይሎች ተከቦ እፊቱ በካ
ቴና ታስሮ እያየ እሪሪ... እያለ ነው። አሳሪዎቹ እናቱ እስከትረከበውና
ከፊታቸው ገለል እስከታደርገው ትእግስት ስላልነበራቸው በአባትየው
ክንድ ሰንሰለት ሲያጠልቁ፤ ናፍቆት መሬት እየተንፈራፈረ ያለቅስ ነበር፡
፡ አሁን ግን የልጅነት ደመ-ነፍሱ አባቱን መልካም ነገር እንዳላጋጠመ
ው ስላወቀም ነው አምርሮ እያለቀሰ ያለው። አቤት.. ይሄኔ የአባቱ ሀዘ
ን እምን ድረስ ጥልቅ ይሆን?... የዚህ ሰው ህማማትስ መቼ ይሆን ማብ
ቂያው? እድሜ ዘመኑን ሲቸነከር፣ ሲሸር፣ ሲቸነከር ሲሸር... በናፍቆት
ሚጢጢ ልብስ ምን እየሰረፀ ይሆን?

ለመፃፍ ነፃነት በሚደረግ ግብግብ የሚደርሰውን ቁስለት ሁሉ ይህ ሰ
ው እየቆሰለ ነው። ..አሸባሪ.. ተብሎም እስር ቤት ከገባ ዛሬ 10ኛ ቀኑ ነ
ው። እኔም ይህን ወዳጄን እንዴት አሸባሪ ሊሆን እንደቻለ ባስበው ባ
ስበው ደከመኝ እንጂ ጠብ ያለ ነገር አላገኘሁም። ልክ ከዚህ ቀደም ጠ/
ሚኒስትር መለስ ስልጣን ይለቁ እንደሆነ ተደጋግሞ መጠየቃቸውን ተ
ከትሎ ..ባስበው ባስበው ደከመኝ.. እንዳሉት ማለቴ ነው። እስክንድር
ን ከአልቃይዳ ወይም ከግንቦት 7 ጋር ለማገናኘት በጭራሽ ሊታሰብ የ
ማይችል ሆነብኝ። ሰውየው ገና ሲጀመርም ከህግ ውጭ የሚደረግ ት
ግልን ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን በጭራሽ አይደግፍም። ከዚህ እኩ
ል ደግሞ ስለኢትዮጵያ በሁለተኛ ሀገር ሆኖ የሚደረግ ትግልንም በጽኑ

ይቃወማል፡፡ ለዚህም ነው በ1984ዓ.ም አሜሪካዊ ዜግነትን አልፈልግ
ም ብሎ ወደ ሀገሩ የገባው፡፡ በዚህ ላይ ጥብቅ ሃይማኖተኛ ነው፡፡በሚ
ከተለው እምነት (ኦርቶዶክስ ክርስትና) ያሉ አጿማቶች አንዱም ሰይቀ
ር የሚፆም፤ ትርፍ ጊዜም ካገኘ በየገደማቶች እየዞረ በረከትን የሚፈል
ግ ሰው ነው፡፡ ይገባሀል እስክንድር ይሄ ነው፡፡ በድጋሚ ይገባሃል ይህ
ሰው አውሮፕላን አግተው የኒዎርክን መንትያ ህንፃዎች ወደ ፍርስራሽነ
ት እንደቀየሩት አሸባሪዎች ..አሸባሪ.. ተብሎ ታስሮአል፡፡ አሳሪዎቹ እን
ደሚሉት ከሆነ ..አስቀድመን በቁጥጥር ስር ባናውለው ኖሮ አንዱን ወ
ይም ብዙዎቹን የአዲስ አበባ ህንፃዎች በፈንጅ ያጋየው ነበር፡፡ ወይም
አንድ ሰሞን ፋሽን ሆኖ እንደነበረው ሚኒባስ ታክሲዎች እና ሆቴሎች
በተጠመደ ፈንጅ ይጠቁ እንደነበረው አይነት ጥቃት ሊሰነዝር በዝግጅ
ት ላይ ነበረ እያሉህ ነው፡፡

...Wikliks (ዊክሊክስ) ለተባለው ድህረ ገጽ ምስጋና ይግባውና ባለፈ
ው ሳምንት ኢትዮጵያን በሚመለከት ባጋለጠው ሚስጥር ላይ በአዲስ
አበባ ይደርስ የነበረው የፈንጂ ጥቃት በመንግስት የተቀነባበረ ነው ብ
ሎናል፡፡ጎበዝ.. ይሄኔ ነው ጉድ ፈላ ማለት.. መንግስት ዜጎቹን በፈንጂ
እያጠቃ የእከሌ ድርጅት አባላት፣የእቶኔ ድርጅት አባላት... ናቸው ሲለ
ን ነበር፡፡ ረጅም እድሜ ለዊክሊክስ ይሁንና፤ ነበር ባይሰበር ሆኖ ቀረ
እንጂ፡፡ ግን ከዚህ ሁሉ ስቃይ ምን ሊያተርፉ ፈልገው ይሆን? ፖለቲካ
የሚሉትስ ይሄ ይሆን እንዴ? ግብር የሚከፍሉ ዜጎችን በከፈሉት ግብ
ር ፈንጂ እየገዙ መንደድ? ...ብቻ እንጃ፡፡ በእርግጥም በኢትዮጵያ የ
አሜሪካ አምባሳደር ወደ ሀገሩ በላከው መልእክት ላይ እነዚህን ጥቃቶ
ች ሆን ብሎ መንግስት እንደሚያደርስ ዊክሊክስ ከነገረህ በኋላ ..አዲሱ
የፀረ ሽብር አዋጅ.. ስለምን እንደተቀመረ የጠረጠርከው ነገር የለም? አ
ረ ጎበዝ.. ጠርጥር እንጂ፡፡ ያልጠረጠረ እየተመነጠረ እኮ ነው፡፡ ወንድ
ሜ ኢህአዴግ መለኛ ሰው አለው፡፡ መለስ የሚባሉ፡፡ ለእያንዳንዷ መሰ
ናከል አስቀድመው የሚዘጋጁ፡፡ ለምሳሌ የመያዶች ህግ፣ የፕሬስ ህግ፣
የፖለቲካ ፓርቲዎች መደራጃ ህግ፣ የፀረ-ሽብርተኛ ህግ... ሁሉም ከም
ርጫ 97 በኋላ የተቀመሩ ናቸው፡፡ አሁን ደግሞ እነዚህ ህጎች ቁና ቁና
ሙሉ እያመረቱ ነው፡፡ እመነኝ ገና ያመርታሉ፡፡ ምናአልባት ..ጌቶች..

# በአሰብ ወደብ መወሰድ ነፍሳችን አብሮ ተወስዶብናል

- ከ10 በላይ የሚሆኑ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አሰብን ለማስመለስ ፕሮግራም ቀርፀው ይ
ታገላሉ
- ወደብ አልባ መሆን የውጭ ንግድን ከ33-43 በመቶ እንዲቀንስ ያደርጋል
- ኢትዮጵያ ከድሃም ድሃ ከሆኑ 13 አገሮች ተርታ ትገኛለች
- ኢትዮጵያ ለወደብ በቀን ከ3 ሚሊዮን ብር በላይ ትከፍላለች

ደሳለኝ በዛብህ
desalew@yahoo.com

ካለፈው የቀጠለ

## የባህር በር ለማዘጋት የተደረገ ጥረት

ዶ/ር ያዕቆብ የባህር በር አስረካቢ ስለሚሉት ህወሓት/ኢህአዴግ ከዚህ እንደሚከተለው
ጽፈዋል፡፡ የህወሓት መሪዎች ኤርትራን አስገንጥሎ ኢትዮጵያን ወደብ አልባ እንድትሆን
የሰረፀባቸው ስሜት ገና በተማሪነታቸው ..ማህበረ ገስግስቲ ብሄር ትግራይ.. የተባለው የ
ተማሪዎች ማህበር ከአቋቋሙበት ጊዜ ጀምሮ ነው ይላሉ፡፡ ወደ ህወሓት ከተለወጡም በ
ኋላ የኤርትራ ጥያቄ ነፃ የመውጣትና የቅኝ ግዛት ጥያቄ ነው በማለት የትግላቸውን አንኳ
ር ጣሉ ይላሉ፡፡ በ1983ዓ.ም የተደረገው የሰላም ጉባኤ ምንም አይነት ውክልና እና ስል
ጣን ሳይኖረው ኤርትራ እንድትገነጠል መወሰኑ ውሳኔውን ተከትሎም የሽግግር መንግስ
ቱ ፕሬዚዳንት የነበሩት አቶ መለስ ዜናዊ የጉባዔውን ውሳኔ ለተባበሩት መንግስታት ድር
ጅትና ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት አስተላልፈው ለኤርትራ እውቅና እንዲሰጡ ያሳወቁበ
ት ደብዳቤ ኤርትራን ለማዋለድና ኢትዮጵያን ወደብ አልባ ለማድረግ ችሏል ይላሉ፡፡ ከ
ዚህም በተጨማሪ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ጊዜ የኢትዮጵያ ጦር ኤርትራ ግዛት ዘልቆ ገ
ብቶ ወታደራዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ቦታዎች ይዞ መቆየት ሲችልና ኤርትራንም አንዳንድ
ግዴታዎች ውስጥ ሳያስገባ የኢትዮጵያ ጦር በሩጫ እንዲወጣ መታዘዙ ህወሓት/ኢህአዴ
ግ ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት እንድትሆን አለመፈለጉን የሚያሳይ ነው ይላሉ፡፡ የኢት
ዮ-ኤርትራ ጦርነት ከተጠናቀቀ በኋላም ቢሆን ኢህአዴግ ኢትዮጵያ የማትገደድባቸውን
ና አምስት ጊዜ ያክል በተለያየ ምክንያት የሞቱትን የ1900፣ የ1902 እንዲሁም የ1908 የቅ
ኝ ግዛት ውሎችን መሰረት በማድረግ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ እንድትሆን ማድረጋቸውን
ያስረዳሉ፡፡ ኢህአዴግ በዲፕሎማሲም ይሁን ወይንም በሌላ በማናቸውም መንገድ አሰብ
ወደ ኢትዮጵያ እንድትታጠፍ ፍላጎቱ እንደሌለውና ብሎም እንዲያውም እንደሚቃወም
በከረሩ ቃላትና በብስጭት ስሜት በተደጋጋሚ ገልጾአል፡፡ ከዚህም አልፎ አሰብን ወደ ኢ
ትዮጵያ ለማካለል የሚመክር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ኃይል ቢነሳ ኢህአዴግ እርምጃ እን
ደሚወስድበት ከዚህ ቀደም ጠ/ሚኒስትሩ በአጽንኦት አስጠንቅቀዋል፡፡ ይህም ማለት ኢ
ህአዴግ በኢትዮጵያ በስልጣን እስከቆየ ድረስ የኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት የመሆኗ እ
ድል ዜሮ ነው ይላሉ ዶ/ር ያዕቆብ፡፡

## ሉዓላዊ ግዛትን አስመልክቶ የሌሎች አቋም

ዶ/ር ያዕቆብ ሉዓላዊ ግዛትን በተመለከተ ሌሎች አገሮችና ህዝቦች ያላቸውን ጠንካራ እ
ና ጊዜ የማይሽረውን አቋማቸውን ከዚህ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡ አሰብን አስመልክ
ቶ በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መካከል ያለው አቋምና ስሜት በእስራኤሎችና በፍልስጤ
ማዊያን መሃከል ካለው አቋምና ስሜት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ኢየሩሳሌም በይሁዳዊያን ል
ብ ሰርፆ እንደገባ ሁሉ አሰብም በኢትዮጵያዊያን ዘንድ በተመሳሳይ ሁኔታ ይንፀባረቃል፡
፡ ስለሆነም እስራኤላዊያን ኢየሩሳሌምን በምንም አይነት ለፍልስጤማዊያን እንደማያስ
ረክቡት ሁሉ ኢትዮጵያዊያንም መቼም ቢሆን አሰብ የኤርትራ ግዛት ናት ብለው አይቀ
በሉም ይላሉ፡፡
ቦሊቪያ በ1883ዓ.ም ከቺሊ ጋር ባደረገችው ጦርነት የባህር ጠረፍ ግዛቷ በቺሊ ተወሰደ
ባት፡፡ ቦሊቪያ የባህር በር ሲወሰድባት ነፍሷ ከዚያው ጋር ሄደ እያሉ ቦሊቪያዊያን ይገል
ጹታል፡፡ እንደ ቢቢሲ ዘገባ የቦሊቪያ ዜጋ ሁሉ ከልጅነቱ ጀምሮ ያደገው ቺሊ የባህር ጠ
ረፋችንን ሰረቀችን ሲባል እየሰማ ሲሆን እርሱም በተራው ለልጆቹ ይህንኑ እየነገረ ያሳድ
ጋል፡፡ ማንኛውም ቦሊቪያዊ አገርህ ወደብ አልባ ሆነች ሲሉት በምንም አይነት የማይቀ
በለው ሲሆን ህዝቡም በየዓመቱ የባህር በር የተወሰደበትን ቀን ዘክሮ ይውላል፡፡ ቅርብ
ጊዜ ደግሞ ከ132 አመታት በኋላ የባህር በሬ በቺሊ ተወሰደብኝ የምትለዋ ቦሊቪያ ጉዳዩ
ን ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እንደምትወስደው አስታውቃለች ይላሉ ዶ/ር ያዕቆብ፡፡

## ወደብ እንድናጣ ያደረጉ የወጭ ኃይሎች

ግሪጎሪ ኮፐሌይ የተባለ የአፍሪካ ኤክስፐርት ጋዜጠኛ ስለኢትዮጵያ እና ግብጽ ግንኙነት
ሲጽፍ የሚከተለውን አስፍሯል ይላሉ ዶ/ሩ.. የግብፅ የአፍሪካ ቀንድ ዋነኛው ፖሊሲ ኢት
ዮጵያ በአካባቢው የበላይነት እንዳይኖራት ከባህሩ ዙሪያ ማግለል ነው፡፡ ይህን አላማዋን
በኤርትራ እና በኢራን እያስፈጸመች ነው፡፡ ግብጽ የኤርትራ የነፃነት ንቅናቄዎችን በመርዳ
ት ቀደም ሲል የኢትዮጵያ የባህር ኃይል ይቆጣጠረው የነበረው የቀይ ባህር ደቡብ ክፍል
ከኢትዮጵያ እጅ በማውጣት ኤርትራ ነፃ እንድትወጣ እና ኢትዮጵያ ከቀይ ባህር ተገልላ
በተፈጥሮም ሆነ በባህል መቼም የኤርትራ አካል ሆና የማታውቀውን አሰብንም እንድታ
ጣ አደረገቻት፡፡ ግብፅ የአረብ መሪነትዋን በመጠቀም ሱዳን፣ ሶሪያ፣ ኢራቅ፣ የመን፣ ሊቢ
ያ እና ሳውዲ አረቢያን በማቀነባበር ኢትዮጵያን ለማዳከም በመጣር ላይ ነች፡፡ ግብጽ ይ
ሄን የምታደርገው ጠንካራዋ ኢትዮጵያ በአባይ ውሃ ላይ ያላትን መብትና የባህር መብትዋ
ን ልታስከብር ትችላለች ከሚለው ፍራቻ በመነሳት ነው ሲል ጽፏል.. በማለት ያስረዳሉ፡፡
ኢትዮጵያ ለምታነሳው ጥያቄ የኤርትራዊያን ምላሽ በኢትዮጵያ የባህር በር መዘጋት ከኢ
ትዮጵያዊያን የሚደመጠው ምሬት ኤርትራዊያንን ማስከፋት አይገባውም፡፡ ኤርትራዊያን
ስለሀገራቸው የሚሰማቸውን ያህል ኢትዮጵያዊያንም ይሰማናል፡፡
እኛም እንደ ኤርትራዊያን አገራችንን እንወዳለን፡፡ አቅማችን በፈቀደ መብትዋንና ህጋዊ
ጥቅሟን ለማስጠበቅ እንጥራለን፡፡ በተለይም አንዲት ጋሻ መሬት በሌላው የማያስነካው የ
ኤርትራ መንግስት ኢትዮጵያ ተቆርቋሪ ስለሌላት ብቻ የባህር በር ይቅርባት ማለት ኢትዮ
ጵያዊያን መቼም ቢሆን የማይቀበሉት በደል ከመሆኑም በላይ ለዘለቄታውም ቢሆን ለኤ
ርትራም የማይበጃት ነገር ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያ እና ኤርትራዊያን አሰብ ወደ ኢትዮጵያ የ
ሚታጠፍበትን ሰላማዊና ፍትሃዊ መንገድ ቀይሰው አቋማቸውን ይፋ ማድረግ ይጠበቅባ
ቸዋል ይላሉ ዶ/ር ያዕቆብ በዚሁ መጽሐፍ፡፡

## በመፍትሄው ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች

ዶ/ር ያዕቆብ አሰብ የማን ናት በሚለው በዚሁ መጽሐፋቸው ገጽ 195-196 ላይ 3 የመፍ
ትሄ ሃሳቦችን አቅርበዋል፡፡ የመፍትሔ ሀሳቡ ያጠነጠነው በዋናነት በአሰብ ላይ ነው፡፡ ይ
ህ ግን ጥያቄውን በከፊል እንጂ በሙሉ መልስ የሚሰጥ አይደለም፡፡
ኢትዮጵያ አሰብ ብቻ ሳትሆን ኤርትራም ሉዐላዊ ግዛቷ ነበረች፡፡ አሰብም እንዲሁ፡፡ በመ
ሆኑም ጥያቄው መፍትሔው ለምን በአሰብ ላይ ብቻ ተወሰነ የሚል ነው፡፡ በእኔ አስተሳ
ሰብ ኤርትራ ሉዓላዊ ግዛታችን እስከነበረችና የተገነጠለችውም ስልጣንና ውክልና በሌላ
ቸው አካላት አማካኝነት እስከሆነ ድረስ ኤርትራን የተመለከተ መፍትሄም መጽሐፉ ማቅ
ረብ ይጠበቅበት ነበር፡፡ ሌላው በመጽሐፉ አላማ እንደተገለጸው አሰብም ሆነች ኤርትራ
ኢትዮጵያዊያን አእምሮ ውስጥ እየተንቀለቀሉ እንዲኖሩ ለማድረግ የሚያስችሉ የመፍት
ሄ ሃሳቦችን አላካተተም፡፡ ለምሳሌ ለአሰብ የሚታገሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንድነት አሰ
ብም ሆነች ኤርትራ የተወሰዱበትን ቀን የሚያስታውሱበት እና የሚዘክሩበት ቀን ማክበ
ር የፓናል ውይይት ማድረግና ልዩ ልዩ የድጋፍ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞችን ማካሄድ አን
ድ መፍትሄም ሊሆን ይችላል፡፡

# እስክንድር ነጋ እና ስብሃት ነጋ!

ጋዜጠኛ ዮናስ በላይ

የሁለቱ ..ነጋ..ዎች የአብራክ ክፋይ የሆኑት እስክንድርና ስብሃት በፍትህ ጋዜጣ የ2003ዓ.ም ..የዓመቱ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች.. ከሆኑ 5 ሰዎች መካከል ይገኙበታል፡፡ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ በመካከለኛው ምስራቅ፤ እንዲሁም በሰሜን አፍሪካ አገራት እየተቀጣጠለ ባለው ሕዝባዊ አብዮት ዙርያ ..ኢንተርቪው.. ብቻ ሳይሆን ሞያዊ ትንተናና አጫጭር መጣጥፎችን በማቅረብ የሕዝቡን ንቃተ ህሊና ከፍ ለማድረግ ታጥቆ በመክረሙ፤ ፖለቲከኛው ስብሃት ነጋም (አቦይ አልላቸውም-አባትነታቸውን ስለማላምንበት) በ..ሙያቸው.. (..ጠልፎ በማውደቅ..) ወደ ታሪክ ትንተና ገብተው ..ሁለቱ ፕሮፌሰሮች.. (መስፍንና ገብሩ..ን ማኖ ያስነኩበት፤ ልክ በደደቢቱና በቡናው ጨዋታ ዋንጫ ..እንደበሉ.. ሁሉ በፍትህ ጋዜጣ ላይ በተደረገው የ..ቶምና ጄሪ.. አይነት ..ፍልምያ..ም የዓመቱ ሁለተኛው ዋንጫቸውን ያነሱበት ..አጋጣሚ.. ነበር፡፡ እስክንድርም ወደ ጨዋታው መቀላቀል ፈልጎ እንደነበር አጫውቶኛል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ የመጽሐፍት ምርቃት ፕሮግራም በመገኘት የተጠመዱት ስብሃት ነጋ፣ በአክሱም ሆቴል አዳራሽ (አ.አ) ..አብነት.. የሚል ርዕስ የተሰጠው የዶ/ር ሰለሞን ዕንቋይ የህይወት ታሪክን የሚተርክ መጽሐፍ ሲመረቅም ዘግይተው ተገኝተው ነበር፡፡ አቶ ስብሃት መጽሐፉን ሲመርቁ ያደረጉት ንግግር ባጭሩ ይህንን ይመስላል፡- ..ይህን ሰራን፣ እንዲህ አደረግን፣ ይሄን አለማን አትበሉ ገና ነን፤ ገና.. ምንም አልሰራንም፣ ኢትዮጵያ የለችም፡፡ ወደኋላ ቀርተናል፣ የዓለም መጨረሻዎች እኛ ነን፡፡.. የዚህ አይነት ተመሳሳይ ንግግር ለማግኘት ትንሽ ወደ ኋላ ልዞር ነው፡፡ ከወራት በፊት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ለቪ.ኦ.ኤ የሰጠው ቃለ ምልልስን ሳዳምጥ የ..ፍርሃት.. ስሜት ያዘለ ንግግር ያደረገ መስሎ ተሰማኝ፤ ..ሰውየው የተግባር ሰው ናቸው፡፡ ከእንግዲህ አንተን ማሰር ሰልችቶናል ካሁን በኋላ የምንወስደው እርምጃ እናንተን አጥፍቶ መጥፋት ነው.. ብለውኛል.. ሲል ይሄ ሰው መፃፍ ሊያቆም ይሆን? አንቺ ያልታደልሽ የሀገሬ ብዕር ሆይ የካድሬዎች መጫወቻ መሆን መረጥሽ ማለትስ ይሆን? ብዬ ያሰብኩትን ሳልጨርስ ..እኔ ግን መፃፌን አላቆምም.... አለና ከጭንቀት ገላገለኝ፡፡ ለምንድነው ግን ያ አንደበተ ርትዑ ሰው ቀዝቀዝ ባለ ስሜት ከአፉ የሚወጡ ቃላትን እየተቆጣጠረ መልስ ለመስጠት የመረጠው? ከራሱ አንደበት መልስ ማግኘት አለብኝ፡፡ ሆኖም ትዕግስቱ ስላልነበረኝ እሱን እስከማገኘው ሌሎችን ቀድሜ ሳጠያይቅ በድምሩ ..ለሌላ ዓላማ እንደፈለጉት.... ተረዳሁ፡፡ ይህ ደግሞ የበለጠ ሆዴን አሳመመው፡፡ ምንድ ነው ዓላማው? እነሱ ከእስክንድር ምን ይፈልጋሉ? ..ሰላይ ሁንልን?.. ሊሉት? አይደረግም፡፡ ይህ በጀማሪዎች ላይ የሚደረግ የ..ማሸበር.. አንድ መንገዳቸው ነው፡፡ እሱ ከ..እነሱ.. የማይተናነስ የ20 ዓመት ልምድ ያለው፤ እየታሰረ የውስጥ እግሩ ሳይቀር እየተገረፈ፤ እንጀራው ተዘግቶበትም እንደ ..ሌሎቹ.. አገሩን ጥሎ ያልፈረጠጠ፤ ሀገሩን ከራሱና ከልጁ አስበልጦ የሚወድ ምርጥ ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኛ መሆኑን ነበር ከብዙዎች የሰማሁት፡፡ ታድያ ለምን?

የሆነ ሆኖ እስክንድርን በአንድነት ፓርቲ ጽ/ቤት ..ሠላማዊ ለውጥ በኢትዮጵያ እንዴት?.. በሚል ርዕስ ጥናታዊ ፅሁፍ ባቀረበበት ማግስት ፒያሳ አገኘሁት፡፡ ወደ ፕሮግራሙ ለመሄድ ፈልጌ ነበር ነገር ግን ፈራሁ፡፡ ባለቤቱ ትግርኛ ማንበብ ትችላለች (ትግርኛ ቋንቋ መናገር የምትችል ኢትዮጵያዊት) የሚል ወሬ ሰምቼ መጽሔቴን (ጥሕሎ) ልኬለት ስለነበር ልክ እንደተገናኘን ..መጽሔትህ ጥሩ ነው.... አለኝ፡፡ ባለቤትህ አነበበችልህ እንዴ? አልኩት፡፡ ..እህ.. ይህን ያህልምኮ አይቸግረኝም፣ ትግርኛ..... ሲለኝ ከአፉ ለጠቅ አድርጌ፣ ..ትግርኛ እችላለሁ እንዳትለኝ?.. ስለው ..የመጀመርያው የትግረኛ ነፃ ጋዜጣ (ደሐይ) የማን ሆነና..?.. ብሎ ፀጥ አረገኝ፡፡ እስክንድር በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የነፃ ጋዜጣ ..ኢትዮጲስ.. አዘጋጅ መሆኑን እውቅ ነበር፡፡ የትግርኛና የኦሮምኛ ጋዜጦች እንደነበሩት ግን ገና አሁን ከአፉ መስማቴ ነው፡፡ ቀጥታ ወደ ጥያቄዬ ገባሁ፡፡ ..እስክንድር በቅርቡ የፌደራል ም/ኮሚሽነሩ አስፈራርተውኛ ነበር.. ብለህ የሰጠከውን ቃል አድምጬ ግልጽ ያልሆኑልኝ ነገሮች በአእምሮዬ እየተመላለሱ አስቸገሩኝ.. ስለው ልክ በቪ.ኦ.ኤ እንደሰማሁት ..ቃል.. የት እንዳገኙት፤ እንዴት እንደወሰዱትና ከሰውየው ጋር ስልነበረው ..ቆይታ.. ሁሉ ሳይቀንስ ሳይጨምር ተረከልኝ፡፡ እኔ የፈለኩት ግን ይህ አልነበረም፡፡ እስክንድርን አሰፈራርተው ውብሽትን ቃሊቲ የማስወረዳቸው ..ሚስጥር..ን ነው፡፡ ስለዚህ ጥያቄዬን ማስተካከል አለብኝ.. እናም ፊት ለፊት መጠየቅ ይኖርብኛል፡፡ ..ምን ፈልገው ነው እንደዛ ያሉህ? መፃፍ እንድታቆም ነው ወይስ ሌላ ..መልእክት.. አለው?.. ስለው በረጅሙ ተነፈሰ፤ ..ይኸውልህ.. እነሱ የፈለጉት ሁለት ነገር ለማስተላለፍ ነው፡፡.. ሲለኝ ልቤ በሃይል መምታት ጀመረ፡፡ ..አንደኛው ከዚሁ ፒያሳ ነበር የወሰዱኝ፡፡ ሲወስዱኝ በመኪና ወደ አምስት የሚሆኑ ፖሊሶች መጥተው ነው፡፡ ስለዚህ ለአካባቢው ህዝብ እንደ የሰሜን አፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ ህዝቦች ..የሆነ ነገር ብታደርጉ ወዮላችሁ.... ለማለት ነው እንጂ እንደሌላው ጊዜ በስልክ ሊጠሩኝ ይችሉ ነበር፡፡ ሁለተኛው..... ተቁነጠነጥኩ፡፡ ..ሁለተኛው እንዲህ አይነቱ ነገር ቢነሳ ህዝቡን ለመከፋፈል ፈልገው ፣እናንተ ትምክህተኞች ነፍጠኞች ...’ የመሳሰሉ ቃላት ተጠቅመው እኔን ለማበሳጨት ፈልገዋል፡፡ እኔም ማስፈራራታቸውን ስናገር ይሄንንም ..መልእክት.. በሚድያ አብሬ እንዳስተላልፈው እና ህዝቡ ፣አሃ.. ትግሉ እኛን አይመለከትም ለካ የ..እነሱ.. ነው፣ እንዲል እንደፈለጉ ስልተረዳሁ ይህን ቆርጬ አስቀረሁት፡፡.. ብሎ የሚያምር ፈገግታውን ለገሰኝ፡፡ በ93ዓ.ም በሠራዊቱ መሃከል ገብታ ያተራመሰች ..የትግራይ የበላይነት....፣ ለጥቆም በ97ቱ ምርጫ ማግስት የመጣችው ..ዕቃ ወደ ቀበሌ ትግሬ ወደ መቀሌ.....ን የፈበረከች ፋብሪካ ከወዴት ነበረች? አሁን ማንሰልሰል ጀመርኩ፡፡

..ከምንም ነገር በላይ የዚህች ሀገር ህልውናን ማስቀደም አለብንህ፤ ከእንግዲህ አንድ እፍኝ መሬት እንኳን እንዲቆረስብን መፍቀድ የለብንም፤ አንድ ነገር ልንገርህ?.. አለኝ እስክንድር አሁንም ትንታኔውን እንደቀጠለ ..አንድ ነገር ልንገርህ ይህቺ ሀገር ከምትበታተን መለስ እየረገጠ ቢገዛን ይሻላል፡፡.. ማመን አቃተኝ፡፡ የሚያወራው ግን ከልብ ነው፡፡ ማን ነው ይሄ ሰው? ለዚህች ሀገር ከመሪዎቿ በላይ የሚያስበው? ብዬ ስመራምር በመሃል አቦይ ስብሓት በአንድ ወቅት የሰጡኝ ..ቃለ መጠይቅ.. ትዝ አለኝ፡፡ ጥያቄዬ ከሉዓላዊነታችን መደፈር (ኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት) ጋር የተያያዘ ነበር፡፡ ለምንድነው መዋጋታችን ልክ አይደለም የሚሉት? ሉአላዊነታችን እኮ ነው የተደፈረው? መሬታችንኮ ነው የተወረረው? ስላቸው ..ለምን 20 ዓመት አይዟትም (ባድመን) ክብር ነው የሚበልጠው ወይስ እንጀራ?.. ብለው ነበር የመለሱልኝ፡፡ ለእስክንድር ነጋ የዚህች አገር ክብርና ሉዓላዊነት ከነፃነት የላቀ (ከዳቦ በላይ የሆነ) ትርጉም ሲኖረው፤ ለአቦይ ስብሃት ግን ይህች አገር ከመለስ አልፎ በኢሳያስ እንኳን ብትገዛ ለ..ቡና ቁርስ.. የሚሆን ዳቦ እስከተገኘ ድረስ፤ ..አቦይ.. እስከተባሉ ድረስ ለሳቸው ኢትዮጵያዊ የመሆን ትርጉሙ ከዚህ የዘለለ አይመስለኝም፡፡ የእስክንድር ነጋና የስብሃት ነጋም ልዩነት ከዚህ ይጀምራል፡፡ ሲቀጥል ስብሃት ነጋ በመቀሌው ..አፓርታይድ.. መንደር (ስለ አፓርታይድ መንደር ከዚህ ቀደም በፍትህ ላይ እንደፃፍኩ ይታወቃል) ከእህታቸው ወ/ሮ ቁዱሳን ነጋ (የአቶ ፀጋይ በርሀ ባለቤት፣ የዚህ መንደር የበላይ አስፈፃሚ) ጋር የሁለት ቪላዎች ባለቤት ሁነው ስናገኛቸው፤ እስክንድር ነጋ ግን ጠ/ሚኒስትሩ በወቅቱ ለነዚህ ወገኖች እንዳሉት ..አንድም በሚስቱ ወይም በልጁ.. የዚህ ሰፈር አባል አለመሆኑ ነው፡፡ ለነገሩ እስክንድር መች የህወሓት አመራር ሆነና? አይደለም ለእስክንድር አይደለም ለተራ አባል ይቅር እና ለመካከለኛው አመራር እንኳ እዛ ሰፈር መግባት የተፈቀደ አይደለም፡፡ ..አፓርታይድ.. ውስጥ ለመግባት ወይ የክልሉ አመራር መሆን አልያም ..ተላላኪ.. ኢንቨስተር መሆን ይጠበቅብሃል፡፡ እናም እስክንድር አይደለም በነዚህ ደረጃ ቀርቶ የኢትዮጵያ መንግስት በጋዜጠኝነትም ..አያውቀውም..፡፡ እስክንድር ግን ይናገራል .....እቺ ለአፍሪካ የነፃነት አምሳያ የሆነች፣ ነፃነትን ያስተማረች ሀገር ወደኋላ መቅረቷ ነው የሚያብከነክነኝ ከአሜሪካና ከአውሮፓ እያነፃፀርኩ አይደለም እማወራልህ፤ ከዚሁ ከኋላችን ተነስተው ከቀደሙን ከነደቡብ አፍሪካና ጋና እንጂ.. በሁሉም ነገር ወደኋላ መቅረታችን አንሶ በነፃነትም የመጨረሻ መጨረሻ እንሁን..?.. ሲለኝ እነዚህን ቃላት የት ነበር የሰማኋቸው ብዬ ራሴን ጠየቅኩ፡፡ ..አብነት.. የተባሉት ሰውዬ መፅሐፋቸው ሲመረቅ የተገኘው ..ጓደኛዬ.. ስብሃት ተናገሩት ብሎ ከነገረኝ ቃላቶች ተመሳሰሉብኝ፡፡ ስብሃትም ..አብነት.. ተብለው በተሞካሹት ሰውዬ ተናደው ..በደርግ የተነጠቀው መሬቱን ለማስመለስ የታገለ ሁሉ ..አብነት.. ከተባለ ለነፃነት የታገለ ሰው ምን ሊባል ነው? ለዳቦ ሲል እየዋሸ ከየመድረኩ እየተንተተ የተዋረደ ሰው ..አብነት.. ከተባለ እንደ የ77ቱ ምርጥ ኢትዮጵያዊያን ጀግኖች ..የኦሮሞና ሶማሊያ ነዋሪ የሆኑት ዜጋዎቻችን በዳቦ እጦት እየሞቱ ነው.... ብለው ለሚጮሁ ምን አይነት ቃል ሊሰጣቸው ነው? ብለው ተናደው ይሁን ወይም ..አቦይ ስብሃትን ሊያስመትዋቸው ፈልገው በጦማር ጋዜጣ ላይ አፃፉቸው.... የሚለውን የ..የዋሆች.. ወሬ ሰምተው ጭሰው ወይም ሌላ የሚያውቀው እግዚአብሔር አልያም ኮሚኒዝም ነው ፡፡ ምክንያታቸው ከጎጣቸው ይሻገር አይሻገር የራሳቸው ጉዳይ፤ እሳቸው ያሉት ግን ..የለንም.. ወደ ኋላ ቀርተናል ምንም አልሰራንም.. ነው፡፡ በምን? በዳቦ፡፡ እስክንድርም ያብከነከነው ነገር የዓለም መጨረሻ መሆናችን፡፡ በምን?በዴሞክራሲ፡፡ ስለዚህ በሀገራችን ወቅታዊ ጉዳይ ላይ ሁለቱም የሚመሳሰል አቋም ያንፀባርቃሉ፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ አንድ ልዩነት እናገኛለን፡፡ ስብሃት ነጋ በሚያምረው መኪናቸው የአዲስ አበባን መልካም ገፅታ አብሳሪዎች የሆኑት ..እምቡጥ ፅጌረዳዎች.. በመንገድ ላይ ሲሆኑ እስክንድር ነጋ ደግሞ ልጁ እያለቀሰ ጨክኖ ማዕከላዊ ገብቷል፡፡ እስክንድር ግን ለልጁ ትንሽ አያስብለትም? ስብሃት እኮ ለልጃቸው በጣም ነው የሚያስቡለት፤ ..ቻይና ድረስ ልከው እያስተማሩት ነው..፡፡ እስክንድርስ? ልጁ በእርሱ ምክንያት ከርቸሌ ተወለደ፤ አሁንም አባቱ እስር ቤት ይገኛል፡፡ ይሄ ልጅ አድጎ ኢትዮጵያ ምንህ ነች? ሲባል አገሬ ከማለት ይልቅ እስር ቤቴ እንዳይላት ስጋት አድሮብኛል፡፡

ጋዜጠኛ ስለሺ ሓጎስ (የርዕዮት ዓለሙ ጓደኛ) በታሰረ በአምስተኛው ቀን መሆኑ ነው፡፡ የእስክንድር ..በሽብር ተግባር.. ተጠርጥሮ መታሰር የተሰማው፡፡ ከአራት ኪሎ ነበር የተያዘው አሉ፡፡ በፖሊሶች ሲወሰድ የአካባቢው ህዝብ ተሰብስቦ እንደነበር ስሰማ እስክንድር ያለው ትዝ አለኝ፡፡ ..የሆነ ነገር ብታደርጉ ወዮላችሁ.. ብታስቡም.... ለማን? ለአራት ኪሎ ህዝብ፡፡ ቀበናም እንደዛ አድርገው ይሆን? እንጃ.. እንዴት ነው ነገሩ? ያ እንደዛ ለሀገሩ የሚሳሳላት ሰው ..አንድ የፍየል ወጠጤ... አራት ኪሎ አካባ

ቢ.... ለዳቦ ሲል አገሩንና ህዝቡን ለማሸበር በመነሳት.. ቢሉኝ እነዛን የ..ዴንማርክ.. ጋ
ዜጠኞች እንዴት ልመናቸው? እስክንድር ነጋ ሲባል ይሄ ..የአባት.. ነገር አምታቶኝ ስ
ብሃት ነጋ ያሉኝ መሰለኝ፡፡ እነዛ ..ምርጥ.. የደህንነት ሰዎቻችንስ ለምን ተቻ ኮሉ? ቀን
በቀን እየተከታተሉት ትንሽ ቢቆዩ እኮ አንድ ጊዜ እንዳየነው ..ድንቅ.. ዶክመንተሪ ፊ
ልም ለዛውም ከዛ የበለጠ የሚሰራበት ፣ስቶሪ፣ ነበር.. ከዚህ ተጨማሪ ..ይታሰራሉ..
የተባሉትን ሰዎችም በቀላሉ ለማጥመድ አይጠቅምም ነበር ይላሉ ክቡር ሚኒስተር..?
እስክንድርና እኔ የተገናኘንባት እለት በነጋዜጠኛ ውብሸት ታዬና ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓ
ለሙ ላይ ክስ የተመሰረተበት ቀን ነበረችና የክሱ ወረቀት በእስክንድር እጅ በደቂቃ
ዎች ውስጥ ደረሰ፡፡ ስናነበው በአብዛኛው የክሱ መሠረት ከውጭ ሚዲያዎች በተለ
ይ ከኢትዮጵያን ሪቪዩ ጋር በተያያዘ ጉዳይ ነበር፡፡ እንደዚህ አይነት መረጃ ፃፉ (ለም
ሳሌ ጋዜጠኛ ርዕዮት ..በቃ.. የሚል ፅሁፍ የተፃፈበት ወረቀት የተለጠፈበት ግድግዳ
ፎቶ በማንሳት ላከች..፣ ገንዘብ ተቀበሉ ፣ ሌላው ..መልዕክት.. ተቀበለችና አሰራጨች
ነው፡፡ መልዕክቱ ምንድነው? ግልፅ አልሆነልኝም እና እነዛን ቃላቶች ሰንጥቆ የማስረ
ዳት ቸሎታ ያለውን እስክንድርን ጠየኩት፡፡ ..በውብሸትና በርዕዮት ክስ ውስጥ ልዩ
ነት አለ፡፡ የውብሸት ክስ ..ድርጊት..ን ሲያካትት (በተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤ
ቶች ጥቃት ለማድረስ.....፣ የርዕዮት ግን ከጋዜጠኝነት ሥራዋ በተያያዘ ነው፡፡.. አለኝ፡
፡ አንድ ጥያቄ ሰነዘርኩ፡፡ ታድያ አንተስ ለውጭ ሚዲያዎች ትፅፍ የለ ፤ ለምን አንተ
ን አላሰሩህም? እስክንድርም አለኝ ..ይሄን ጥያቄህ ጊዜ ነው የሚመልሰው....፡፡ አሁ
ን እስክንድርን አግኝቼ ልጠይቀው አልቻልም፡፡ ጊዜው ደርሶ ይሆን መልስ የሰጠኝ?

# ፀረ-ሽብር ሽብር እንዳይሆን በደንብ እናስብበት ለመሆኑ ሽብር ምንድን ነው? አሸባሪስ ማነው?

ደሳለኝ በዛብህ
desalew@yahoo.com

ከሰሞኑ ዋነኛው የኢትዮጵያዊያን የመነጋገሪያ አጀንዳ ሽብር እና ፀረ-ሽብር የሚሉት ናቸው፡፡ መ
ንግስት እንዳለው እና ባለው ደረጃ ሽብርተኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ ካለ እጅግ በጣም የምንወዳ
ት፣ የምንመካባት፣ ተስፋችን፣ መጠጊያችን፣ አለኝታችን፣ ታሪካዊቷ፣ የታላላቅ ህዝቦች አገር የሆ
ነችው፣ እንግዳ ተቀባይዋ ኢትዮጵያ አደጋ ላይ ነች ማለት ነው፡፡ ይህ ከሆነ መንግስት ለእያንዳን
ዱ ኢትዮጵያዊ በግሉ እንዲሁም በጋራ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ተጨባጭነት ያለው መረጃ ሊሰጠ
ን ይገባል ደግሞም ግዴታው ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ በቂና አሳማኝ መረጃ ከተሰጠው አገሩን እ
ና የአገሩን ክብር ለመጠበቅ ጎትጓች፣ ቀስቃሽ፣ ለማኝ አጃጋኝ አይፈልግም፡፡ ይህን የኢትዮጵያ ህ
ዝብ ታሪክ የሩቅ ጠላቶቹ ብቻ ሳይሆን የውስጥ ጠላቶቻችን እና ተላላኪዎቻቸው ጭምር ያውቃ
ሉ፡፡ እነዚህ የኢትዮጵያ የሩቅ ጠላቶች በዘመናት ጥረታቸው የእነሱን ተላላኪዎችና አላማ አስፈፃ
ሚዎች በተለያየ መንገድ በኢትዮጵያ ህዝብ ሊሰገሰጉበት ቢችሉም፣ ለጊዜውም የተሳካላቸው ቢ
መስላቸውም ምንም ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ በእንሱ መልክተኞች እንደጥጃ ሲታሰርና ሲፈታ ቢ
ውልም የቱንም ያክል እየተገደለ ቢሆንም እነዚህ ሁሉ መከራዎችና የአንድ ወቅት አምባገነኖች የ
ኢትዮጵያን ህዝብ ደም እና የደም ይዘት የመለወጥ አቅም የላቸውም፡፡ የኢትዮጵያን ህዝብ ታሪ
ክ እንደ አንድ ዛፍ 100 አመት ነው ቢሉትም ወይም ቢያስብሉበትም፣ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሆ
ነ አንዴ ሲፈጠር ኢትዮጵያዊ ተብሎ የተፈጠረና ማንም ሊከልሰውና ሊለውጠው የማይችለው
ኢትዮጵያዊ ደም አለው፡፡ በእርግጥ በታሪክ እና በዚህ አለም ብዙ ገናና ስልጣኔዎች አብበው ተ
መልሰው እንደሽክላ ተንኮታኩተው የተረሱ ቢሆንም የኢትዮጵያ ስልጣኔ እና የኢትዮጵያ ማንነ
ት ግን መቼም ቢሆን ወድቆ የሚነሳ እንጂ እንደሽክላ ተነካክቶ የሚቀር አለመሆኑ እየታየ ነው፡፡
እርግጥ ነው ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝበ የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ ተሰዷል፣ ተርቧል፣ ተዋርዷል፣ በአጠ
ቃላይ የአረብ አገሮች ወጥ ሰሪ ገረድ እና ጫማ ጠራጊ ሆኗል፡፡ ይህ የሆነው ኢትዮጵያ አገሩ የተ
ፈጥሮ ደሃ ሆኖ ሳይሆን ወይም የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ ህዝብ  ሰነፍ ሆኖ ሳይሆን የሩቅ እና ታሪ
ካዊ ጠላቶቹ አላማቸውን የሚያስፈጽሙላቸው ወኔ ቢሶችና ተላላኪዎች በመካከሉ እንዲገኙ በ
ማድረጋቸው፤ በመካከሉ የተገኙ ተላላኪዎችም ትልቁን የኢትዮጵያ ህዝብ ትንሽ ለማድርግ በገበ
ያ ለሽያጭ እንደተደረደረ በግ ዝም ጭጭ ለማድረግ፣ በሱቅ እንደሚቸበቸብ እቃ ዝም ብሎ እነ
ዲቸበቸብ ለማድረግ ቀንና ሌት እየሰሩ በመገኘታቸው ነው፡፡ የቅርቡን እንኳን ብንወስድ የኢት
ዮጵያ ህዝብ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም አገሩን በጭራሽ እንደማያስደፍር ሻቢያ፣ የውጪ መጋቢ
ዎቹና የውስጥ ተላላኪዎቹ በደንብ አይተው ትምህርት ወስደውበታል፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ
መንግስት በሚለወ ደረጃ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ሽብር ተደቅኖበት ከሆነ የመንግስት ድርሻ እው
ነተኛውን መረጃ ለህዝብ በወቅቱና በትክክል የማድረስ ሲሆን አገሩን ከሽብርተኞች የማዳን እና
ሽብርተኞችን አሳዶ የመያዙ ስራ ለራሱ ለህዝቡ የሚተው ነው፡፡ መንግስትን ከኢትዮጵያ ህዝብ
በተለየ ጉትጓች ፣ አልቃሽና አስለቃሽ፣ ቀባሪና መርዶ ነጋሪ የሚያደርገው ነገር የለም፡፡ ይህ የመን
ግስት ተግባር ሊሆን ይችላል፡፡ ደግሞም ነውም፡፡  የመንግስት ተዋጽኦ፣ ማንነትና ምንነት ቁልጭ
ብሎ በሚታወቅበት ኢተዮጵያችን መንግስት ከህዝቡ በላይ ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪው እኔ ስለሆን
ኩ እየመጣችሁ በየምሽቱ በቴሌቪዥን አላቅሱኝ የሚል ከሆነ እለቅሶውን ትቶ ..ልንበላ የፈለግና
ትን አሞራ ቆቅ አላት.. ወደ ሚል ቅኔ መቀየሩ የተሻለ ነው፡፡ መንግስትን የሚያስጠይቀው እያለቀ
ሰ አላቅሱኝ ባለማለቱ ሳይሆን፤ ሽብርን በተመለከተ ትክክለኛውንና ጥርት ያለውን የሽብር መረ
ጃ ለህዝቡ ሳየቀርብ የቀረ እንደሆነ ወይም በሬ ወለደ አይነት መረጃ ለህዝቡ የሰጠ እንደሆነ ብቻ
ነው፡፡ በሌላ በኩል መንግስት የቀረቡለትን የዴሞክራሲ፣ የመልካም አስተዳደር፣ የልማትና የህግ
የበላይነት ጥያቄዎች መፍታትና መልስ መስጠት አቅቶት የሌለ ነገር አለ፣ ያልተደረገ ነገር ተደረ
ገ፣ ያላደገ ሰው አደገ እያለን ከሆነ ይሄም ቢሆን ለኢትዮጵያ ህዝብ ልዩነት የሌለው ከባድ ሽብር
ነው፡፡ ይሄ በኢትዮጵያ ህዝብ በራሱ ላይ በራሱ መንግስት የተለቀቀ ሽብር ይሆናል ማለት ነው፡፡
በመሆኑም አሁን ሽብር እየተባለ የሚባለው ለዚያኛው አላማም ይለቀቅ ለዚህኛው አላማ የኢት
ዮጵያ ህዝብ የለየለት ሽብር ውስጥ ይገኛል ማለት ይቻላል፡፡ በአንድ በኩል በእርግጥም ተጨባ
ጭ ሽብር በትክክለኛ አሸባሪዎች ተለቆብናል ወይም ደግሞ በሌለ እና መኖሩንም ለማሳየት የማ
ይቻል ሽብር በህዝቡ ላይ ተለቆበታል ማለት ነው፡፡ የመንግስት ተቀዳሚ ተግባርና ግዴታውም
በትክክል ኢትዮጵያ ሽብር ውስጥ ሆና ከሆነ ምንም መደባበቅና ማድበስበስ ሳያስፈልግ ለህዝቡ
ማሳወቅ ወይም  እሱ እራሱ ለፖለቲካ፣ ለኢኮኖሚና ለስነ-ልቦና የበላይነት የለቀቀው ሽብር ከሆ
ነም ባስቸኳይ ህዝቡን ይቅርታ መጠየቅና አስፈላጊም ከሆነ ስልጣኑን በመልቀቅ ህዝቡ ወደ ተረ
ጋጋ ልማትና ሰላም እንዲመለስ ማድረግ ይገባዋል፡፡

እሾህን በሾህ፣ ኮሶን በኮሶ

አንድ በሽታ የነበረውን መድሃት ከለመደውና ከተቋቋመው በሽታው ዝም እንደማይባል ይታወ
ቃል፡፡ ለበሽታው ሌላ አዲስና ፍቱን የሆነ መድሃት ይቀመምለታል፡፡ ጨቋኞ ም የነበራቸው ስ
ውር የመጨቆኛ ስልቶች ከከሸፉ ወይም ከተነቃባቸው ሌላ የመጨቆኛ እና የማስፈራሪያ ስልት
እንደሚዘረጉ የታወቀ ነው፡፡ አሁን በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው የተያዙትና ክስ የተመሰረተባቸ
ው ጋዜጠኞችና የፖለቲካ ፓርቲ አባላት የግል ስብዕና እና የተሰማሩበት አላማ የሽብርተኛ ሰው
ባህሪ አይደለም፡፡ ወደ ኋላ እንደምንመለከተው ሽብርተኛ ግለሰቦች የራሳቸው የሆነ የአሸባሪነት
መለያ ባህሪና መገለጫ አላቸው፡፡ አሁን በሽብር ወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎች የሽብርተኛ ድርጊቶ
ችን ቀርቶ የሽብርተኛ ባህሪ እንኳን ሳይኖራቸው ሽብርተኛ ተብለው መወንጀላቸውና መከሰሳቸ
ው ለብዙ መላ ምት የተጋለጠ ነው፡፡ የመጀመሪያው መላምት ጭቆናን ለሚታገለው የኢትዮጵያ
ህዝብ አጠር ያለ እና አጠቃላይ መልእክት ለማስተላለፍ ሊሆን ይችላል የሚል ነው፡፡ መልዕክቱ
ም እናንተ ነፃነት፣ ዴሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደርና የህግ የበላይነት የምትፈልጉ ኢትዮጵያዊያ
ን በሙሉ አይናችሁን ግለጡ፣ ተመልከቱ ሴት አስረናል፣ ወንድ አስረናል፣ ወጣት አስረናል፣ የፖ
ለቲካ ፓርቲ መሪዎችንና አባላትን አስረናል፣ በቀጣይም በየቀኑ ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን
እያሰርን በቴሌቪዥን እናሳያችኋለን፣ ማየት አይሳናችሁ፣ ይሄን ሁሉ ጉድ እያያችሁ ገና ለገና ነፃነ
ት፣ ዴሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደር ያስፈልገናል ትላላችሁ? እንዲህ ያለውንስ ትመኛላችሁን፣
እንዲህ ያለው ምኞት ይቅርባሁ፣ እኛንም ተዉን፡፡ መላ ምቱ ትክክል ከሆነ እኔም አይን ያለው አ
ይኑን ይጠቀምበት፣ ልብም ያለው ልቡን ይጠቀምበት ባይ ነኝ፡፡ ሁለተኛው መላ ምት ደግሞ እ
ነ ዘበርጋ፣ እነ አበበ፣ እነ መልካሙ፣ እነ በርሄ፣ እነ አንሙት... ግንቦት 20 የሚባል ፕሮጀክት ከፍ
ተንላችኋል፣ እነ ጊዳደ፣ እነ ጣፋ፣ እነ ጫላ ደግሞ ኦነግ የሚባል ፕሮጀክት ከፍተንላችኋል፣ ሌላ
ው ቀርቶ ስማችሁ እንኳን ቢደብረን ግንቦት 7 እና ኦነግ ከተባሉት ፕሮጀክቶች ውስጥ ወስደን እ
ንቀላቅላችኋለን ለማለት ይሆናል፡፡ እናም እነ ዘበርጋ፣ እነ ቱል፣እነ አለሙ አትደብሩን፣ በጭራሽ
አትደብሩን ከምንወጣበት ከምንገባበት መንገድ ገለል በሉ ብትፈልጉ ባህር ውስጥ ስጠሙ፣ ብት
ፈልጉ በግርድና ወደ ምትሄዱበት ሂዱ፣ ብትፈልጉ የዱር አውሬ ይብላችሁ፣ ብትፈልጉ ራሳችሁን
አንቃችሁ ግደሉ፣ በቃ ዋናው ነገር እኛን አትደብሩን፣ በአይናችን አንያችሁ፣ ይሄን የማታደርጉ ከ
ሆነ እንደ ምድባችሁ ያው ወደ መደብናችሁ ፕሮጀክት እንልካችኋለን የሚል ይሆናል፡፡ መላ ም
ቱ እውነት መሆኑን ወይም ሀሰት መሆኑን የሚያውቀው እንግዲህ አድራጊዎችና አንድ ፈጣሪ ብ
ቻ ነው፡፡ ለመላ ምቱ ማጠናከሪያ ግን ሁለት መረጃዎች አሉ፡፡ አንድ ልክ እንደ ልማት፣ ልክ እን
ደክትባት፣ ልክ እንደምርምር፣ ልክ እንደ እግር ኳስ ጨዋታ፣ ልክ እንደ በጎ አገልግሎት እስሩ ይ
ቀጥላል ሲል መንግስት ዘና ያለ መመሪያ መስጠቱ ነው፡፡

ሁለተኛው መረጃ ደግሞ አሁን እስር ቤቶቻችን ለዚሁ አላማ እየተመቻቹ መሆኑ ነው፡፡ በፌደራ
ል፣ በአማራ አና በኦሮሚያ መንግስት ስር ካሉ ማረሚያ ቤቶች ውስጥ ከ10 ሺህ በላይ እስረኞች
በምህረት ተለቀዋል ወይም በምህረት ሰበብ ቦታ ለቀዋል፡፡ ይህ የተለቀቀ ቦታ በዋናነት በአማራ፣
በኦሮሚያ እና በፌደራል መንግስቱ ስር ባሉ ማረሚያ ቤቶች የሚገኝ መሆኑ ዜጎች በፖለቲካ ልዩ
ነታቸው የሚማቅቁባቸው ናቸው፡፡ ይሄ መላ ምት ነው፡፡ እውነታው እግዜር ዘንድ ያለ ሲሆን እ
ኛ ደግሞ በጊዜ ሂደት የምናየውና የምናረጋግጠው ይሆናል፡፡ ሶስተኛው መላ ምት እሾህን በእሾ
ህ ለማጥፋት የወጠነው ዘመቻ ነው ሊባል መቻሉ ነው፡፡  ..እሾህን በእሾህ.. በሚለው አባባል በ
ሰው እግር ውስጥ ተሰንቅሮ ሰውን ለሚቆጠቁጠው እሾህ በአለም ላይ ያሉት ሌሎች እሾሆች በ
ሙሉ ጠላቶቹ ናቸው ለምን ቢባል በ..እሾህን በእሾህ.. አባባል ሰው እግር ውስጥ የተሰነቀረውን
እሾህ የሚያወጣው ሌላ እሾህ ስለሆነ ነው፡፡ እና እግር ውስጥ የተሰነቀረ እነ የሰውን ስሜት የሚ
ቆጠቁጥ እሾህ ከራሱ ህልውና አንፃር ሌሎችን እሾሆች ለማጥፋ መሞከሩ ትክክል ባይሆንም ሎ
ጂክ ሊሆን ይችላል፡፡ የሰው እግር ውስጥ የተሰነቀረ እሾህ ገና ለገና የሰዎችን ስሜት መቆጥቆጥ
ይቀርብኛል ብሎ ሌሎችን እሾሆች የማጥፋት መብት የለውም፡፡

እሾህን በእሾህ ስልት የኢህአዴግ እሾህ መድረክ ነው፡፡ መድረክ ከተቋቋመ አጭር ጊዜ ቢሆነው
ምና የታመነበት ጠንካራ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማድረግ ገና ብዙ የሚቀረው ቢሆንም ለእሾሁ
እሾህ መሆኑ ግን በሁሉም ዘንድ የታወቀና የታመነ ሆኗል፡፡ በ2002 ምርጫ በህዝብ አካል እ
ና ስሜት ውስጥ የተሰነቀረውን ኢህአዴግን አሽንፎ የሚያወጣው እሾህ መድረክና መድረክ ብ
ቻ መሆኑ ታይቷል፡፡

ዴሞክራሲያችን ላይ የተሰነቀረው እሾህ ኢህአዴግም ይህን በደንብ አውቆታል፡፡ እናም መድረክ
የሚባል እሾህን የሚያነክት እሾህ የሚቆርጥ መጥረቢያ ማምረት፣ መግዛት ወይም መዋስ ለኢህአ
ዴግና ደጋፊዎቹ እንዲሁም ለጥቅም አጋሮቹ የግድ ሆኖባቸዋል፡፡ እናም እሮብ ከአምኒስቲ ኢንተ
ርናሽናል ጋር የተገናኘ የመድረክ አባልና ድርጅቶች አባልና አመራር ሐሙስ ኦነግ ተባለ፡፡ ቅዳሜ
ወይም እሁድ ጋዜጣዊ መግለጫ የሰጠ የመድረክ አባል እና አመራር ሰኞ ግንቦት ሰባት ተባለ፡፡ አ
ሁን እንግዲህ መጥረቢያው መጥረቢያ ብቻ ሳይሆን በጣም ስለት ማንንም ከመቁረጥና ከማረድ
የማይመለስ የፈሪ መጥረቢያ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሌላው መላ ምት ደግሞ ጨቋኞች ሁሉ ነገር
ሞልቷቸው፣ ኪሳቸው ሞልቶ፣ ሆዳቸው ሞልቶ፣ ቦንብና ፈንጅ ተሸክመው አንድ ነገር ይጎድላቸ
ዋል፡፡ ሃሳብ ይጎድላቸዋል፡፡ ሃሳብ በተለይም ጠቃሚ ሀሳብ፣ ሊለማ የሚች ል ሃሳብ፣ እነደ ፀሐ
ይ ሁሉንም የሚያሞቅ ሀሳብ፣ እንደ ፅጌረዳ አ በባ ሁሉንም የሚያነቃቃ ሃሳብ፣ እንደ መልዓክ ሁ
ሉንም የሚያስማማ ሀሳብ፣ እግዚአ ብሔር የሚወደው ሀሳብ፣ ሰው የሚደው ሃሳብ ለማመንጨ
ት የሚል ጭንቅላት እግዚአ ብሔር ነፍጓቸዋል፡፡ ጨቋኞች እንሸነፋለን ብለው ሁሌ የሚያስቡት
ም በመሳሪያ ሰይሆን በሀሳብ ብልጫ ነው፡፡ ምግብ በደንብ አከማች ተዋል፣ መሳሪያም አከማች
ተዋል፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ሀሳብ የሌላቸው መሆኑና ሀሳብ ያላቸው ሰዎች አንድ ቀን ሊነሱ ይች
ላሉ ብለው  ይሰጋሉ፡፡ እናም እነዚህን የሀሳብ ሰዎች አፈላልጎ ማነቅና ማጥፋት የዘወትር ቅዠታ
ቸው ነው፡፡ ሀሳብ ከሚያፈልቁት ውስጥ ወይም ሀሳብ እንዲፈልቅ፣ ሀሳብ የበላይነት እንዲይዝ ከ
ሚያደርጉት ደግሞ እነዚያ አርፈው የማይተኙት እነዚያ ለህዝብ እና ለትውልድ ጥቅም ሲሉ ራሳ
ቸውን ለአደጋ እና ለስደት፣ ለእስር የሚያጋልጡት፣ ለህዝባቸው ሲሉ የደረሰባቸው ሁሉ ደርሶባ
ቸው ምንም የማይመስላቸው ጋዜጠኞች ይገኙበታል፡፡ ምንም እንኳን ጋዜጠኛውን ጋዜጠኛ አ
ይደለም የሚሉ ባለስልጣናት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን ጋዜጠኛ መሆኑን አናውቅም ቢሉም እን
ደ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ያሉ ጋዜጠኞችንና የሃሳብ ሰዎችን ጨቋኝ ከየትኛውም ህዝብ ጨራሽ
መሳሪያ በላይ ይፈራቸዋል፡፡ ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙን የመሰሉ ሴቶች ከማጀት ወጥተው ለመብ
ታቸው የሚታገሉ ጋዜጠኞችን ጨቋኞች በጣም ይፈራሉ፡፡ ልጅነት ዱሮ ቀረ ብለው በልጅነታ
ቸው ለህዝብ ጥቅም የሚቆረቆሩና የሚደክሙ ጋዜጠኛ ውብሸት ታየን የመሰሉ ወጣት ጋዜጠኞ
ችን ጨቋኞች በጣም ይጠላሉ፡፡ እኒህንና የመሳሰሉ  ወጣት ጋዜጠኞች የብዕር ቋንጃ በቶሎ ካል
ተቆረጠ ጨቋኞች አለቀልን ብለው እንደ ተወጋ አውሬ ይደነብራሉ፡፡ እናም እነዚህን ሃሳብ አሳ
ዳጅ ጋዜጠኞች ሰዶ ከማሳደድ በልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች አማካኝነት ወደ ቃሊቲ መላክ ምርጥ የመ
ሰንበቻ ዘዴ ሆኖ አግኝተውታል፡፡ ይሄም መላ ምት ነው፡፡ እውነታው እገዚአ ብሔር ዘንድ ቁል
ጭ ብሎ አለ፡፡ እኛ ደግሞ ጊዜው ሲደርስ መላምቱ እውነት ነው ሀሰት ነው የሚለውን እናያለን፡፡
እንግዲህ እኔም በዚሁ ማፈር ልልመድና የጽሑፉን እርዕስ አንድም ጊዜ ሳልነካ እዚህ በመድረሴ
በጣም አፍሬአለሁ፡፡ በሚቀጥለው ሳምንት ግን ስራዬ ሁሉ እርዕሱ ላይ ይሆናል ብዬ ተስፋ አደ
ርጋለሁ፡፡ ቁም ነገሩ ግን የሳምንት ሰው መሆኑ ላይ ነው፡፡

# ስለ ደበበ እሸቱ

ከወንድወሰን አንድአርጋቸው
(ለመመረቂያ ካዘጋጀሁት ሥራ የተቀነጨበ) 2001 ዓ/ም አዲስ አበባ

ደበበ እሸቱ በኢትዮጵያ ተወልዶ ባህላዊ የሆነውን ትምህርቱን ተከታትሎ፤ ትምህርቱን በቀጣይ በተፈሪ መኮንን ት/ቤት እስከ 10ኛ ክፍል ድረስ ተከታትሎ ከአስረኛ ክፍል ወደ ኢትዮጵያ ዓየር ኃይል ለመግባት የሚወሰደውን ፈተና ተቀብሎ በማለፉ ወደ ዓየር ሃይል ሄደ፡፡

ተፈሪ መኮንን በሚማርበት ጊዜ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን አጫጭር ጭውውቶችን በየሚደርስባቸው ክፍሎች ያቀርብ ነበር፡፡ እስከ ስምንተኛ ክፍል ትምህርቱን ተከታትሎ የአንደኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና በወሰደበት ጊዜ፤የመሰነባበቻ ፕሮግራም በትምህርት ቤቱ ይዘጋጅ ስለነበር፤ ደበበም በዚህ ወቅት ነው የመጀመርያውን የመድረክ ሙሉ ቴአትር በትምህርት ቤት ደረጃ ለተማሪዎች ሲዘጋጅ የሴት ባህሪ ወክሎ እንዲጫወት ተመርጦ የተጫወተው፡፡ከዚያ ለጥቀው በነበሩት የትምህርት ዘመናት ከቴያትር ጋር በቀጥታ ባይገናኝም በትምህርት ቤቱ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች ቴአትር በሚዘጋጅበትና በሚቀርብበት ጊዜ ከአካባቢው አይጠፋም ነበር፡፡

ወደ ዓየር ሃይል ከገባም በኋላ በዓየር ኃይል ግቢ ቴአትር ለማዘጋጀትና ለማቅረብ እንደሚፈልግ በጊዜው የዕጩ መኮንኖች የመዝናኛ ሃላፊ ከሆኑት ከመቶ ዓለቃ በቀለ እንዳይላሉ ጋር ተመካክሮ አንድ ቴአትር ከጓደኞቹ ጋር አዘጋጅቶ በማቅረብ በወቅቱ ከሃላፊዎቹ ምስጋና፤ ከጓደኞቹ ደግሞ መወደድን አትርፏል፡፡

ዓይር ኃይልን ለቆ ከወጣ በኋላ በፖስታ ቤት ተቀጥሮ ለአንድ ዓመት ሰርቶ በኋላም ወደ ደብርብርሃን መምሕራን ማሰልጠኛ ት/ቤት ለመግባት የሚያበቃውን ፈተና ወስዶ በማለፉ ወደዚያው ሄዶ ትምህርቱን ተከታትሏል፡፡

ወዲያው በትምህርት ቤቱ ውስጥ ክበቦች ሲቋቋሙ የመዝናኛ ክበብ ሃላፊ ሆኖ በመመረጥ የፎቶግራፍ ክበብ፤የስነጽሁፍ ክበብ፤የቴአትር ክበብ በማዋቀር አባላት አሰባስቦ ከአባላቱ ጋር በርካታ ስራዎች ለመስራት ችለዋል፡፡

በዚህ አጋጣሚ ነው ደበበ ትኩረቱን ወደ ቴአትር በማድረግ በርካታ የመዝናኛ ጭውውቶች፤ብቻውን የሚያቀርባቸው ትርኢቶች ራሱ በመጻፍና በመተወን ከመምህራን ማሰልጠኛ ት/ቤት ውጪም ለደብረብርሃን ነዋሪዎችም ትርኢቱን በቅድሚያ በነጻ፤ ለጥቆም አነስተኛ ክፍያ በማስከፈል ገቢውን ለፎቶግራፍ ማተሚያ ወረቀትና ለመሳሰሉት መግዣ፤ለአዳራሽ መከራያ እንዲውል ያደርግ ነበር፡፡ በዚህም እንቅስቃሴው ደበበ የማሰልጠኛው የእጩ መምህራን ፕሬዜዳንት ሆኖ ተመረጠ፡

በወቅቱ ት/ቤቱ በጀት ያገኝ የነበረው ከአሜሪካን መንግሥት ነበርና ለተማሪዎች የሚገዛውም ልብስ ራንግለር በመባል ይታውቅ የነበረው ጂንስ ሲሆን በምግብም በኩል በጣም ከፍተኛ ደረጃ የነበረው አቅርቦት ነበረው፡፡እየቆየ ሲሄድ ምግቡም ደረጃው እየወረደ፤ ልብሱም ከጂንስ ወደ ካኪ በመውረዱ ተማሪው አቤቱታ አቀረበ፡፡አስተደደሩ ጥያቄውን አልቀበልም በማለቱ ተማሪው ለአቤቱታ ከደብረ ብርሃን አዲስ አበባ በእግሩ ጉዞ ጀመረ፡፡ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ጉዳዩን ለደብረብርሃን ገዢ በማሳወቁ ለመመለስ ክትትል ቢደረግም ሳይሳካ ቀረ፡፡ጉዞውን ለመቀጠል አቅም ያጡትና የደከሙትም ጨለማን ተገን አድርገው ወደ ደብረብርሃን ቢመለሱም ወደ ትምህረት ቤቱ ቅጥር ግቢ ሳይገቡ አዲስ አበባ የሄዱትን ጓደኞቻቸውን መመለስ ሲጠብቁ ቆይተው ሲመለሱ ተቀላቅለው ነው የገቡት፡፡

ይህም በተማሪዎቹ፤በአስተዳደሩና በደብረብርሃን ገዢ መሃል ቁርሾ ፈጠረ፡፡በ1953 ዓ/ም በተሞከረው መፈንቅለ መንግሥት ከእድሜያቸውም ማነስና በግቢው በነበሩም መምህራን ግፊት ተማሪዎቹ እንቅስቃሴውን እንደግፋለን በማለት በጠዋቱ የጸሎትና የሥነስርአት ፕሮግራም ላይ ላለመገኘት ወስነው አመጽ አደረጉና ይህም ሌላ ቅሬታ ፈጠረ፡፡የዚህን አመጽ መሪዎች በማለት የትምህርት ቤቱ አስተዳደር መርጦ መዘገበ፡፡ከጥቂት ወራት በኋላ ተማሪዎች የመጨረሻውን ዓመት ፈተና ወስደው ሊመረቁ 1 ሳምንት ሲቀራቸው የታህሳሱን ድርጊት አስተባብረዋል በመባል የተመዘገቡት 10 ተማሪዎች ድንገት ከግቢው በፖሊሶች ተይዘው ወደ ተለያየ ቦታ ተወሰዱ፡፡ ደበበም ኢሉባቦር ተመደበ፡፡ኢሉባቦር ክፍለ ሃገር ዋና ከተማ ጎሬ ደርሶ በእስር ደረጃ ጠዋት፤ ቀን፤ ማታ እንዲፈርም ግን በአስተማሪነትም አገልግሎት እንዲሰጥ ተብሎ በወር 70 ብር እየተከፈለው ለጥቂት ወራት ከቆየ በኋላ፤ ወደ መቱ ተዛውሮ ከዚያ በሚሰጠው መሸኛ፤ ዱረኒ ወደተባለ ስፍራ እንዲሄድ ቢወሰንም በወቅቱ ያጋጠመው ውሃ ሙላት ድልድዩን ስለሰበረው ለመሄድ ባለመቻሉ፤ በመቱ የትምህርት ቤቶች ጽ/ቤት ሃላፊ በአቶ ታደሰ ላፍቶ ውሳኔ የሳቸው ጸሃፊ ሆኖ እንዲሰራ ሆኖ፤ ከፊል ጊዜውንም በማስተማር አሳለፈ፡፡

ደበበ በአንድ አጋጣሚ ከኢሉባቦር ወደ አዲስ አበባ ከመጣ በኋላ ነው በአዲስ አበባ ዮኒቨርሲቲ በተጀመረው የቴአትር ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ቤት ኪነጥበባት ወቴአትር ገብቶ ስልጠና የጀመረው፡፡ ቤተኪነጥበባት ለሁለት ዓመታት ትምህርቱን ከተከታተለ በኋላ ለሙከራ የተመደበው ገንዘብ በማለቁ የተነሳ በትምህርቱ ሳይመረቁ በመቋረጡ በግል አፈላልጎ በተገኘው የውጭ ትምህርት ዕድል ከጓደኛው ከወጋየሁ ጋር ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ቡዳፔስት ለመሄድ ቻሉ፡፡

ከቡዳፔስት መልስ ለጥቂት ጊዜያት ሥራ ቢያጡም በግላቸው በተለያየ ቦታ በመዘዋወር ትርኢት ከማቅረብም አልፈው በቴሌቪዥን አዲስ የመዝናኛ ፕሮግራምና እንዲሁም ተውኔቶች በማቅረብ ተወዳጅነትንና ዝናን ማትረፍ ችለዋል፡፡ ወጋየሁና ደበበ በሚያቀርቧቸው ትርኢቶች አዲስ የቴአትር ጥበብ በር ከፍተዋል፡፡ በተለይም ፓንቶማይም የተባለውን የእንቅስቃሴ ድምጽ አልባ ትርኢት በማቅረብ ቀደምት ቦታውን ይይዛሉ፡፡ ከዚያ በፊት የፓንቶማይም ትርኢት አይታወቅም ነበርና አንድ ጊዜ ከጀመሩት በኋላ መታወቂያቸው ሆነ፡፡

ይህንና ሌላም ጥበባዊ ተግባር ሲያከናውኑ ቆይተው ደበበና ወጋየሁ በስተመጨረሻው ወደ ኢትዮጵያ ሬዲዮ በመግባት የሬዲዮ ተውኔት ፕሮግራም ማዘጋጀት፤ ማቅረብና መምራትን ቀጠሉ፡፡ከዚሁ ጋር በተያያዘም ደበበ ዜና ማንበብና የመዝናኛ ሙዚቃዎችን ማቅረብ ቀጠለና ፕሮግራሞቹም ተወዳጅ እየሆኑ ስምና ዝናም እየጨመረ መጣ፡፡

ኢትዮጵያ በመላው የጥቁር ሕዝቦች በዓል አልጄርያ በተጓዘበት ወቅት ደበበና ወጋየሁም የቡድኑ አባላት ሆነው እንዲጓዙ በመመረጣታቸው ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ከጥቂት ዓመታትበኋላ ሁለተኛው በዓልም በናይጄርያ ሲከበር ተሳታፊ ነበሩ፡፡ በሁለቱም ቦታዎች አኩሪ ተጋበር መፈጸማቸውን በወቅቱ አብረዋቸው የተጓዙት ይመሰክራሉ፡፡

ደበበ በሃገር ውስጥ ካለው ታዋቂነትና ለሙያው ካደረገው አስተዋጽኦ ለመጠቀስ ያህል

<u>በመድረክ ላይ</u>

በቤተኪነጥበባት ወቴአትር

| | |
|---|---|
| ያላቻ ጋብቻ | ተዋናይ |
| ሮሚዎባ ዡልየት | ተዋናይ |
| ጠልፎ በኪሴ | ተዋናይም አዘጋጂም |
| ዳንዴው ጨቡዴ | ›› |
| ዘ ጌም ኦፍ ቼዝ (በእንግሊዝኛ) ተዋናይ | |
| ኦቴሎ (በአንግሊዝኛ) | ተዋናይም አዘጋጂም |
| ኦዳ ኦክ ኦራክል (በእንግሊዝኛ)ከሎ.ጸ.ገ.መ | ተዋናይ |

<u>በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ(ብሔራዊ) ቴአትር</u>

| | |
|---|---|
| የበጋ ሌሊት ራዕይ | ተዋናይ |
| አንድ ዓመት ከአንድ ቀን | ተዋናይ |
| እናት ዓለም ጠኑ | ተዋናይ |
| ኪንግ ሊር | ተዋናይ |
| ዋናው ተቆጣጣሪ | ተዋናይ |
| ጠያቂ | ተዋናይ አዘጋጅ |
| በቀይካባ ስውር ደባ | አዘጋጅ |
| ተሓድሶ | አዘጋጅ |
| የአዘውንቶች ክበብ | አዘጋጅ ተዋናይ |

በሃገር ፍቅር ቴአትር

| | |
|---|---|
| ጠልፎ በኪሴ | አዘጋጅ/ተዋናይ |
| የወፍ ጎጆ | ተዋናይ |
| ኪንግ ሊር | ተዋናይ |
| የቬኒሱ ነጋዴ | ተዋናይ |
| ናትናኤል ጠቢቡ | ተዋናይ |
| ድብልቅልቅ | ተርጓሚ/ ተዋናይ |
| ማዕበል | ተርጓሚ አዘጋጅ |

<u>በፊልም በሃገርና በዓለም አቀፍ</u>

ዘ ሴይለር ፍሮም ጂብራልታር
ሻፍት ኢን አፍሪካ
ጉማ
ዚ አፍሪካን ስፓይ
ዜልዳ
አፍሪካ
ዘግሬቭ ዲገር

ዘ ግሬት ሪቤሊየን

እነዚህ ለምሳሌ ያህል የቀረቡ ናቸው እንጂ የደበበ ስራዎች በጣም ብዙ ናቸው፡፡ ደበበ ከመድረክና ፊልም ስራዎቹ ባሻገር ተማሪዎችም አሰልጥኗል፡፡ ሎሬት ጸጋዬ ገብረመድህን በብሔራዊ ቴአትር የተዋንያን ስልጠና ማዕከል ሲያቋቁሙ ከመምሃራኖቹ መሃልና በግምባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው መምህር ደበበ ሲሆን ለተማሪዎቹም መማርያ እንዲሆን የተረጎመው የስታንስላቭስኪ የተዋናይ ሀሁ ለበርካታዎች የሙያ ተማሪዎች የሙያቸው ፊደል መቁጠርያ ሆኖ ይገኛል፡፡

<u>በትርጉም በኩልም ደበበ ከቴአትር</u>
ያልታመመው በሽተኛ
ድብልቅልቅ
ጎርፉ

<u>ከመጽሐፍ ደሞ</u>
የዳዊት ወልደጊዮርጊስን
የደም እንባ

<u>የራሱን ወጥ ሥራ በተመለከተ</u>
የእምነቴ ፈተና
ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው

ደበበ ለአፍሪካ ጥበብ ያለውን አመለካከትና ግንዛቤ ከቅኝ ገዢዎች ትርጓሜ ለማውጣትና ሶስተኛው ዓለም ኋላ ቀር ሲባልም በኤኮኖሚና በቴክኒዮሎጂ እንደሆነ፤ ይህም የሆነው ነጩ የአፍሪካን የዋህነት፤ እንግዳ ተቀባይነትና ሩህሩህነት መንጠላጠያ በማድረግ ቅኝ አድርገው ህሊናውን ስለዘጉበትና ስላሰሩት መሆኑን፤በባህል በኩል ግን ጨርሶ ሊደርሱበት የማይችሉትና ሊያጠፉትም ያደረጉት ሙከራ ዋጋ ቢስ ሆኖ እንደቀረ የሚያስረዳ ጥናታዊ ጽሁፍ በማቅረብ ተቀባይነትን አግኝቶ ድል ያደረገና፤ ቀደም ሲል የጀመረውን ትግል አጠናክሮ በመቀጠል በ1985 ዓ/ም እንደ አውሮፓውያን ቆጣጠር በርሊን ላይ በተካሄደው የዩኔስኮ የባህል(አይ ቲ አይ) ኢንተርናሽናል ቴአትር ኢኒስቲቲዩት ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያን ወክሎ በመገኘት  በአፍሪካ ውስጥ የመጀመርያው ፕሮፌሽናል ቴአትር ቤት የሃገር ፍቅር ቴአትር መሆኑን በማስረጃ አስደግፎ ተቀባይነትን አገኘ፡፡ በዚሁ ዓመት የዩኔስኮ የባሕል ክፍል አይ ቲ አይ  የአፍሪካ ተጠሪ ሆኖ በመመረጥ፤ በዚያው ዘመን ዝምባብዌ ላይ በሚካሄደው ቴአትር ለልማትና ዕድገት ወርክሾፕ ላይ በመሪነት እንዲገኝ በዩኔስኮ ተወክሎ በመሄድ ወርክሾፑን በአጥጋቢ ችሎታውና የአመራር ብቃቱ ከመፈጸሙም ባሻገር ለብዙ ጊዜ ተሞክሮ ሲወድቅ ሲነሳ የነበረውን የአፍሪካ የመድረክ ባለሙያዎች ማሕበርን አስተባብሮ በማቋቋም የማሕበሩም መስራች ፕሬዜዳንት ሆኖ ለ12 ዓመታት መርቷል፡፡ አሁንም መስራች ፕሬዛዳንት በመባል ይጠራል፡

ደበበ በችሎታውና በብቃቱ በማስተባበር ችሎታው ዩኔስኮ ዓለም አቀፍ የቴአትር ኢንሳይክሎፒዲያን ለማዘጋጀት ሲወስን ደበበንም አፍሪካን በመወከል የኤዲቶርያል ቦርድ አባል አድርጎ መድቦት ሥራውን በሚገባ ተወጥቷል፡፡

ደበበ ቴአትር ለልማትና ለእድገት በሚል የሚታወቀውን የቴአትር ዲሲፕሊን ስልጠና ለበርካታ ሃገራት ባለሙያዎች ያስተማረ ሲሆን በርካታ ወርክሾፖችም በየሃገራቱ እየተጋበዘ መርቷል፡፡ ይህን ዘዴ ካዋቀሩትም አምስት አፍሪካዊ ባለሙያዎች አንዱ ደበበ ነው፡፡

ወርክሾፕ የሰጠባቸው ቦታዎች፤

ታንዛኒያ፤ኡጋንዳ፤ኬንያ፤ማላዊ፤ኮንጎ  ብራዛቪል፤አይቮሪ  ኮስት፤  ካሜሩን፤  ናይጄርያ፤አይርላንድ፤ብራዚል፤ሰሜን አሜሪካ፤እንግሊዝ፤ ኩባ፤ በርሊን፤ካናዳ ይገኙበታል፡፡

ደበበ ላለፉት ከ40 በላይ ዓመታት በቴአትር ጥበብ ውስጥ ኖሮ በ1995 በተካሄደው ሃገራዊ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውስጥ «ቀስተደመና» የፖለቲካ ፓርቲን ተቀላቅሎ፤ በኋላም ቅንጅት ሲፈጠር የምክር ቤት አባልና የሕዝብ ግንኙነት በመሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገ ቅንጅትን ለድል ያበቃ፤ የሬዲዮና  የቴሌቪዥን ዝግጅቶቹ ገዢውን ፓርቲ ያንበረከኩና ቅንጅትና ያገዘፉ ነበሩ፡፡በዚህም ከሌሎች አመራሮች ጋር ለአንድ ዓመት ከአስር ወራት ለእስር ተዳርጓል፡፡

ከእስርም ከተፈታ በኋላ ፓርቲው በመደበው መሰረት ወደ ካናዳ ተጉዞ ከም/ሊቀመንበር ብርቱካን ሚዴቅሳና ብቻውንም በርካታ ቦታዎች በመዘዋወር ከፍተኛ ግምት የተሰጠውና አንቀላፍቶ የነበረውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ተመልሶ እንዲነቃና እንዲንቀሳቀስ በማድረግ  በቂ  ባለሙያ ለመሆኑ ሁሉም መስክረውለታል፡፡

ደበበ ፓርቲውን ወክሎ በደረሰበት ቦታ ሁሉ ከታዳሚው ይቸረው የነበረው ከበሬታ፤ በሙያው ካገኘው በተጨማሪ በፖለቲካው መንደር ገብቶ አስፈላጊውን መስዋዕትነት ለመክፈል የቆረጠና፤ እራሱን ነጻ በማውጣት ለሌሎች ነጻነት ለመታገል የወሰነ፤ የወገን ጉዳት የተሰማው፤የወገን ብሶት ያሳመመው፤የወገን ፍትሕ ማጣት ያሸማቀቀው፤ለሃገርና ለወገን ነጻነት በቆራጥነት ከቆሙ የትግል አጋሮቹ ጋር ለመቆም ወኔ ያለው የጥበብ ብቸኛ አርበኛ በመሆኑም ጭምር ነበር፡፡

በሱ ሙያ የተሰለፉ «አይተነው ጊዜ» ሲሉ እሱ ግን «እኔም ድርሻ አለኝ» በማለት ቤተሰቡን፤ ምቾቱን፤ ተድላውን፤ ሁሉ ችላ በማለት ከግል ይልቅ ለህብረተሰቡ፤ ከራሱ ይልቅ ለወገኑ በመወገን የተሰለፈ ብቸኛ የጥበብ ሰው ነው፡፡አንዳንዶች ሹመትና ገንዘብ ሲያታልላቸው፤ እሱን ያታለለው ግን ነጻነት ፍትህና ዴሞክራሲ ከሰብአዊ መብት መከበር ጋር ነው፡፡ለዚህም ነው ከማንም በላይ ሕዝባዊ የክብር ዘውድ የተደፋለት፡፡ ዛሬ ያንን ዘውድ ደፍቶ ባናየውም ታሪክ ግን እንዳለበሰው ይኖራል አንድ ቀን ይህም ይፉ ሆኖ ይከበራል፡፡

ደበበ በሃገሩ ለመሸለም ባይበቃም በዓለም አቀፍ ደረጃ ግን ለሽልማቶች የበቃ ባለሙያ ነው፡፡ለዚሁ የሙያ አስተዋጽኦ ክፍተኛው ክብሩ በአትላንታ ጆርጂያ ኖቬምበር 24 የደበበ እሸቱ ቀን ተብሎ እንዲሰየም የከተማው ምክር ቤት ማጽደቁ ነው፡፡

ደበበ ባለትዳር ከሚወዳትና ከሚያከብራት የችግርና የደስታ መንትያው አልማዝ ደጀኔ ጋር የአራት ልጆች ለጊዜው የአምስት የልጅ ልጆች ያፈሩ የ36 ዓመታት የሚቀናባቸው ባልና ሚስት ናቸው፡፡

## <u>ከአዘጋጁ</u>

**ይህ አንጋፋ አርቲስት እና ትንታግ ፖለቲከኛ ከጳጉሜ 4 ቀን 2003 ጀምሮ ተጠርጣሪ አሸባሪ ተብሎ በማዕከላዊ እስር ቤት እየተሰቃየ ይገኛል።**

# ዜናዎች

## አርቲስት ደበበ እሸቱ የታሰረው በፃፈው ፅሁፍ እንደሆነ ኢትዮ ቻናል ጋዜጣ ዘገበ

በሚያወጣቸው ፅሁፎች የመንግስት ደጋፊ እንደሆነ የሚገልፀው ኢትዮ ቻናል ጋዜጣ አርቲስት ደበበ እሸቱ የታሰረው በሽብርተኝነት ሳይሆን ጳጉሜ 4 ቀን በወጣው ጋዜጣ ላይ በላከው ጽሁፍ መንግስት ቀድሞ መረጃ ደርሶት እንደሆነ ምንጮች ጠቅሶ ቅዳሜ መስከረም 6 ቀን 2004ዓ.ም ባወጣው እትሙ ላይ ገልጿል፡፡
አንጋፋ አርቲስት እና ታዋቂ ፖለቲከኛ የሆነው ደበበ እሸቱ በተያዘበት እለት የመንግስት ኮምኒኬሽን ጉዳዮች ምክትል ሚኒስትር እና ረዳት ኮሚሽነር ደበላሽ ገ/ሚካኤል በሰጡት መግለጫ አርቲስት ደበበ የታሰረው ከግንቦት 7 ጋር ግንኙነት እንዳለው፤ መንግስት ለወራት ተከታትሎ ስለደረሰበት እና በቂ ማስረጃ ስለሰበሰበበት ነው ቢሉም ኢትዮ ቻናል ጋዜጣ ግን በተጠቀሰው ቀን እትሙ ..መንግስትም፣ ተቃዋሚዎችም ይህችን አገር ለመታደግ መፍትሄ ሊያመጡ ይገባቸዋል.. በሚል ርዕስ ስር ባሰፈረው ፅሁፍ አርቲስት ደበበ እሸቱ የታሰረው በፃፈው ፅሁፍ እንደሆነ ምንጮቼ ነገሩኝ ሲል የመንግስትን ውንጀላ አጋልጧል፡፡
በርካታ ሰዎች አፍቃሪ ኢህአዴግ የሆነውን ኢትዮ ቻናል ጋዜጣን ዋቢ በማድረግ መንግስት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙን፣ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬን እና የመሳሰሉትም የታሰሩት አሸባሪ ሆነው ሳይሆን በፃፉት ፅሁፍ እንደሆነ አስተያየታቸውን ለፍትህ ገልፀዋል፡፡ በቀጣይም ከመንግስት አካባቢ ታማኝ ምንጮች ያሉት ኢትዮ ቻናል ጋዜጣ እነ እስክንድር ነጋ በግፍ መታሰራቸውን እንደሚያጋልጥ ተስፋ እንዳላቸው ለፍትህ ጨምረው ተናግረዋል፡፡

## “ህዝብን የሚያሸፍብር ሁሉ እርሱ ራሱ በማያቋርጥ ፍርሃትና ሽብር የተዋጠ ነው” አንድነት
## “የኢትዮጵያን ህዝብ የለውጥ ፍላጐት የዴሞክራሲ ታጋዮችን በማሰር አይገታም” ብአዴፓ

አንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ ፓርቲ /አንድነት/ ሽብርተኝነት የንፁሃንን ህይወት በጅምላ የሚያጠፋ፣ አካልን የሚያጐድል፣ የሀገር ሀብት፣ የልማት አውታሮችና ተቋማትን የሚያወድም ኃላፊነት የጎደለው ተግባር በመሆኑ ፓርቲው እንደማይቀበለው አርብ እለት በጽሕፈት ቤቱ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ገለፀ፡፡ በተመሳሳይም በሽብርተኝነት ስም ሽብርን የሚነዛ አካልን ፓርቲው አጥብቆ እንደሚቃወምም ተናግሯል፡፡
መስከረም 3ቀን 2004ዓ.ም የፓርቲው ም/ል ሊቀመንበር እና የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ በሆኑት አቶ አንዱአለም አራጌ እና የብሔራዊ ምክር ቤት አባላት አቶ ናትናኤል መኮንን እና በአቶ አሣምነው ብርሃኑ ላይ የተወሰደው የእስር እርምጃ ኢህአዴግ የሽብርተኝነት አዋጁን ዜጐች በመንግስት ላይ የሚያነሱትን ህጋዊና ሰላማዊ ተቃውሞ ማፈኛ ዋና መሳሪያ እና መገልገያ አድርጎታል ሲል ፓርቲው ተቃውሞውን በመግለጫው አሰምቷል፡፡
በተጨማሪም ብርሃን ለአንድነት እና ለዴሞክራሲ /ብአዴፓ/ መስከረም 6 2004ዓ.ም የኢትዮጵያ ህዝብ ያለውን ፍላጎት የዴሞክራሲ ታጋዮችን በማሰር አይገታም በሚል ርዕስ ባወጣው መግለጫ ላይ ..የፀረ-ሽብር ህጉን በመንተራስ ሽብርተኛ ናቸው የተባሉ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች፤የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች እና ታዋቂ ግለሰቦች የብሔራዊ መረጃ እና የፀረ-ሽብርተኝነት ግብረ ኃይል ረዥም ጊዜ ሲከታተል መቆየቱን እና ለሽብር ተግባር ሲንቀሳቀሱ እንደነበር የሚገልጽ መረጃ እና ማስረጃ በእጁ እንደገባ እየገለፀ በሌላ በኩል ግለሰቦችን ለፍርድ የሚያቀርበው ፖሊስ የምርመራ ጊዜውን አ ለመጨረሱን ለፍርድ ቤት በማሳወቅ የሚገኝበት ሁኔታ ግልፅ ያልሆነ እና የሚጋጭ ትንተና በመሆኑ ጭምር የግለሰቦቹ ሽብርተኛ መባል የበለጠ ታማኝነትን ያሳጣዋል.. ሲል በመግለጫው ላይ ገልፆአል፡፡
በመጨረሻም ፓርቲዎቹ የታሰሩት ሰዎች በአስቸኳይ እንዲፈቱ መንግስትን በመግለጫቸው ጠይቀዋል፡፡

## የእስክንድር ነጋ ባለቤት መኪናዋ አሁንም በፖሊስ እንደተያዘ እንደሆነ ገለፀች

መስከረም 3 ቀን 2004ዓ.ም በአሸባሪነት ተጠርጥሯል ተብሎ በፌደራል ፖሊስ ተይዞ የታሰረው ታዋቂው ጋዜጠኛ እና የፖለቲካ ተንታኝ እክንድር ነጋ ባለቤት ጋዜጠኛ ሥርካለም ፋሲል መኪናዋን ፌደራል ፖሊስ እንዲመለስላት ብትጠይቅም ..እምናጣራው ስላለ አጣርተን ሳንጨርስ አንመልስም.. ማለቱን በተለይ ለፍትህ ገለፀች፡፡
እንደ ሥርካለም ገለፃ በወቅቱ እስክንድር መኪናውን ይዞ የነበረ ቢሆንም፤ የመኪናው ባለቤት ግን እሷ መሆኗን ሊብሬውን ለፌደራል ፖሊስ አባላት ብታሳይም ..ከአንቺ እጅ አልተያዘም አጣርተን ነው የምንመልሰው.. በማለት መኪናውን ለመስጠት ፍቃደኛ አልሆኑም፡፡
ከዚሁ ጋርም ተያይዞ እስክንድር ነጋ ከተያዘበት እለት ጀምሮ ባለቤቱም ሆነች የህግ ባለሙያዎች ሊያዩት እንዳልቻሉ እና በምን ደረጃ ላይ እንዳለ አለመታወቁ ስጋትን እንደፈጠረባቸው ተገለጿል፡፡

# ጊዜ ለኩሉ
# «እስከ መቼ ድረስ በሁለት አሳብ ታነክሳላችሁ?»
# መጽሐፈ ነገስት ቀዳማዊ ም.18 ቁ.21

መላ እስራኤልን ያስተዳድር የነበረው ንጉስ አክዓብ በቤቱ አጠገብ የነበረውን የናቡቴን የወይን ቦታ ለራሱ ማድረግ ፈልጎ ለናቡቴን እንዲህ አለው ..በቤቴ አቅራቢያ ነውና የአትክልት ቦታ አደርገው ዘንድ የወይን ቦታህን ስጠኝ ስለእርሱም ከእርሱ የተሻለ የወይን ቦታ እሰጥሃለሁ ወይም ብትወድድ ግምቱን ገንዘብ እሰጥሃለሁ፡፡.. ናቡቴም ..የአባቶቼን ርስት እሰጥ ዘንድ እግዚአብሔር ያርቅልኝ.. ሲል የንጉሱን ሀሳብ ተቃወመ፡፡ በዚህ መልስም ንጉሱ ክፉኛ ተናዶ ወደ ቤተመንግስቱ ሲመለስ በርካታ ነብያቶችን እያሳደደች ታስገድል የነበረችው እና ጨካኟ ሚስቱ ኤልዛአቤ የባሏን ማዘን አይታ ..ልብህ የሚያዝን እንጀራስ የማትበላ ስለምንድር ነው?.. ስትል ጠየቀችው፡፡ ንጉስ አክዓብም ናቡቴ የወይን ቦታውን በገንዘብ ወይም በሌላ የእርሻ ቦታ እንዲቀይረው ለምኖት እምቢይ ስላለው መሆኑን ነገራት፡፡ ኤልዛቤልም ..አንተ አሁን የእስራኤልን መንግስት ትገዛለህን? ተነሳ እንጀራም ብላ፤ ልብህም ደስ ይበላት፤ የኢዝራኤላዊው የናቡቴን የወይን ቦታ እሰጥሃለሁ.. ስትል አፅናናችው፡፡

ወዲያውኑም በንጉሱ አክዓብ ስም ደብዳቤ ፅፋ፤ ማህተም አትማበት ስታበቃ ከናቡቴ ጋር ተቀምጠው ወደ ነበሩት ሽማግሌዎች እና ከበርቴዎች ደብዳቤውን ላከችው፡፡ ያች ሴት በደብዳቤው ላይ የፃፈችው መልእክት እንዲህ የሚል ነበር ..ስለፆም አዋጅ ንገሩ፤ ናቡቴንም በህዝብ ፊት አስቀምጡት፤ ሁለትም ምናምቴ ሰዎች በፊቱ አስቀምጡና፡- እገዚአብሔርንና ንጉሱን ሰድቦአል ብለው (በሀሰት) ይመስክሩበት፤ አውጥታችሁም እስከሞት ድረስ ውገሩት፡፡.. ትእዛዙ የተላከላቸው ሽማግሌዎች እና ከበርቴዎችም ኤልዛቤል እንዳዘዘቻቸው የፆም አዋጅ ነገሩ፤ ናቡቴንም በህዝብ ፊት አስቀመጡት ሁለት ምናምንቴ (የሀሰት) ሰዎችም በፊቱ ገብተው ተቀመጡ፡፡ ከዚያም እንዲህ ሲሉ በሀሰት መሰከሩ ..ናቡቴ እገዚአብሔርን እና ንጉሱን ሰድቦአል፡፡.. ከዚህ በኋላም ናቡቴን ከከተማው አውጥተው እስኪሞት ድረስ ወገሩት፡፡

ወደ ኤልዛቤልም ናቡቴ መሞቱን የሚናገር መልእክተኛ ላኩ፡፡ ኤልዛቤልም የምስራቿን ከሰማች በኋላ ንጉሱን ..ናቡቴ ሞቶአል፤ እንጂ በህይወት አየደለምና በገንዘብ ይሰጥህ ዘንድ እንቢ ያለውን የኢይዝራኤላዊውን የናቡቴን የወይን ቦታ ተነስተህ ውረስ.. አለችው፡፡ አክዓብም ናቡቴ እንደሞተ በሰማ ጊዜ ይወርሰው ዘንድ ወደ ኢዝራኤላዊው ወደ ናቡቴ ወይን ቦታ ሊወርድ ተነሳ፡፡ (መጽሐፈ ነገስት ቀዳማዊ ም.20)

ይሄ የንጉስ አክዓብ እና የክፉ ሚስቱ ድርጊት ዛሬም በተለያዩ የአለማችን ክፋት በተግባር እያየነው ነው፡፡ ዛሬ እንደ አይጥ በስርቻ ውስጥ ተደብቀው የሚገኙት እና አምባገነን የሊቢያ ገዥ የነበሩት ጋዳፊ የሊቢያውያን የጭቆና አገዛዛቸው አስመርሮአቸው ለተቃዋሞ በወጡ ጊዜ ..አንዴ አልቃይዳ ናቸው.. ሌላ ጊዜ ደግሞ ..ሀሽሽ ያጨሱ ህገወጦች ናቸው.. በማለት የሀሰት ውንጀላ በመፍጠር ህዝባዊውን ተቃውሞ ለማፈን ያልፈነቀሉት ድንጋይ እንዳልነበረ ያየነው ሃቅ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ይሄው ተመሳሳይ ውንጀላ እየተያ ነው፡፡ መንግስትን የሚተች ጋዜጠኛ ወይም በሰላማዊ መንገድ የመንግስት ለውጥ እንዲመጣ የሚቀሰቅስ ህጋዊ ፖለቲከኛን ..አሸባሪ.. የምትባል የሀሰት ውንጀላ እየለጠፉ እስር ቤቱን እያጨናነቁ ነው፡፡ መንግስት ..አሸባሪ ናቸው.. ሲል ለሚወነጅላቸው ጋዜጠኞች እና ፖለቲከኞች እስከ አሁን እያቀረበ ያለው የኤልዛቤልን ምስክሮች ነው፡፡ እነዚህ መስካሪዎችም ያለ አንዳች ህፍረት ..ናቡቴ እግዚአብሔርን እና ንጉሱን ሰድቦአል.. እንዳሉት አይነት ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ፡፡ አክዓብ የወይን እርሻውን ሊሸጥለት ያልፈቀደውን ናቡቴን የአስገደለው በሚስቱ መላ ነው፡፡ ሚስቱ ኤልዛቤል ..ናቡቴ ለባሌ መሬት አልሸጥም.. አለ ስትል አይደለም የከሰሰችው፡፡ እንዲህ ብላ ቢሆን የከሰሰችው በህዝቡ እና በችሎቱ ተቀባይነት ስለማይኖረው የሀሰት ክስ ፈጥራበታለች ..እግዚአብሔርን እና ንጉሱን ተሳድቦአል.. ስትል፡፡ ህጋዊ ፖለቲካኞች ወይም በጋዜጠኛነታቸው ሳይሆን ..አሸባሪ.. እየተባሉ ነው፡፡ ልክ ኤልዛቤል በተጓዘችበት መንገድ አይነት ማለት ነው፡፡

ኤልዛቤል ከናቡቴ በሽገርም በርካታ ነቢያቶችን በማስገደል ትታወቃለች፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት በአብዛኛው አለም የሚተዳደረው በህገ ልቦና እንጂ በህገ መንግስት አልነበረም፡፡ እናም ሚዲያ የሚባል ነገር ባለመኖሩም ነገስታቶች ሲያጠፉ አንድም ከስህተታቸው እንዲመለሱ፤ እማይመለሱም (የማይታረሙ) ከሆነም የእግዚአብሔር ቅጣት የሚላከላቸው በነብያቶች ነበር፡፡ እነዚህ ነብያቶች ጨካኝ እና ሀያል የነበሩትን ገዥዎች ሳይፈሩ ..ፍትህን አጓድለሀል፤ ህዝብ  በድለሀል.. ሲሉ ፊት ለፊት ይነግሯቸው ነበር፡፡ እነዚህ ነቢያቶች ለነገስታቶቹ እና ለህዝቡ በአሁኑ ወቅት በህሊናው እና በህገ መንግስቱ መሰረት የሚሰራ ጋዜጠኛ አይነት ሚና ነበራቸው፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ የንጉሱን ጉድለት እና ድክመት ወይም ኢፍትሃዊነት የሚተች ጋዜጣ ገና የሰው አእምሮ አልደረሰበትምና ነው፡፡ ስለዚህም ነቢያቶች ሳይፈሩ ይተቹ ይገስጡ፣ ነበር፡፡ ኢዮርብዓም የሚባለው ንጉስ ለእግዚአብሐር መስዋት በሚቅርብበት መሰዊያ ላይ ለጣኦት በመስዋቱ የእግዚአብሔር ሰው (ነብይ) ወጥቶ በድፍረት ባወገዘው ጊዜ ..ያዙት.. ብሎ ንጉሱ አዘዘ፡፡ በዚህን ጊዜም የንጉሱ እጅ ደርቃ ቀረች፡፡ እንደቀድሞ ለማድረግም ተሳነው፡፡ ንጉሱም ..አሁን የአምላክህን የእግዚአብሔርን ፊት ለምን፤ እጄም ወደ እኔ ትመለስ ዘንድ ስለእኔ ፀልይ.. ሲል ለመነው፡፡ የእግዚአብሔርም ሰው እግዚአብሔርን ለመነለት፡፡ የንጉሱም እጅ ዳነች፡፡ ይህን ጊዜ ንጉሱ ..ከእኔ ጋር ወደ ቤቴ ና እንጀራም ብላ በረከትም እሰጥሃለሁ.. አለው፡፡ የእግዚአብሔርም ሰውን እንዲህ ሲል መለሰለት ..የቤትህን እኩሌታ እንኳ ብትሰጠኝ ከአንተ ጋር አልገባም፡፡ በዚህም ስፍራ እንጀራ አልበላም፡፡ ውሃም አልጠጣም፡፡.. (መጽሐፈ ነገስት ቀዳማዊ ም.13)

ሌላ ምሳሌ ደግሞ እንጨምር ነብዩ አልያስ ንጉስ አክዓብ ጣኦትን ባመለከ ጊዜ ወደ ቤተመንግስቱ ሄዶ ፊት ለፊቱ ቆሞ ..በፊቱ የቆመሁት የእስራኤል አምላክ ህያው እግዚአብሔርን ከአፌ ቃል ቢቀር በእነዚህ አመታት ጠልና ዝናብ አይሆንም.. አለው፡፡ የነብዩ ኤልያስ ቃል ከእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፡፡ እንደ ትንቢቱ ዝናብ ቆመ፡፡ በሶተኛው አመትም ..ሂድ ለአክዓብ  በምድር ላይም ዝናብ እሰጣለሁ.. የሚል የእግዚአብሐር ቃል ወደ ኤልያስ መጣ፡፡ ኤልያስም ለአክዓብ ይገለጥ ዘንድ ሄደ፡፡ በሰማርያም ረሀብ ፀንቶ ነበር፡፡ አክዓብም የቤቱን አዛዥ  ጠራና ..በአገሩ መካከል ወደ ውኃው ምንጭ ሁሉና ወደ ወንዝ ሁሉ ሂድ፤ እንስሶችም ሁሉ እንዳይጠፉ፤ ፈረሶችንና በቅሎችን የምናድንበት ሳር ምናልባት እናገኛለን አለው፡፡ ሁለቱም የሚመለሱበትን አገር ተካፈሉ፤ አክዓብም ለብቻው በአንድ መንገድ አብድዮም ለብቻው በሌላ መንገድ ሄዱ፡፡ አብድዮም ከሄደበት መንገድም ኤልያስን አገኘው አብድዩ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ነበር፡፡ በግንባሩ ተደፍቶ ..ኤልያስ አንተነህን?.. ሲል ጠየቀው፡፡ ኤልያስም ..እኔ ነኝ ሄደህ ለጌታህ ኤልያስ ተገኝቷል በል.. አለው፡፡ ከዚህ በኋላም አብድዮ ለአክዓብ ሄደ ነገረው፡፡ አክዓብም ኤልያስን ሊገናኘው መጣ፡፡ አክዓብም ኤልያስን ..እስራኤልን የምትገለባብጠው ከእግዚአብሔር ይልቅ ጣኦት የሚያመልከው አክዓብ ራሱ እንደሆነ ነገረው፡፡ እናም ህዝቡ ሁሉ እንዲሁም አራት መቶ ሀምሳ የጣኦት ነቢያቶችም በቀርሜሎስ ተራራ ይሰበስቡ ዘንድ ኤልያስ በጠየቀው መሰረትት ንጉሱ ሰበሰባቸው፡፡ አልያስም ..እስከ መቼ ድረስ በሁለት አሳብ ታነክሳላችሁ? እግዚአብሔር አምላክ ቢሆን እርሱን ተከትሎ በአል (ጣኦት) ግን አምላክ ቢሆን እርሱን ተከትሉ.. አላቸው፡፡ (መጽሐፈ ነገስት ቀዳሚው ም.17 እና 18)

እንግዲህ ከዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በርካታ እውነታዎችን ሳንወድ በግድ መቀበል ይኖርብናል፡፡ ጨቋኝ ገዥዎች ራሳቸው እያሸበሩ፤ እራሳቸው ሀገር እየገለባበጡ፤ ድርጊታቸውን የሚተቸውን እና የሚያወግዘውን አገር ትገለባብጣለህን?.. ሲሉ ይከሳሉ፡፡ አክዓብ ኤልያስን እንደከሰሰው እና ኤልያስም በድፍረት ሀገር የሚያተራምሰው ራሱ ንጉሱ እንደሆነ እንደመለሰለት ማለት ነው፡፡

ሌላው አልያስ ..እስከ መቼ ድረስ በሁለት ሀሳብ ታነክሳላችሁ?.. ያለው ቃል በደንብ ሊተኮርበት ይገባል፡፡ አዎን.. በአሁኑ ወቅት መንግስት በሁለት ሀሳብ እያነከሰ ይመስለኛል፡፡ አንዱ ሀሳብ ..አስተዳደሬ ዴሞክራሲያዊ ነው፤ ስልጣን በኢትዮጵያ የሚያዘውም በምርጫ ነው.. የሚል ሲሆን ይሄ የአስፈለገውም በአለም አቀፍ ማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖር ነው፡፡ በእርግጥም እነዚህ ነገሮችን የሚያጠናክሩ እና የሚያረጋግጡ መብቶች በህገ መንግስቱ ላይም እንዲሰፍሩ ተደርገዋል፡፡ ሁለተኛው ሀሳብ ደግሞ ይሄ መንግስት ራሱ ..ውጡና ምረጡ..፣ ..በፈለጋችሁት የፖለቲካ ድርጅት ተደራጁ..፣ ..የመሰላችሁን ሀሳብ ሳትፈሩ ግለፁ.. የመሳሰሉትን ባለው መሰረት ህዝቡ መብቱን መጠቀም ሲጀምር መንግስት ብዙ አድሎት እና ድክመት ስላለበት ከስልጣኑ የሚያወርደው በመሆኑ ..አንዴ አሸባሪ ሌላ ጊዜ.. የጎዳና ላይ ነውጠኛ፣ ..ደርግ፣ ትምክህተኛ ኢንተርሃሞይ ወዘተ... እያለ የሚያፍንበት ነው፡፡ እናም መንግስት በሁለት ሀሳብ ማነከስ የለበትም፡፡ አንዱን መምረጥ አለበት፡፡ ልክ እንደ ደርግ መንግስት የመፃፍ ነፃነትን፣ የመደራጀት መብትን፣ የመቃወም መብትን... በአዋጅ በመንሳት  ግልፅ አምባገነን መሆኑ፡፡ አሊያም በህገ-መንግስቱ እንደሰፈረው እና ጠ/ሚኒስትሩን ጨምሮ ሁሉም ባለስልጣናት በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ እንደሚፎክሩት በሀገሪቷ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲካሄድ ፈቅዶ የሚመጣውን ውጤት በፀጋ መቀበል ነው፡፡

አሁን ያለው ግን በሁለት ሀሳብ ማነከስ ነው፡፡ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ..ዴሞክራት ነን.. እየተባለ የተቃወመን በሙሉ እየወንጀሉ አስሮ   ማሰቃየት፡፡ በይበልጥ ሰሞኑን እየታሰሩ ያሉት ፖለቲከኞቸ እና ጋዜጠኞች ለዚህ ማስረጃ ናቸው፡፡ ሌላው ቀርቶ እስክንድር ነጋን ጋዜጠኛ አይደለም የሚል ክህደት ሁሉ እስከ መናገር የተደረሰበት ሁኔታ አለ፡፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ ይህ ሰው በዚህ ሃያ አመት ውስጥ ከጋዜጣ ስራ ውጭ የትኛውም መስሪያ ቤት ተቀጥሮ አሊያም በየትኛውም ሙያ ተሰማርቶ አላየንም፤ ሲጀመርም ጋዜጠኛ ነው፡፡ በሀገሪቱም የነፃው ፕሬስ የመጀመሪያውን የግል ጋዜጣ ያቋቋመ ባለውለተኛ ጋዜጠኛ ነው፡፡ ሆኖም ግን የታሰረው በጋዜጠኝነቱ አይደለም ለማለት ኤልዛቤል በናቡቴ ላይ እንዳደረገችው አይነት እየተደረገበት ነው፡፡ አንዱአለም አራጌም በሰላማዊ መንገድ የሚታገል የፖለቲካ ፓርቲ አመራር ነው፡፡ አስፈላጊ ከሆነ ፓርቲውን በአዋጅ ማገድ እንጂ ገና ለገና ጠንክሮ እየሰራ ነው በሚል ስጋት ..አሸባሪ.. እያሉ ማሰሩ የማታ ማታ መዘዝ ያመጣል፡፡

የሆነ ሆኖ ናቡቴ ላይ የመሰከሩትን አይነት ምናምቴ መስካሪዎችን እያሰባሰባችሁ ሰላማዊ ዜጐችን ..አሸባሪ.. እያሉ በእስር ማሰቃየት ህዝብንም ማሸበር ሄዶ ሄዶ አንድ ቦታ ላይ ሲደርስ ሊመለስ የማይችል ጎርፍ ሊፈጥር ይችላል፡፡ ይሄ ደግሞ በተለያዩ ሀገሮች ተከስቶ ያየነው ነው፡፡ እናም አንድም በሁለት ሀሳብ አታነክሱ፡፡ በግልፅ መቃወምም ሆነ ትችት መፃፍ አይቻልም በሉ፡፡ አሊያም በህገ መንግስቱ የአሰፈራችሁትን ተግብሩ፡፡ ኤልዛቤል በናቡቴ ላይ እንዳደረገችው አይነት ማድረግ የኤልዛቤልን እጣ ፈንታ እንድትጋሩ ማድረጉ አይቀርም፡፡ እነሆም ለሁላችሁም አስተዋይ ልቦና ይስጣችሁ፡፡ አሜን ይስጠን፡፡